አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

ወርቅነሽ ቱፋ

ሚያዚያ 2004 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የወንድና የሴት ገፀባህሪያት አሳሳል በሶስት የተመረጡ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

አማካሪ - ዘሪሁን አስፋው

በ

ወርቅነሽ ቱፋ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሚያዚያ 2004 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በ

ወርቅነሽ ቱፋ

ሚያዚያ 2004 ዓ.ም

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ	ፊርማ
የውስጥ ፈታኝ	ፊርማ
የውጭ ፈታኝ	ፊርማ

ማውጫ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ምስጋና I

አጠቃሉ II

1. መግቢያ 1

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 1

1.2. የጥናቱ ዓላማ 2

1.3. የጥናቱ ወሰን 3

1.4. የጥናቱ ዘዴ 3

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት 4

2. የተዛማጅ ጥናት ቅኝት 5

2.1. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት 5

2.1.1. ገፀባህሪያት 5

2.1.2. የገፀባህሪያት አይነቶች 8

2.1.3. የገፀባህሪያት አሳሳል ዘዴዎች 9

2.1.4. የገፀባህሪ ትንተና 9

2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 10

3. የወንድ እና የሴት ገፀባህርያት አሳሳል በተመረጡ ሶስት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ 18

3.1. እመ ምኔት 18

3.1.1. የልቦለዱ ታሪክ 18

3.1.2. የሴት ገፀባህሪያት አሳሳል በእመ ምኔት 21

3.1.3. የወንድ ገፀ ባሕርያት ምስል በእመ ምኔት 28

3.2. የደራሲዋ ፋይል 33

3.2.1. የልቦለዱ ታሪክ 34

3.2.2. የሴት ገፀባህርያት ምስል በየደራሲዋ ፋይል 36

3.2.3. የወንድ ገፀባህርያት ምስል በየደራሲዋ ፋይል 41

3.3. የገቦ ፍሬ 46

3.3.1. የልቦለዱ ታሪክ 46

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

3.3.2. የሴት ገፀ ባሕርያት ምስል በየገቦ ፍሬ 49
3.3.3. የወንድ ገፀ ባሕርያት ምስል በየገቦ ፍሬ 55
4. በሶስቱ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የሚታዩ ተመሳስሎዎች እና ልዩነቶች 59
4.1. ተመሳስሎ 59
4.1.1. የዋና ገፀ ባህሪያቱ የዖታ ተመሳስሎ 59
4.1.2. የሰው ቤት ሰራተኝነት 60
4.1.3. የአባቶቻቸው ፍላጎት 62
4.1.4. መታሰር 63
4.1.5. ራስን የመቻል ትግል 64
4.2. በሦስቱ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የሚታዩ ልዩነቶች 65
4.2.1. ሰው ቤት በሰራተኝነት የሚገቡበት ምክንያት 65
4.2.2. የገፀ ባህሪያቱ እጣ ፈንታ 65
4.2.3. ከእስር ቤት የሚወጡበት መንገድ 66
ማጠቃለያ 68
ዋቢ ምንጮች 71

ምስጋና

በቅድሚያ በመማር ማስተማሩ ወቅት በነበረን ቆይታ ያላቸውን ዕውቀት ሳይሰስቱ በመስጠት በፍቅር ላስተማሩኝ የትምህርት ክፍሉ መምህራን እና ጥናቱን እንዲካሂድ የገንዘብ ደጋፍ ላደረገልኝ ለዩኒቨርስቲው ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

እያንዳንዱን የጥናት ክፍል በየደረጃው በመከታተል፣ በማረም፣ የተጣመመውን በማቅናት፣ ለጥናት የሚያስፈልጉኝን መጻሕፍት በመስጠት እንዲሁም ጊዜያቸውን በመሠዋት አስፈላጊውን ምክር እና ክትትል በማድረግ ለዚህ ላበቁኝ ለውድ መምህሬ ዘሪሁን አስፋው ምስጋናዬ በቃላት መግለጽ ከምችለው በላይ ነው። ለሌሎችም እንዲተርፉ ዕድሜና ጸጋውን ያድልልኝ።

በትምህርት ቤት ቆይታዬ የምፈልገውን ሁሉ በማድረግና በማገዝ ፍቅራችሁን ላሳዩኝ ለቤተሰቦቼ በአጠቃላይ ለጓደኞቼ እና የሥራ ባልደረቦቼ በሙሉ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው።

አጠቃለሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በተመረጡ ሶስት መጻሕፍት ውስጥ ማለትም በፀሐይ መላኩ "እመ ምኔት" ፣ በየዝና ወርቁ "የደራሲዋ ፋይል" እንዲሁም በእነዬ ሺበሺ "የገቦ ፍሬ" ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ሴት እና ወንድ ገፀባህሪያት የተሳለበትን መንገድ መመርመር ፣ አካላዊ እና ህሊናዊ መልካቸው ምን እንደሚመስል ማሳየት እንዲሁም በሶስቱ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ያሉትን ተመሳስሎዎች እና ልዩነቶች መመርመርና ማሳየት ነው።

ጥናቱ በተመረጡት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የገሀዱን ዓለም ሰዎች ወክለው የተሳሉት ወንድ እና ሴት ገፀባህሪያት በተወከሉበት የልቦለድ ዓለም የተሰጣቸው ምስል ምን እንደሚመስል ቃኝቷል። ገፀባህሪያቱ ራሳቸውን ነፃ ለማወጣት የሚፍጨረጨሩ ፣ ትዕግስተኛ ፣ ጠንካራ ፣ ታማኝ ፣ በቃላቸው የሚፀኑ ፣ የራሳቸው ፍላጎት ብቻ እንዲሳካ የሚፈልጉ ፣ ሆደ ባሻ ፣ ራስ ወዳዶች ፣ አፅናኝ ፣ መካሪ ፣ ነፃ አውጪ ፣ ቀናተኛ፣ በቶሎ ተስፋ የሚቆርጡ እና የባህል ተጠቂ ሆነው ተስለዋል።

ሶስቱም ረጅም ልቦለዶች የተለያዩ ደራሲዎች ስራዎች ይሁኑ እንጂ በመሀከላቸው አንዳች ተመሳስሎ እና ልዩነት መኖሩም በጥናቱ ተመልክቷል። የዋና ገፀባህሪያታቸው ሴቶች መሆን፣የቤት ሰራተኝነት ፣ እስር ቤት ፣ ነፃነት ፣ ራስን መቻል፣ የመንፈስና የአካል እስረኛ መሆን ... የመሳሰሉት መጻሕፍቱ የሚጋሩአቸው ተመሳስሎዎች ሲሆኑ ሰው ቤት በሰራተኝነት የሚገቡበት መንገድ ፣ ከእስር ቤት የሚወጡበት መንገድ እና የዋና ገፀባህሪያቱ እጣ ፈንታ በጉልህ የታዩ ልዩነቶች ናቸው።

ባጠቃላይ ደራሲዎቹ በየልቦለዶቻቸው የማህበረሰቡን እውነተኛ ገፅታ በወንድና ሴት ገፀባህሪያታቸው አማካይነት ምን እንደሚመስል አሳይተዋል።ገፀባህሪያታቸው በከተማ እና በገጠር ያለውን ህይወት ፣ማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት እንዲሁም ከዕምነት እና ከባህል ጋር ተያይዘው የሚመጡ አመለካከቶች እና ተፅእኖዎች ቁልጭ አድርገው አሳይተውናል።

1. መግቢያ

በአንድ ማህበረሰብ የወንዶችም የሴቶችም መኖራቸው የሚታወቅ ነው ። በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሴቶች እና ወንዶች የሚገኙበትን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ደረጃ ከምናውቅባቸው መንገዶች አንዱ ልቦለድ ነው ።ልቦለድ የተለያዩ ሰዎችን የኑሮ ልምዶች፣ የግለሰቦችን ልዩ ልዩ ገጠመኞች አጠቃላይ የገሀዱን ዓለም እውነታ በተዋበ ቋንቋ የሚያቀርብ የኪነ ጥበብ ዘር ነው። አንድ ደራሲ ለተደራሲው እንዲደርስለት የሚፈልገውን መልዕክት በልቦለዱ ዓለም ውስጥ በሚንቀሳቀሱ ሴት እና ወንድ ገፀባህሪያት አማካይነት ያስተላልፋል። ገፀባህሪያቱን ከሚያስተላልፉት መልዕክት ባሻገርም አንዱን ከአንዱ ለይተን በምናውቅበት መንገድ አካላዊና ህሊናዊ መልክ አላብሶ ይቀርፃቸዋል።

ይህ ጥናት በሶስት ሴት ደራሲያን ፡-በፀሐይ መላኩ "እመ ምኔት"፣ በየዝና ወርቁ "የደራሲዋ ፋይል" እና በእነዬ ሺበሺ " የገቦ ፍሬ" ረጅም ልቦለዶች ላይ የተሰራ ነው።። በአራት ምዕራፎችም ተከፋፍሎ ቀርቧል።

በምዕራፍ አንድ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ እና የጥናቱ አስፈላጊነት እንደቅደም ተከተላቸው ቀርበዋል።።ምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጥናት ቅኝት፣ ምዕራፍ ሶስት በሶስቱ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ ወንድ እና ሴት ገፀባህሪያት ምስል የተተነተነበት ነው።። በምዕራፍ አራት በመጻሕፍቱ ውስጥ ባሉ ገፀባህሪያት መካከል በጉልህ የሚታዩ ተመሳስሎዎች እና ልዩነቶች ተተንትነዋል።

ሰፊውን የጥናቱ ክፍል የያዘው ምዕራፍ ሶስት ሲሆን በዚህ ክፍል ከሶስቱም ልቦለዶች የተመረጡ ሴት እና ወንድ ገፀባህሪያት አካላዊ እና ህሊናዊ መልካቸው በሰፊው ተተንትኗል። ገፀባህሪያቱ ከሌሎቹ ተለይተው የተመረጡበት ምክንያት በልቦለዱ ዓለም ውስጥ ባላቸው ሰፊ እንቅስቃሴ እና ከዋና ገፀባህሪያቱ ጋር ባላቸው መስተጋብር ጭምር ነው።

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የገሃዱ ዓለም እውነታ ከሚንፀባረቅበት መንገድ አንዱ ስነጽሑፍ ነው። ስነጽሑፍ በተለያዩ ቅርጾች የሚከሰት ሲሆን ከነዚህም ቅርጾች አንዱ ረጅም ልቦለድ ነው። በልቦለድ ዓለም ውስጥ

ሴቶች እና ወንዶች ገፀባህሪያት ይህንን የገሃዱን ዓለም እውነታ ለማንፀባረቅ በደራሲዎች አማካይነት መለያ ስም ተሰጥቶአቸው ፣ የሚኖሩበት ቦታ ተበጅቶላቸው ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ።

ደራሲዎች የመረጧቸውን ወንድ እና ሴት ገፀባህሪያት እኩይ እና ሰናይ ባህሪን አላብሰው አንዳች ቁምነገር ወደ ማህበረሰቡ እንዲያደርሱላቸው ይፈጥሯቸዋል። ወንዶችም ሆኑ ሴት ደራሲያን በሚሳተፉበት የስነጽሑፍ ዓለም ውስጥ ሴት እና ወንድ ገፀባህሪያት የሚሳሉበት መንገድ የተለያየ እንደሆነና በተለይም ብዙ ጊዜ በወንድ ደራሲያን በተፃፉ ልቦለዶች ውስጥ ሴት እና ወንድ ገፀባህሪያት የሚሰጣቸው ምስል የተዛባ መሆኑን የሚያሳዩ ብዙ ጥናቶች እናገኛለን።

ሴቶች እንደ ደካማ ፣ግብ ወይም ዓላማ እንደሌላቸው፣ እንደ እናት ፣እንደ ሚስት ፣እንደ ቤት ሰራተኛ ከውበት ጋር ተያይዞ ፣ ረዳት እንደሚሹ ፣ በተቃራኒው ወንዶች ጀግና ፣ ራሳቸውን የቻሉ ፣ቁጡ፣ ደፋር ምስል ተሰጥቷቸው በልቦለድ ውስጥ ይሳላሉ። እኔም ሴት ደራሲያን ገፀባህ ለሴትና ለወንድ ገፀባህሪያታቸው ምን መልክ ሰጥተው እንደሚስሏቸው ፣ በተለይም ስለተቃራኒ ጾታቸው ምን እንደሚያስቡ የተሻለ ሰብዕና ያጎናፅፉአቸዋል ወይስ ማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ አመለካከት እነሱም ተቀብለው ያንፀባርቃሉ? የሚለውን ለማወቅ ፈለግሁ ለዚህም የሶስት ሴት ደራሲያንን ልቦለዶች መረጡ በዚያ ላይ ጥናት ለማድረግ ተነሳሳሁ።

1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በተመረጡ ሶስት የሴት ደራሲያን ማለትም በፀሐይ መላኩ እመ ምኔት ፣ በየዝና ወርቁ የደራሲዋ ፋይል እንዲሁም በእነዱ ሺበሺ የገቦ ፍሬ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ያሉ ሴትና ወንድ ገፀባህሪያት እንዴት እንደተቀረፁ (እንደተሳሉ) መመርመር ነው። የሚከተሉትን አቢይ እና ንዑስ ዓላማዎችን ይዟል።

አቢይ ዓላማ

- በተመረጡት ሶስት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ወንድ እና ሴት ገፀባህርያቱ እንዴት እንደተቀረፁ መመርመር፤
- ወንድና ሴት ገፀባህሪያቱ ከህሊናዊና አካላዊ መልክ አሳሳል አንፃር እንዴት እንደተቀረፁ መመርመር፤ በዚህም ውስጥ የወንድ ወይስ የሴት ገለፃ በዝቷል? የሚለውንም ማሳየት ነው።

ንዑስ ዓላማ

- ወንድና ሴት ገፀባህርያቱ ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ርዕዮት አንፃር እንዴት እንደተቀረፁ መመርመር፣
- ባህሉ ለሴቶችና ለወንዶች የሰጠውን ቦታ በገፀባህርያቱ እንዴት እንደተንፀባረቀ ማሳየት
- እንዲሁም በደራሲያቱ ስራዎች ውስጥ ባሉ እና በተመረጡ ገፀባህርያት መካከል አንዳች ተመሳስሎ እና ልዩነት መኖሩን ማሳየት ነው።

1.3. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በሴቶች በተሰሩ ሶስት ረጅም ልቦለዶች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው። በተመረጡት ሶስት ረጅም ልቦለዶች ውስጥም ለትንተና የተመረጡት ገፀባህርያት የተወሰኑ ናቸው። ለትንተናው የተመረጡበትም ምክንያት በልቦለዶቹ ውስጥ ባላቸው ሰፊ ሚና ወይም ልዩ ተግባር ነው።

ጥናቱ ከልቦለዶቹ ውስጥ በተመረጡ ሴት እና ወንድ ገፀባህሪያት ምስል ትንተና ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን ከዚህ ውጭ ያሉ ሌሎች የልቦለድ ገፅታዎችን(አላባዎችን) አይመለከትም።

መጻሕፍቱ የተመረጡበት መንገድ፡-

1. ደራሲዎቹ በተለይ ፀሐይ መላኩ እና የዝና ወርቁ አንጋፋ ደራሲዎች በመሆናቸው ለሌሎች አርአያ ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ በማሰብ፣
2. አነጡ ሸበሸ ወደ ስነጽሑፍ ከገቡ አዲስ ደራሲዎች መሆኑ ፣
3. ሶስቱም መጻሕፍት በተቀራራቢ ዘመን መታተማቸው ሴቶች በስነጽሑፍ ረገድ እያሳዩ ያለውን እድገት ማሳያ ስለሆኑ ለጥናቱ ተመርጠዋል።

1.4. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በሶስቱ ረጅም ልቦለዶች ላይ ጥልቅ ንባብ በማድረግ ላይ የተመሰረተ ነው። ልቦለዶቹ ውስጥ ያሉ ወንድ እና ሴት ገፀባህሪያትንም በመውሰድ የተመረጡትን ገፀባህሪያት አካላዊና ሀሊናዊ መልካቸውን ይተነትናል። በትንተናውም ንፅፅራዊ ዘዴን ይጠቀማል።

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

ስነጽሑፍ የማህበረሰቡን ባህል፣ አመለካከት፣ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ማንፀባረቂያ አቢይ መሳርያ መሆኑ ይታወቃል። በገሀዱ ዓለም ውስጥ ያሉ ዘርፈ ብዙ የሕይወት ገፅታዎች፣ የእለት ከእለት ህይወት ቁምር ማሳያ መስታወትም ነው።

ይህ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ እውነታዎችን ፈልፍሎ ለማውጣት ይሁን ለማወቅ ስነጽሑፍ ትልቅ እገዛን ያደርጋል። የዚህ ጥናት አስፈላጊነትም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው አመለካከት፣ እምነት እና ፍልስፍና በስነጽሑፍ በተለይ በገፀባህሪያቱ አማካይነት ሲተላለፍ ይህንን ይመስላል ብሎ ወደ አንባቢ ለማድረስ ነው።

በስነጽሑፍ ውስጥ ሴትና ወንድ ገፀ ባህርያት እንዴት እንደሚሳሉ እና በእነርሱ አማካይነትም የፈለቁበት ማህበረሰብ እምነት፣ አመለካከት ፍልስፍና የመሳሰሉትን ነቅሶ ለማውጣት እና ለማሳየት ይጠቅማል።ባጠቃላይ ይህ ጥናት የሴት ደራሲያንን ልቦለዶች ለሚያጠና ሰው እንደመነሻ /እንደ መረጃ/ በመሆን ያገለግላል፣ የሴትና የወንድ ገፀባህርያትን አሳሳል ከሴት ደራሲያን አንፃር ለሚያጠና ሰው መረጃን ይሰጣል፣ ሴት ደራሲያን ለሴትና ለወንድ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ይረዳል። ከዚህም በተጨማሪ የሀገራችንን ሴት ደራሲያን እና ስራዎቻቸውን ለማወቅ ለሚፈልግ ሰው በተወሰነ መልኩ ግንዛቤን ይሰጣል።

2. የተዛማጅ ጥናት ቅኝት

2.1. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት

2.1.1. ገፀባህሪያት

ደራሲያን የገሀዱን አለም ገፅታ በጽሑፎቻቸው አማካይነት ለማህበረሰቡ ለማድረስ ገፀባህሪያትን ይቀርፃሉ።በቀረውአቸው ገፀባህሪያትም አማካይነት የተለያዩ መልዕክቶችን ለአንባብያን ያስተላለፋሉ። እነዚህ ገፀባህሪያትም በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው እምነት ፣ ባህል ፣ትውፊት ፣ ፍልስፍና ፣ አመለካከት ውጤቶች ናቸው። ፈቃደ አዘዘ (1998፣ 4) እንደሚሉት" የማህበረሰቡ አካል የሆነው ደራሲ በሚፈጥራቸው ሴቶች ገፀባህሪያት ዛሬ ከሚኖርበት የእለት ተእለት ሩጫ እያየ ብቻ የሚፈጥራቸው ብቻ ሳይሆኑ ቀደም ብዬ ከጠቀስኩት የባህል እና የአተያይ ኮተት ውስጥም የሚፈለፍላቸው ናቸው ማለት ይቻላል።ይህ የባህል ስንቁ ግን ሆን ብሎ የሚያስበው አይደለም።"

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ደራሲው የፈጠራ ስራውን በሚሰራበት ጊዜ ውስጡ ካለውና አብሮት ከቆየው ምንጩ እየቀዳ የሚጠቀምበት መሆኑን ነው። ገፀባህሪያቱን በሚፈጥርበት ጊዜም አውስጡ ከቆዩት እና በማህበረሰቡ ውስጥ ከተመለከታቸው ህይወታዊ ክንውኖች ውስጥ መርጠ ገጸባህሪያቱን ይቀርፃል። የሚሳሉት ገፀባህሪያትም በልቦለዱ ዓለም ውስጥ አንዱን ከሌላው ለመለየት በሚያስችል መልክ መቅረብ ይኖርባቸዋል።ደራሲው ገፀባህሪያቱን ሰው ናቸው ብለን እንድንቀበላቸው አካላዊና ህሊናዊ መልክ ሰጥቶ ወደ ልቦለድ ዓለም ያመጣቸዋል። በደራሲው እንደተሰጣቸው ቦታ የተለያየ የስራ ድርሻ እና አገልግሎት ይኖራቸዋል።

ገፀባህሪያት ከላይ በተገለፀው መልኩ ለይተን በምናውቅበት መንገድ ተስለው ወይም ተቀርፀው ስናገኛቸው በልቦለዱ ዓለም ውስጥ ብቅ ባሉ ቁጥር ሰብዕናቸውን፣ አመለካከታቸውን ፣ ባህሪያቸውን፣ መልካቸውን ለይተን ልናውቅ እንችላለን። በእነሱም ላይ ያለን እምነት እንዲጨምርና ልክ እንደ እውኑ ዓለም ሰዎች እንድንቀበላቸው ገፀባህሪያቱ " *ዘላቂነት ሊፍዎምነት እና ግለወጥነት /ዘሪሁን1992፣ 161/*። ሊኖራቸው ይገባል። የምናውቀው ባህሪያቸው ያለበቂ እና አሳማኝ ሁኔታ ሊለውጥ አይገባም ፣ ምንም ስህተት እና ጉድለት የሌለባቸው ወይም ምንም የማይሳናቸው ተደርገው መሳል የለባቸውም እንዲሁም የራሳቸው የሆነ እና ከሌሎች ተለይተው የሚታወቁበት ባህሪም ሊኖራቸው ይገባል።

እነዚህ ነገሮች ተሟልተው በሚገኙበት አንድ ልቦለድ ውስጥ የገፀባህሪያትን ምስል ከአካላዊና ህሊናዊ መልክ አንፃር ይህንን ይመስላል እንዲህ አይነት ባህሪ አለው ወይም እንዲህ አይነት ሰው ነው ማለት ብዙ አይከብድም።

ለምሳሌ ወንዶችና ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ፣አተያይ ፣ ህሊናዊ እና አካላዊ መልካቸው ምን ምስል እንዳለው በስነጽሑፍ አሻራነት በግልጽ ማየት ይቻላል። ስነጽሑፍ ማህበረሰቡ የሚያንፀባርቃቸውን እሴቶችና ወጎች መልሶ ለማህበረሰቡ ያንፀባርቃል።ወንዶች እና ሴቶች ገፀባህሪያት እንደየባህሉ እና እንደየ ማህበረሰቡ አመለካከት የሚቀመጡበት ቦታ ፣ አካላዊና ህሊናዊ ምስላቸው የሚቀረፅበት መንገድ የተለያየ ነው። ደራሲው የማህበረሰቡ አካል እንደ መሆኑ ለሚፈጥራቸው ገፀባህሪያት የሚሰጠው ምስል ከሚኖርበት ማህበረሰብ የወጣ አይደለም። Ferguson(1977:10) እንደሚለት "ሴቶች በእያንዳንዱ የእድሜ ክልላቸው በስነ ህይወታዊ ደረጃቸው በተለያዩ ምስሎች ይወከላሉ ለምሳሌ አንዲት ሴት፣ እናት ፣ሚስት ፣ እቁባት ፣ የወሲብ እቃ . . . ተደርጋ ትታያለች ከዚያ ይልቅ ወንዶች ትርጉም የተሰጣቸው ከውጭም ዓለም ጋር ፣ ከተፈጥሮ ጋር ፣ ከማህበረሰብ ጋር ይልቁንም ከአምላክ ጋር ባላቸው ግኑኝነት ነው።ሴቶች ግን ከወንዶች ጋር ባላቸው ግኑኝነት እና ሚና ነው የሚገለጡት"።/

በህብረተሰቡ ውስጥ ስር ሰዶ ያለው አመለካከት በስነጹሑፍ ውስጥም እንዴት እንደሚንፀባረቅ ነው ከዚህ የምንረዳው ።ማህበረሰቡ ወንዶችን እና ሴቶችን የሚያይበት መንገድ ባጠቃላይ በሁለቱም ዕቃ ላይ ያለው ግንዛቤ ባህሉ ፣ እሴቱና ወጉ ከልሎ ያስቀመጠው ቦታ ወይም ድንበር የት ድረስ እንደሆነ ያሳያል። በማህበረሰቡ ውስጥ ሰፍኖ ያለው ወንድና ሴትን ከፋፍሎ እና ደረጃ ሰጥቶ የማየት ሁኔታ የኪነጥበቡንም ዓለም እንደገባው የምንረዳበት ጥሩ ምሳሌ ነው።

አባዛኛቹን የኪነ ጥበብ ስራዎች በምናይበት ጊዜ የዚህ የተዛባ አመለካከት ሰለባ ሆነው ነው የምናገኛቸው ። በየትኛውም ዓለም ያሉ ደራሲያን ከአካባቢያቸው እና ከማህበረሰባቸው ወግ ፣ ልማድ፣ እሴት ፣ አመለካከት ተጽእኖ ስር የወደቁ በመሆናቸው በስራቸውም ላይ እንዳች ተመሳስሎ መኖሩን እንገነዘባለን።

ወደ አፍሪካውያን ጸሐፊዎችም ስንመጣ የወንድ እና የሴት ገፀባህሪያት አሳሳል ተመሳሳይ ሆኖ ነው የምናገኘው። Chukukere (1995:3) "በአብዛኛው የአፍሪካ ስነጽሑፍ ውስጥ የሴት

የቢታችንትና የወንድ የበላይነት የሚያነጸባርቁ ምስሎች በርከት ብለው ይታያሉ።" ይሉናል።

ይህም በእኒኢራቸው እና በእውነተኛ ታሪካቸው ዝቅ ተደርጎ የተሰጣቸው ስፍራ በስነፅሁፍ አለምም እጅግ ሲንፀባረቅ ተስተውሏል። በአባዊው አለም የሚመራው ስነፅሁፍ ሴቶችን በመጥፎ ጎኑ በማንሳት በፈጠራ ስራዎች ሲንፀባረቅ ይታያል። አንዳንዶች ወንድ ጸሐፍያን እውነታውን እንዲሁም ሴት ገፀባህሪያት ያላቸውን እውነተኛ ምስል በመልካም ጎን ቢስሉም በአብዛኛው ግን ማህበረሰቡ በወሰነላቸው እንደ እናትነት፣ ሚስትነት፣ የበታችነት፣ ተሸናፊነት ቦታ ላይ እንዲቀመጡ ነው የተደረገው። ይህንንም ታላላቅ ናቸው በሚባሉት በእነ ቺንዋ አቼቤ ስራዎች ውስጥ ሳይቀር መንፀባረቁን ይነግሩናል Chukukere (1995:7)።

ባጠቃላይ ሴቶች በስነጽሑፍ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ በተመለከተ ያለፈውን ታሪክ ስናጠና አንድ ማወቅ ያለብን ብርቱ ጉዳይ ብዙዎቹ የወንዶችን አተያይ ወይም አመለካከት የሚያንፀባረቁ ሆነው እናገኛቸዋለን። እነዚህ የወንድ ምስሎች ባህላችንን የመሰረቱና ወንዶችንም ሆነ ሴት ጸሐፊያንን የተቆጣጠሩ እንደነበሩ ይህ ግን ብዙ እንዳልዘለቀና አፍሪካውያን ሴት ጸሐፊያን ለዚህ እይነቱ የተዛባ ምስል መልስ መስጠት መጀመራቸውን ይናገራሉ።

አፍሪካውያን ሴት ፀሐፍት የሚስሏቸው ሴት ገፀባህሪያት በልቦለዱ ውስጥ ተጠቃሽ ሚና ያላቸው እና ታሪኩን ተወዳጅ የሚያደርጉ ናቸው። ለምሳሌ የእናትነት ወይም የሚስትነት ድርሻ ከተሰጣቸው እጅግ በጣም ጠንካራ የሆነ የአክብሮትና የታታሪነት ባህሪን የተላበሱ Chukukere (1995:10) አድርገው እንደሚስሏቸው ይገልፃሉ።በምሳሌም እንደ Flora Nwapa እና Buchi Emechataን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ።

አፍሪካውያን ሴት ደራሲያት ብዛት ስናይ ከነበረባቸው ተደራራቢ መገለል የተነሳ ያን ያህል የጎላ ቁጥር እንደሌላቸው እንገነዘባለን። ያሉትም ጥቂት ገፀባህርያት ባገኙት የመፃፍ አጋጣሚም ያላቸውን የተሻለ ሰብዕና በማላበስ በፊት ይቀረፁበት ከነበረው በተቃራኒው ለመቅረፅ እንደሞከሩ እንገነዘባለን።

ወደ ሀገራችን ስንመጣ በቁጥር ጥቂት የሆኑት ሴት ደራሲዎቻችን (ልቦለድን በተመለከተ) ልክ እንደ አፍሪካውያን እቆምቻቸው ሁሉ ሴት ገፀባህሪያቶቻቸውን በጥሩ በመቅረፅ የተሻለ ቦታ እንዲደርሱ በማድረግ እና ጠንካራና በራሳቸው የሚተማመኑ ገፀባህሪያትን በመፍጠር ረገድ ምን ያህል ሰርተው ይሆን?

2.1.2. የገፀባህሪያት አይነቶች

ደራሲው በትረካው ውስጥ የሚያመጣቸው እና የራሳቸውን ታሪክ የሚነግሩን ብዙ አይነት ገፀባህሪያትን እና ስራቸውን ያስተዋውቀናል።የተወሰኑት እና በስፋት የሚታወቁት የሚከተሉት ናቸው፡-

Major or Central Characters - በልቦለዱ ውስጥ ዋናውን ስፍራ የሚይዙና ታሪኩን ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ይዘው የሚጓዙ ሲሆኑ ሴራው እና መፍትሄው በእነርሱ ዙሪያ የሚሽከረከር ነው።

Minor Characters - ዋናውን ገፀባህሪ የሚያጅቡ እንዲሁም ምሉዕ ሆኖ እንዲታይ የሚያደርጉ ገፀባህሪያት ሲሆኑ ሴራው ወደፊት እንዲራመድ ከፍተኛ ሚናን የሚጫወቱም ናቸው።

Dynamic Characters - በጊዜ ሂደት የሚለወጡ ገፀባህሪያት ሲሆኑ ዋናውን ግጭት መፍትሄ የሚሰጡ እና በልቦለድ ዓለም ውስጥ ባላቸው እንቅስቃሴ ብዙ አደጋዎችን የሚጋፈጡ ገፀባህሪያትም ሞምር ናቸው።

Static Characters - የ Dynamic Characters ተቃራኒ ሲሆኑ በጊዜ ሂደት የማይቀየሩ ወይም የማይለወጡ በታሪኩ ሂደት ውስጥም አንድ አይነት ሆነው የሚቆዩ ገፀባህሪያት ናቸው።

Round Characters - በልቦለዱ ዓለም ውስጥ በብዙ ቦታ የምናገኛቸው፡ ታሪኩን ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ይዘው የሚዘልቁ እና ብዙ ታሪክ በእነርሱ ዙሪያ የሚሽከረከር ውስብስብ ገፀባህሪያት ናቸው። እነዚህ ገፀባህሪያት እንደሚያጋጥማቸው ሁኔታ ባህሪያቸው ስለሚለዋወጥ በቀላሉ የሚታወቁ አይደለም። ብዙ ጊዜም በልቦለድ ውስጥ ተግራሪ ሆነው ነው የሚሳሉት።

Flat Characters - ዝርግ ገፀባህሪያት የምንላቸው ሲሆኑ ከ Round Characters በተቃራኒው በቀላሉ የሚታወቁ ፡ በልቦለዱ ውስጥ ብቅ ባሉ ቁጥር ቶሎ የሚታወቅ ሰብዕና ያላቸው ገፀባህሪያት ናቸው።

Symbolic Character - በልቦለዱ ውስጥ ዋና ወይም ንዑስ ሆነው ሊመጡ የሚችሉ ነገር ግን በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን አመለካከት እና እሳቤ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ

የተለየ ቦታ ለሚሰጣቸው እና ከሌሎች ተለይተው የሚታወቁ ነገሮች፣ ሀይማኖታዊ፣ ልማዳዊና ማህበራዊ እሳቤዎችን የሚወክሉ ገፀባህሪያት ናቸው።

2.1.3. የገፀባህሪያት አሳሳል ዘዴዎች

ደራሲያን የፃፉትን ልቦለድ ታሪክ በአንባቢያን ዘንድ ተቀባይነት ያለው ተነባቢና እውነተኛ ለማድረግ እንዲሁም ታሪኩ ህይወት ያለው ይሆን ዘንድ በገፀባህሪያት አቀራረፅ ረገድ አራት ዋና ዋና ዘዴዎችን ይጠቀማሉ እነሱም፦

አካላዊ ገለፃ ፦ የገፀባህሪውን አጠቃላይ መልክ እና አለባበስ ምን እንደሚመስል የምንረዳበት ነው። በውስጡም የገፀባህሪውን የሰውነት መጠን (ወፍራም፣ ቀጭን፣ ረጅም፣ አጭር)፣መልክ(ቀይ፣ጥቁር፣የቀይ፣ዳማ፣ጠይም)፣እድሜ(ሽማግሌ፣ወጣት፣ህፃን)፣አለባበስ የመሳሰሉትን የሚታዩ እና የሚዳሰሱ ነገሮች ይይዛል።

እንጋገርና ተግባር ፦ ገፀባህሪው በተሳለበት የልቦለድ ዓለም ውስጥ በሚሰራው ስራ እና በሚናገረው ንግግር ከሌሎች ገፀባህሪያት ተለይቶ ይታወቃል። ይህም የገፀባህሪውን ንግግር፣ስራ፣ሰብዕና፣ከሌሎች ጋር ያለውን ግኑኝነት በሙሉ ያጠቃልላል።

የሌሎች አስተያየት (አመለካከት) ፦ ሌሎች ገፀባህሪያት ስለእሱ ያላቸው አመለካከት እና አስተያየት ነው።

የገፀባህሪያቱ አመለካከት ፦ ገፀባህሪያቱ የሚያስቡት ፣ የሚፈልጉት ባጠቃላይ ስሜታቸውን ያጠቃልላል።

ባጠቃላይ ገፀባህሪያት በሚቀረፁበት ጊዜ እነዚህን ከላይ ያነሳናቸውን አራት አበይት ነገሮች መሰረት አድርገው ይቀረፃሉ።

2.1.4. የገፀባህሪ ትንተና

በልቦለድ ዓለም የምናገኛቸውን ገፀባህሪያት ምንነት ለማወቅ እና በእነርሱም ዙሪያ አጠቃላይ ትንተና ለማድረግ የሚከተሉትን አቢይ ነገሮች መሰረት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ለትንተና የመረጥነውን ገፀባህሪ ፦

- አስተሳሰብ አመለካከት ፍላጎት ምን እንደሆነ ማወቅ፣
- የገፀባህሪውን አካላዊ ገለፃ ማወቅ መልኩ ፣ ቁመናው ፣ አለባበሱ ... ወዘተ ማየት፣

- ገፀባህሪው የሚናገረውን ነገር መስማት፤
- የሚሰራውን ስራ ምንነት ለይቶ ማወቅ፤
- ሌሎች ስለእነርሱ የሚነግሩንን ከግንዛቤ ማስገባት፤
- ከፈለቱበት አካባቢ አንፃር ምን እንደሚመስሉ ማየት፤
- ለሌሎች ያላቸው አመለካከት፣ ምላሽ እና ለራሳቸው ያላቸው ምላሽ ምን እንደሚመስል ማጤን የገፀባህሪያት ትንተናን ለማድረግ ከማገዙም በላይ የገፀባህሪያቱን አጠቃላይ ማንነት በደንብ ለመረዳት እና ለማስታወስ ይረዳል።እኔም ከላይ የተዘረዘሩትን የትንተና መንገዶች በመጠቀም በተመረጡት ገፀባህሪያት ላይ አካላዊና ሀሊናዊ አሳሳል ትንተናን አድርጌአለሁ።

2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በሴት እና በወንድ ገፀባህሪያት አቀራረጽ ላይ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና በውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ በፒ ኤች ዲ፣ በሁለተኛ ዲግሪ እና በመጀመሪያ ዲግሪ በረጅም ልቦለድ፣ በአጭር ልቦለድ፣ በስነግጥም፣ በተውኔትና በስነቃል ዙሪያ በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል።

እነዚህም ጥናቶች በአፍሪካውያን እና በኢትዮጵያውያን ሴት እና ወንድ ጸሐፍያን /ደራሲያን/ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ናቸው። ጥናቶቹ አንዳንዶቹ የሁለቱም ጾታ ስራዎች የተካተቱበት ሌሎቹ በአንድ ፆታ ላይ ብቻ ያተኮሩ ሲሆኑ፣ ጥናት ከተካሄደባቸው ውስጥ የብዙ ደራሲያንን ልቦለዶች አንድ ላይ በመውሰድ አልያም የአንዱን ደራሲ የተለያየ ልቦለዶች በመምረጥ የተካሄዱ ናቸው። ከስነጽሑፍ ዘውግ አንፃርም በአንዱ የስነጽሑፍ ዘውግ ለምሳሌ፦ በረጅም ልቦለድ ላይ ብቻ ፣ በረጅም እና አጭር ልቦለድ ላይ ፣ ልቦለድንና ግጥምን በመቀላቀል የተጠኑ ጥናቶች ይገኛሉ።

በጥናቶቹ ብዙ ቁጥርን የሚይዘው የሴት ገፀባህሪያት አሳሳል ጥናት ሲሆን በረጅም እና አጭር ልቦለድ እንዲሁም በተውኔቶች ውስጥ ያሉ ዋና ሴት ገፀባህሪያት በሁሉም ጥናቶች ለትንተና የተመረጡ ናቸው። ከስነ ቃል አንፃር ሴቶች በተረትና ምላሌ ውስጥ እንዴት ተቀርፀዋል? የሚል ትንታኔ የተሰጠበት ጥናትም አናገኘለን።። ስነግጥምም ውስጥም በተመሳሳይ መልኩ ወንዶች እና ሴት ገጣሚያን ለተመሳሳይ እና ተቃራኒ ጾታቸው ያላቸውን አመለካከት /የቀረፁበት መንገድ/ ትንታኔ ተሰጥቶታል።

የተዛማጅ ጥናቶቹ በሴት ደራሲያን ላይ ብቻ በማተኮር የተጠኑ እንዲሁም የወንድና የሴት ገፀባህሪያት አሳሳል ላይ የተሰሩ ብዙ ጥናቶች የሉም በዚህም ምክንያት ሁሉም ጥናቶች ከኔ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግኑኝነት ስለሌላቸው በዚህ ጥናት ውስጥ አልካተቱም::እኔም ቀጥተኛና ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናቶች በመውሰድ በኤም ኤ እና በቢ ኤ ደረጃ በመክፈል ከተጠኑበት ዓመተ ምህረት አንፃርም በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ቃኝቻለሁ።

- **በኤም ኤ ደረጃ የተሰሩ ስራዎች**

አሰፋ ወርቁ በ1995 "An Analysis of Literary Techniques in Some of the Prose Works of Ethiopian Authoresses 1959-1985 E.C" በሚል ርዕስ ለድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራም ያቀረበው ጥናት አንዱ ነው።

ጥናቱ ከ1959-1985 ዓ.ም ድረስ በወጡ የ12 ሴት ደራሲያን ማለትም የአስራት ገ/ጻድቅ፣ የእየሩሳሌም ይስማው፣ የገነት ባህሩ፣ የመስታወት መሉአለም፣ የመጠነወርቅ ሳሙኤል፣ የውድነሽ ሀይሌ፣ የወደርየለሽ ማይክል የዘውዲቱ አሸብር፣ የእልፍነሽ በኩረ፣ የፀሐይ መላኩ፣ የእምወድሽ በቀለ እና የየዝና ወርቁ ድርሰቶች ላይ ሲሆን በሶስት ዋና ክፍሎች በመከፋፈል ከአማካኝ ቴክኒክ /ዘዴ/ አንፃር ትንተናን አድርጓል።

አሰፋ በጥናቱ ሁለት አበይት ጉዳዮች ያነሳ ሲሆን እነሱም ንድፈ ሀሳባዊ ዳሰሳ እና ቅድመ አብዮት የነበሩ ሴት ደራሲያት ስራዎች ላይ የሚታይ የገለፃ እና የትረካ አቅጣጫ ናቸው። በዚህ ክፍል ብዙ ሴት ደራሲያት ቢኖሩም በተለይ ቅድመ አብዮት የነበሩ ሴቶች ብዙም የሚታወቁ አለመሆናቸውን ይገልፃል። በቅድመ አብዮት የነበሩ ሴት ደራሲያንን ስራዎች አንድ በአንድ በማንሳት ደብዳቤያዊ አማካኝ የሚንፀባረቅባቸው፣ ሁሉን አወቅ፣ እኔ ባይ ተራኪ የትረካ አቅጣጫዎች ወይም ዘዴዎች ይከተሉ እንደነበር መጽሐፋቸውን በመረጃ በማቅረብ ትንታኔ ሰጥቶበታል።

በድህረ አብዮት የነበሩ አራት ደራሲያትን የትረካ ዘዴ ሲተነትን የዝና ወርቁ፣ የምወድሽ በቀለ፣ ፀሐይ መላኩ እና አልፍነሽ በኩረን በማንሳት ሴት ደራሲያቱ አዲስ የትረካ ስልት መጠቀማቸውን፣ ከነዚህም አዲስ የትረካ ስልት ውስጥ የስልክ ልውውጥ፣ በህልም ዘዴ፣ ንግር፣ ምልሰት እንዲሁም በታሪክ ውስጥ ሌላ ታሪክ የአተራረክ ዘዴዎችን መጠቀማቸውን፣ ከትረካ አንፃርም ሁሉን አወቅ ትረካ እንደሚያዘወትሩ መጻሕፍቱን ዋቢ በማድረግ ተንትኗል።

በቅድመ እና ድህረ አብዮት ባሉት ሴት ደራሲያት ስራዎች ውስጥ ያሉትን የገፀባህሪያት አቀራረፅ፣ የሴራ አወቃቀር እና ቋንቋ አጠቃቀም ከገፀባህሪ አቀራረፅ አንፃር ተአማኒነት፣ ዘሰቂነትና አንጊነት እንዲሁም ከቋንቋ አንፃር ተገቢነት፣ ቁጥብነት እና ተያያዥነት ምን እንደሚመስል ስራዎቹን በመረጃ በማስደገፍ ስፋ ያለ ትንታኔን ሰጥቶበታል።

አሰፋ በቅድመ እና ድህረ አብዮት ያሉ ሴት ደራሲያት ስራዎች ውስጥ በዛ ያሉ /ብዙ አይነት/ የትረካ ዘዬዎችን መጠቀማቸውን በተለይም ደብዳቤ የሚመስሉ የአፃፃፍ ዘዬዎች መንፀባረቃቸውን ጭምር በማንሳት ያጠቃልላል። የአሰፋን ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በሴቶች በተፃፉ ድርሰቶች ላይ ጥናት ማድረጉ ፣የሚለየው ደግሞ የሱ ጥናት የድርሰቶቹ የአፃፃፍ ቴክኒክ ላይ ትኩረት ሲያደርግ የኔ ጥናት በልቦለዶቹ ውስጥ ያሉ ገፀባህሪያት አሳሳል ላይ ያተኮረ ነው።

ሙሉመቤት ዘነበ እ.ኤ.አ በ1996 "A Comparative Analysis of the Images of Men and Women in the Works of Some Ethiopian Women Writers" በሚል ርዕስ ለማስተርስ ዲገሪ ማሟያ ጥናት አቅርባለች።

ሙሉመቤት ጥናቷን ያካሄደችው በሴቶች የተፃፉ አራት ረጅም ልቦለዶች እና ሶስት አጭር ልቦለዶች ላይ ነው ። ከረጅም ልቦለድ- የፀሐይ መላኩ ቋሳ እና አንተዝ፣ የእልፍነሽ በኩረ ጽልሙት እና የመቅደስ አስናቀ መሀጌ፣ ከአጭር ልቦለድ የየገዛኝ ወርቁ የቅርብ ሩቅ እና ሰናይት አንዲሁም የእምወድሽ በቀለን እነግረዋለሁን በጥናቷ አካታለች።

በተሟማጀ ጥናት ቅኝቷ በአውሮፖውያን፣ በአሜሪካውያን እና በአፍሪካውያን ስነጽሑፍ ውስጥ ሴት ገፀባህሪያት /ምስለ ሴት/ Image of Women እንዴት እንደተቀረፀ ትገልፃለች። ለጥናቷ ከመረጠቻቸው ልቦለዶች ውስጥ የተወሰኑትን ወንድ እና ሴት ገፀባህሪያት በመምረጥ ተሸካርማሚ ሴት እና አሸኮርማሚ ወንድ፣ በባህሉ የተጠቁ ገፀባህሪያትና ባህሉን በመጋፈጥ ጠንካራ የሆኑ ገፀባህሪያት በሚል በሁለት ንዑሳን ክፍል በመከፋፈል ትንተና ሰጥታባቸዋለች።

ሙሉመቤት ገፀባህሪያቱ በፈለቁበት ማህበረሰብ ውስጥ ባለው አስተሳሰብ /አመለካከት/፣ ባህል እንዲሁም በተቃራኒ ፆታ ሳቢያ የአመለካከቱ፣ የባህሉ ተጠቂ ሆነው እንደሚታዩ ታሳያለች። የተቀሩት ደግሞ ባህሉን አመለካከቱን እና የተቃራኒ ፆታ ተዕዕኖውን በመቋቋም የሚወጡ ጠንካራ ገፀባህሪያት ሆነው መሳላቸውን በንዕዕር ተንትናለች።

ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ባህል ወንዶቹንም ሴቶቹንም ገፀባህሪያት ለጉዳት እንደዳረጋቸው ትገልፃለች። ይህ ጉዳት /ተጠቂነት/ በሴቶቹ ላይ እንደሚያይል ባህሉ እና ልማዱ ወንዶች እና ሴቶችን እኩል እንደማያያቸው እና ብዙዎቹ ሴቶች በመጨቆን እና በመገለል ውስጥ ሆነው መሳላቸውን በንዕዕር ተንትና አሳይታለች። ሴት ደራሲያኑ ለሴት ገፀባህሪያት አድልኦ እንዳደረጉላቸው በተለይም ካለበቂ ምክንያት ወይም መነሻ ባንድ ጊዜ ተለውጠው ትልቅ ደረጃ ሲደርሱ ማሳየታቸውን በተቃራኒው ወንዶችን ግን በህይወታቸው መጨረሻ ላይ ክፉ ነገር ሲገጥማቸው እና ለውድቀት ሲዳረጉ መሳላቸውን ተንትናለች።

መሉአመቤት በማጠቃለያዋ እና በግኝቷ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ቦታ ሲሰጣቸው የኖረው ስነፆታ /Gender/ ያመጣው ጣጣ መሆኑንና ማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ባህል ማህበረሰቡን በሚፈልገው መንገድ በመቅረፁ ማህበረሰቡ ለወንዶች እና ለሴቶች የሰጠው ቦታ በእጅጉ መለያየቱን ገልፃለች። ይህ ደግሞ የስነ ፆታ አቀንቃኞች እንዲነሳሱ ምክንያት እንደሆናቸው፤ ሴቶች የተቀረፁበት መንገድ ትክክል አለመሆኑን ከስነጽሑፍ ውስጥ ነቅሰው በማውጣት ለማረጋገጥ መሞከራቸውንና ሌሎች ፆታ ነክ እንቅስቃሴ ለማድረግ በር እንደከፈተላቸው እንስታለች። የመሉመቤት ጥናት የወንድ እና የሴት ገፀባህሪያትን ምስል መነሻ በማድረግ መተንተኑ ከኔ ጥናት ጋር በእጅጉ የሚያመሳስለው ሲሆን ፆታን መሰረት አድርጎ በተለይም በስነ እንስታውያን አተያይ መቃኘቱም ከእኔ ጥናት በእጅጉ የሚለይ ነው።

ናፆሊዮን ክፍሌ በየነ በ2000 "Major Themes in the Works of Four Ethipian Women Writers" በሚል ርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ሌላው ነው። ናፆሊዮን የጥናት ስራውን ያካሄደው "እኛ 170" ግጥሞች ከሚለው የግጥም መድበል ከአረጋሽ ሰይፉ፤ ከመቅደስ ጀምበሩ፤ ከፊርማዬ አለሙ እና ከሰናይት አበራ አምስት ግጥሞችን መርጦ በመውሰድ በአራት ምዕራፎች ተከፋፍሎ ትንተና አድርጎባቸዋል።

ናፆሊዮን በአራቱ ሴት ገጣሚያን ግጥሞች ውስጥ ጉልህ ሆነው ባገኛቸው ተመሳሳይ ጭብጦች ትንታኔ የሰጠ ሲሆን በግኝቱ በአራቱም የግጥም መድበሎች ውስጥ ፍቅር፤ ስነምግባር፤ ህይወት /ሞህይወት ፍልስፍና/፤ አስገድዶ መደፈር እና ሰብዕና በተመሳሳይ መልኩ አራቱም ገጣሚያን የሚመሳሰሉባቸው ዋና ጭብጦች መሆናቸውን ጠቅሷል።ገጣሚያኑ በግጥሞቻቸው ምን አይነት መልዕክት እንዳስተላለፉ፤ ያሉበትን ማህበረሰብ እንዴት እንደሄሱ፤ እንዲሁም ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና፤ ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን እንዴት እንዳንፀባረቁ ግጥሞቻቸውን መነሻ በማድረግ ተንትኗል። ከዚህም በተጨማሪ የቃላት አጠቃቀማቸውንና

ዜማ አጠባበቃቸውን ተመልክቷል። በእኔ እና በናፖሊዮን ጥናት መካከል ያለው ተመሳሳይነት የተጠኑት የሴቶች ድርሰቶች መሆናቸው ነው።

ሰብለ ወልደ ኪዳን በ2009 እ.ኤ.አ "The Image of Women in Sisay Nigusu's Novels" በሚል ርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናቷን አቅርባለች።

ለጥናቷ የመረጠችው የደራሲ ሲሳይ ንጉሱ ረጅም ልቦለዶች ግርዶሽ፣ የቅናት ዛር፣ እና ረቂቅ አሻራ ሲሆኑ ከሶስቱ ልቦለዶች ውስጥ አምስት ሴት ገፀባህሪያትን በመምረጥ ትንተና አቅርባለች።

ሰብለ በትንታኔዋ በልቦለዶቹ ውስጥ የተሳሉት ገፀባህሪያት በአብዛኛው ያሉበት የችግር ኑሮ ተስማሞቶአቸው፣ ሁሉን ችለው የሚኖሩ ፣ ስሜታቸውን ገልጠው ለትዳር አጋራቸው መናገር የማይደፍሩ፣ ለባሎቻቸው ተሸናፊ ሆነው የሚኖሩ መሆናቸውን አሳይታለች። ችግራቸውን በራሳቸው መፍታት የማይችሉ ፣ የወንድ ጥገኞች፣ ከትዳር ውጭ ተስፋ ያላቸው የማይመስላቸው፣ ሴሰኞችና ችግር ፈጣሪዎች ተደርገው መሳላቸውን ከልቦለዶቹ መረጃን በመጥቀስ ተንትናለች።

በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ ካሉት ገፀባህሪያት ረቂቅ አሻራ ውስጥ የምትገኘው ህሊና ብቻ በተቃራኒው በአምንታዊ መንገድ መሳሏን ጭምር ታስረዳለች። ይህች ሴት በራሷ የምትተማመን፣ በፈቃዷ የምታድር፣ በራሷ ነፃ ፍቃድ የምትኖር ነፃ ሴት ተደርጋ መሳሏን በትንታኔዋ አሳይታለች ።

ከዚህም በተጨማሪ በሶስቱም ልቦለዶች ውስጥ ያሉትን ሴት ገፀባህሪያት ችግርን የመፍታት ችሎታ እና ለትዳር ያላቸውን አመለካከት በንፅፅር አቅርባለች። በማጠቃለያም ደራሲ ሲሳይ ንጉሱ ረቂቅ አሻራ ላይ ካለችው ህሊና በስተቀር በሁለቱ መጻሕፍት ውስጥ ያሉትን ሴት ገፀባህሪያት ባብዛኛው በአሉታዊ ገፅታቸው መሳሉን እና ህሊናን ብቻ ከሌሎች ሴት ገፀባህሪያት በተለየ መልኩ በአምንታዊ ጎን እንደሳላት አሳይታለች። ይህም ደራሲው የፃፋቸው ልቦለዶች ሲታዩ በሂደት የተሻለ ሰብዕናን በመቅረፅ ረገድ ለውጥ አምጥቷል ትለናለች። ሰብለ በጥናቷ የገፀባህሪያቱ ምስል አቀራረፅ ላይ ትንታኔን መስጠቷ እንዲሁም በልቦለዶቹ ውስጥ ያሉትን ገፀባህሪያት ተመሳስሎና ልዩነት ማንሳቷ ከኔ ጥናት ጋር በእጅጉ ሲያመሳስላት በወንድ ደራሲ ልቦለዶች ማተኮሯ ከኔ ጥናት ጋር ይለያታል።

- **በቢ ኤ ደረጃ የተሰሩ ስራዎች**

በአለም ባይለየኝ በ1984 ዓ.ም "ሴቶች በሴቶች ደራሲያን አይን" በሚል ርዕስ ለቢኤ ዲግሪ ማሟያ የተሰራው ጥናት ሌላው ያታን መሰረት አድርጎ የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው። አለም ለጥናቷ የመረጠቻቸው ልቦለዶች፡- የዝና ወርቁና ጀማል ሱሌይማን "የተሸጠው ሰይጣን"፣ የአምወድሽ በቀለ "የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም" እና የፀሐይ መላኩ "ቋሳ" ሲሆኑ ጥናቷን በሶስት ዋና ዋና ምዕራፎች በመከፋፈል ትንተና አቅርባለች።

ዓለም በጥናቷ የሶስቱን ደራሲያን ሴት ገፀባህሪያት ውጫዊና ውስጣዊ መልክ ምንነት እንዲሁም የየልቦለዶቹን ታሪኮች ባጭሩ አቅርባ አካላዊና ህሊናዊ መልካቸውን በሁለት ንዑሳን ክፍል በመክፈል በገፀባህሪያቱ ምልልስ እና በደራሲያኑ አማካይነት የተገለፀው በማለት ትንታኔን ሰጥታለች።

ህሊናዊ መልካቸውን በሚመለከት በየልቦለዶቹ ያሉትን ሴት ገፀባህሪያት በእድሜ የገፉ፣ በማግባት የተሳካላቸው፣ በትምህርት ቤት ህይወት ያለፉና ከአዘቅት ወደ ጥሩ ህይወት የሚያመሩ ሆነው መሳላቸውን ትተነትናለች። የሶስቱ ሴት ደራሲያን ገፀባህሪያት እናትነት፣ ባለትዳር መሆን እና ሴተኛ አዳሪነት በተመሳሰሎ እንዲሁም በትዳር ውስጥ የሚገጥማቸውን ችግር የሚፈቱበት መንገድ እና ወደ ሴተኛ አዳሪነት የሚገቡበት መንገድ በእጅጉ እንደሚለያይ በትንታኔዋ አሳይታለች። ጉቦ፣ ሴተኛ አዳሪነት የሚያስከትለው የህሊና ቁስል፣ ጋብቻና ፍቺ፣ አረጋውያንን መንከባከብ እና የልጅ አስተዳደግ ከሶስቱም መጻሕፍት ውስጥ ያገኘቻቸው ዋና ዋና ጭብጦች መሆናቸውንም ትጠቅሳለች።

አለም በማጠቃለያዋ የአምወድሽ በቀለ "የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም" ከሁለቱ መጻሕፍት በተለየ መልኩ እናትነትን በተደጋጋሚ ማንሳቱንና ደራሲያኑ ገፀባህሪያታቸውን እስከመጨረሻው ጠንካራ አድርገው ለመሳል መሞከራቸው ወገናዊነት ይመስላል የሚል ድምዳሜ ሰጥታለች። የሴት ደራሲያን ልቦለዶች ላይ ገፀባህሪያቱን ከህሊናዊ እና አካላዊ ገፅታቸው አንፃር መተንተኗ በልቦለዶቹ መሀከል ያሉ ተመሳሰሎና ልዩነትን ማሳየቷ ሲያመሳስለን ረጅም እና አጭር ልቦለዶችን ቀላቅላ በማጥናት እንዲሁም ጭብጥን ማንሳቷ ከኔ ጥናት ጋር ይለያያል።

ብሌን በላይነህ በ1992 ዓ.ም "የሴት እና የወንድ ገፀባህሪያት አሳሳል ንፅፅራዊ ጥናት በሁለት የአማርኛ አጭር ልቦለድ ስራዎች ውስጥ/ በሙሉጌታ ጉደታና ሳሙኤል ልጃለም/" በሚል ርዕስ ለዲግሪ ማሟያ የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ ያቀረበች ሲሆን ለጥናቷ መነሻ ያደረገቻቸው መጻሕፍት

የመሉጌታ ጉደታ "የአራዳ ልጆች"፣ "የተክፋፈለ ልብ" እና "የተቀጠፈች ፅጌሬዳ" እንዲሁም የሳሙኤል ልጃለም "ማጥምጥም" እና "ያፈነገጠ ወጥመድ" ናቸው።

ብሌን በአፍሪካ ስነ ጽሑፍ ውስጥ የሚታዩ የወንድና የሴት ገፀባህሪያትን አሳሳል ባጭሩ በመዳሰስ የተመረጡት ደራሲያን በድርሰቶቻቸው ወንድና ሴት ገፀባህሪያትን እንዴት እንደቀረጿቸው ትተነትናለች። ደራሲያኑ ወንዶች በመሆናቸው ለወንዶች ገፀባህሪያት ከፍተኛ ቦታ የመስጠት ለሴቶቹ ደግሞ ዝቅተኛ ቦታ የመስጠት ነገር ይታይባቸዋል ወይ? የሚሉትን ጥያቄዎች በትንታኔዋ እንደምትመልስ ጭምር ትገልፃለች።

በሁለቱ ደራሲያን ድርሰቶች ውስጥ ሴት እና ወንድ ገፀባህሪያትን እንዴት እንደተሳሉ በዝርዝር አቅርባለች። በሁለቱም ጸታዎች አላማ ያላቸው፣ መንፈሰ ጠንካራ፣ የአስተሳሰብ ድክመት ያለባቸው፣ በማመዛዘን ውሳኔ የሚሰጡ፣ ማስተዋል የጎደላቸውና ውሳኔ ለመስጠት የሚቸኩሉ ገፀባህሪያት የተሳሉ መሆናቸውን በማነፃፀር ተንትናለች።

ለምሳሌ ሴት ገፀባህሪያቱ አላማ ያላቸው፣ አላማቸውን ከግብ ለማድረስ ሌት ተቀን የሚተጉ፣ ጠንካሮች፣ የራሳቸው አቋም ያላቸው፣ ለፍቅረኞቻቸው ታማኝ የሆኑ በተቃራኒው ሌሎቹ ሣሬን ብቻ የሚኖሩ እና ለወደፊቱ የማያስቡ፣ የህይወትን ምንነት ገና ያልተረዱ፣ በገዛ ነፍሳቸው ቁማር የሚጫወቱ፣ ስለተቃራኒ ፆታ ጓደኞቻቸው ደንታ የሌላቸው፣ የራሳቸውን ፍላጎት ብቻ ለማሟላት የሚጥሩ ሆነው መሳላቸውን አሳይታለች።

ገፀባህሪያት ውስጣዊ ማንነት አሳሳል ከፅናት ፍቅር፣ ትዕግስት፣ ፍልስፍና፣ ጥገኝነት እንዲሁም ከማህበራዊ ጉዳዮች አንፃር ከስራ፣ ትምህርት እና ትዳር አንፃር እንዴት ተደርገው እንደተቀረፁ ከመዕሐፉ ማሳያ በመውሰድ የሁለቱንም ፆታዎች አሳሳል በማነፃፀር ትንታኔ ሰጥታለች።

ዘሪሁን አስፋው በ1997 እ.ኤ.አ "Women In The Works of Ethiopian Short Story Writers " በሚል ርዕስ አስራ ሶስተኛው አለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ ላይ በቶኪዮ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ እንዱ ምስልን መሰረት አድርጎ የተሰራ ጥናት ነው።

ዘሪሁን ከተመረጡ 10 ደራሲዎች የተወሰዱ 133 አጭር ልቦለዶች ውስጥ 100 ሴት ገፀባህሪያትን በመምረጥ ሴት ገፀባህሪያቱ በየልቦለዶቹ የተቀረፁበትን መንገድ አሳይተዋል። ልቦለዶቹ ፍቅር፣ ጋብቻ ፣ የባህል ተቃርኖ ፣ህይማኖት ፣ትምህርት፣ ባህል፣ ጓደኝነት ፣ የፅድሜ ፣ ልዩነት መሰና ፣ድህነት ፣ሴተኛ አዳሪነት ጠጪነት የመሳሰሉ ጭብጦች መያዛቸውን ይነግሩናል።

በልቦለዶቹ ውስጥ ያሉ አጠቃላይ ምስሎችንም በተመለከተ በስድስት ክፍሎች በመክፈል ያላገባች ሴት፣ ብቸኛ ሴት ፣ እናት፣ ሚስት፣ የቤት ሰራተኛ እና ሴተኛ አዳሪ ምስል ሰጥተው እንደቀረፁአቸው ተንትነዋል። ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ካለው የሴት ልጅ አመለካከት የመነጨ መሆኑን ይነግሩናል።

በማጠቃለያቸውም ደራሲያኑ የሴቶችን ምስል ከመቅረፅ አንፃር አዲስ ልምድን እንዳላሳዩ እንዲሁም ከስነ ፆታ ባህሪ ውጭ ያለውንም የሴቶችን ተግባር እንዳላካተቱ በመግለፅ የኢትዮጵያዊያን ሴቶችን ጠንካራነት እና ጀግንነት አጣምሮ ቢቀርብ ጥሩ መሆኑን በጥናታቸው ይጠቁማሉ።

ባጠቃላይ የተዛማጅ ጥናቶቹ ከስነጽሑፍ አላባውያን አንዱን በመምረጥ በአንዱ ነገር ላይ ብቻ ትኩረት አድገርው መስራታቸው፣ያታን መሰረት ያደረገ ጥናት ማካሄዳቸው ከዚያ በፊት ብዙም ያልተለመደ በመሆኑ እንዲሁም ባብዛኛው አንድ ጥናት መያዝ ያለበትን አቢይ ጉዳይ አካተው መቅረባቸው ያላቸውን ጥንካሬ የሚያሳይ ሲሆን አንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ መስራት ሲገባቸው አጠቃላይ ርዕስ በመያዝ ለማጥናት መሞከራቸው ፣ በጥናት ስራዎቹ ውስጥ የሚታየው የወጥነት ጉድለት ለምሳሌ ግጥም እና ልቦለድ፣ ረጅምና አጭር ልቦለድ እንዲሁም የኢትዮጵያና የአፍሪካ ደራሲያን ስራዎች ተቀላቅለው መጠናታቸው፣ በዋናነት የሚጠቀሱ ድክመቶች ናቸው። ብዙዎቹ ጥናቶች የገፀባህሪ አሳሳል ብለው ይነሱ እንጂ ያታን መሰረት አድርገው የተሰሩ በመሆናቸው እና ከኔ ጥናት ርዕስ ጋር የሚሄዱ ስላልነበሩ የተወሰኑትን ብቻ ለጥናቴ መርጫለሁ።

3. የወንድ እና የሴት ገፀባህርያት አሳሳል በተመረጡ ሶስት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ

በዚህ ክፍል በፀሐይ መላኩ እመ ምኔት፣ በየዝና ወርቁ የደራሲዋ ፋይል እንዲሁም በእነዬ ሺበሺ የገቦ ፍሬ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ያሉ የወንድ እና የሴት ገፀባህርያት ምስል ወይም አሳሳል ይተነተናል ::

ከየልቦለዶቹ አራት አራት ገፀባህርያት፡ ከሴቶች ሁለት ከወንዶች ደግሞ ሁለት ለትንተናው ተመርጠዋል:: ገፀባህሪያቱ ለትንተናው የተመረጡበትም ምክንያት በዋናነት የልቦለዱ ታሪክ የነሱ በመሆኑ እና በታሪኩ ውስጥ ከመጀመሪያው እስከ ፍጻሜው የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ሞምር ነው:: ብዙዎቹ የልቦለዶቹ ገፀባህርያት በተለይም ከዋናዎቹ ገፀባህርያት ውጭ ያሉት ንዑሳን ገፀባህርያት በታሪኩ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ መሆኑ ወይም በታሪኩ ውስጥ ብልጭ ብለው የሚጠፉ በመሆናቸው ለትንተናው አልተመረጡም:: ከነዚያ ውስጥ አንዳንዶቹ ለልቦለዱ ወደፊት መራመድ በእጅጉ አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ ትንሽም ቦታ ቢታዩ ለትንተና ተመርጠዋል::

3.1. እመ ምኔት

3.1.1. የልቦለዱ ታሪክ

ወደ ገፀባህሪያቱ ትንተና ከመግባቴ በፊት የልቦለዱን ታሪክ ባጭሩ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

የእመ ምኔት ረጅም ልቦለድ ታሪክ የልቦለዱ ዋና ገፀባህሪ በሆነችው በዘርትሁንና በእንጀራ እናቷ ባዩሽ መካከል በሚፈጠር ፀብ ይጀምራል:: የዘርትሁን እናት በሞቱ በጥቂት ግዜያት ውስጥ በይፋ ቤቱን በመረከብ ሁለተኛ ሚስት የሆነችው ባዩሽ ይማም እና የእናቷን ፍቅር በሞት የተነጠቀችው የዘርትሁን ፀብ የቤቱ ኃላፊ የሆኑት አቶ ስለሺ መቆጣጠር እና መፍትሄ መስጠት አስኪያቅታቸው ድረስ እየተካረረ ይሄዳል:: ይህም የየቀን አግቦ እና አሽሙር ወደ ከፍተኛ መካረር ደርሶ ለባዩሽ ሞት ምክንያት ይሆናል::

በእንጀራ እናቷ ሞት የተደናገጠችው ዘርትሁን ከቤት ሮጣ በመውጣት እዚያው አካባቢ እሚኖሩት የክርስትና እናቷ ወ/ሮ ግምብወግሽ ቤት ትሄድና የሆነውን ሁሉ ነግራቸው በቤታቸው ይሸሸጓታል:: በኋላም በህመም ምክንያት ከዝቋላ ገዳም መጥተው እቤታቸው

በተኙት መነኩሲት ዘመዳቸውና እሳቸውን ለመጠየቅ በእለቱ በተገኙ ሌሎች መነኮሳይት አማካይነት ወደ ዝቋላ ገዳም እንድትሄድና እንድትሸሸግ ያደርጓታል።

በአጋጣሚ ዘርትሁን የእንጀራ እናቷ ስትሞት ለብሳው የነበረው ሸሚዝና ሱሪ የተደበቀበት እንስራ በውሰት ሰበብ ጎረቤታቸው ከሆነው ከቀበሌው ሊቀመንበር ከአቶ አለባቸው ቤት ይሄድና ሲታጠብ ከውስጡ በመገኘቱ ወ/ሮ ግምብወግሽ በቀበሌው ሊቀመንበር በአቶ አለባቸው አይን እንዲጠረጠሩ ያደርጋቸውና በፖሊስ ጥብቅ ክትትል አና ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። ዘርትሁንን ከደበቁበት እንዲያመጧት እና እውነቱን እንዲያወጡ በየጊዜው በደረሰባቸው ድብደባና እንግልትም ለህልፈተ ህይወት ይዳረጋሉ።

ዘርትሁን በገዳም ቆይታዋ ዩኒቨርስቲ የመግባትና የመማር ህሳቧን ቀይራ ወደ መንፈሳዊ ዓለም ታዘነብላለች። ለመመንኮስም ትወስንና ለዚያ የሚያበቃትን የወጣኒነት አገልግሎት በመስጠት ውሃ በመቅዳት፣ ደካማ አረጋውያንን በማገልገል እና ሁሉንም የገዳም ስራ በመስራት ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር ትቆያለች። የወጣኒነት ጊዜዋን ጨርሳ ለመመንኮስ ስትበቃም ሸሽታ ወደ ገዳም በመጣች ጊዜ በእሷ እና በክርስትና እናቷ የተደረገውን ስዕለት ለመፈፀም ወደ አዲስ አበባ ትመጣና ይደነቁ በሚል ስም ራሷን ሰውራ በሰው ቤት ሰራተኝነት ትቀጠራለች።

ለስዕለቷ መፈፀሚያ የሚበቃትን ገንዘብ ሰርታ ካገኘች በኋላ "እናትና አባቴን ማየት አለብኝ" በሚል ሰበብ የምትሰራበትን ቤት ባለቤት አቶ ውድነህን ፣ባለቤቱን ወ/ሮ ኤልሳቤጥንና እጅግ አድርጋ የምትወዳትን ህፃን ልጃቸውን እሴተን ተሰናብታ ወደ ገዳም በመመለስ ሙሉ የምንኩስና ማዕረግ ትቀበላለች። በአጋጣሚ እሷ አገሬ እሄዳለሁ ብላ ቤተሰቡን ተሰናብታ በወጣችበት እለት የአቶ ውድነህ ብቸኛ ልጅ ከቤት ትሰወራለች። ይህም ይደነቁ ይዛት እንደጠፋች ያስጠረጥራትና በፖሊስ ክትትል ይደረግባታል።

በገዳሙ ህግ መሰረት እማሆይ ወለተወልድ ተብላ ስመ ክርስትና የተሰጣት ዘርትሁን ባላት መንፈሳዊ ብቃትና ጠንካራ አገልግሎት ተመርጣ በቅርቡ ባረፉት እመምኔት ምትክ የገዳሙ እመምኔት ትሆናለች። በታህሳስ 24 በዓድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በአለ ንግስ ላይ በመገኘት ማዕረገ ምንኩስናዋን ለማስባረክና እግረ መንገዷንም አባቷን፣ ጓደኞቿንና እንዲሁም ረጅም ጊዜ በቤት ሰራተኝነት ያገለገለችበትን የአቶ ውድነህን ቤተሰብ ለመጠየቅ እቅድ ይዛ ወደ አዲስ አበባ ትመጣለች።

ደብረ ሊባኖስ ደርሳ ስትመለስም አባቷን እና የንሰሀ አባታቸውን መምሬ ዘውዱን ካገኘች በኋላ ተሰናብታቸው ወደጓደኛዋ የሺሀረግ ቤት ስትመጣ ታጣታለች። እስክትመለስ ድረስ አቶ ውድነህ ቤት መሄዷን ለጎረቤት መልዕክት በመተው ወደዚያው ትሄዳለች እንደደረሰችም አቶ ውድነህ ጤንነቱ ታውኮ በማግኘቷ ታዝንና ደህንነቱን በመጠየቅ የድሮ ሰራተኛው ይድነቁ መሆኗን ትገልፅለታለች። አቶ ውድነህም ይደነቁ መሆኗን በለየ ጊዜ "ልጄን ሰርቀሽ ወስደሽ አሁን ደግሞ ልትሰልይን እራስሽን ለውጠሽ መጣሽ " በማለት ይዞ ሲደበድባት አንድ አይኗ ጉዳት ይደርስባትና ሆስፒታል ትገባለች፤ እንደተሻላትም በወንጀለኝነት ስለምትፈለግ ወደ እስር ቤት ትዛወራለች።

ተመልሳ እንደምትመጣ መልዕክት የተነገራት ጓደኛዋ የሺሀረግም ስታድርና በማግስቱም ስትቀርባት ወደ አቶ ውድነህ ቤት በመሄድ ስትጠይቅ ይደነቁ በአቶ ውድነህ ድብደባ ደርሶባት ሆስፒታል እንደገባች በዘበኛ ይነገራትና ወደዚያው ሄዳ ታገኛታለች። በእስር ቤት ቆይታዋም ብቸኛ ዘመድ በመሆን ምግብ በማመላስ ይደነቁን ስትረዳ ትቆያለች። ፖሊስ የደረሰበትን ፍንጭ በማጠናከርና እስከ ዝቋላ ገዳም ድረስ በመሄድ አስፈላጊውን ምርመራ ያከናውናል። የዋስ መብትም ይሰጣትና ከእስር ቤት ውጪ ሆና ጉዳዩን ትከታተል ዘንድ ለዋስትና ቋሚ ንብረት ያለው ሰው እንድታቀርብ ያዛታል። የሺሀረግ ስትመጣም ጉዳዩን በማስረዳት የአባቷን ንስሐ አባት መምሬ ዘውዱን እንድትጠራላት ቤታቸውን በምልክት በመንገር ትልካታለች። መምሬ ዘውዱም መልዕክቱ ሲነገራቸው ከአባቷ ከአቶ ስለሺ ጋር ነበሩና አብረው ወደ ጣቢያ ይመጣሉ። ከጣቢያው ሲደርሱም አባቷ ታሳሪዋ ልጃቸው መሆኗን በተለይም አንድ አይኗ መጥፋቱን ሲመለከቱ ራሳቸውን ስተው ይወድቁና ሆስፒታል ይገባሉ።

በተለያየ አትጣጫ ምርመራውን ሲያካሂድ የነበረው ፖሊስ የህፃኗ ገዳይ እና ሰዋሪ ይደነቁ ሳትሆን የህፃኗ እንጀራ እናት እና የአቶ ውድነህ ባለቤት ወ/ሮ ኤልሳቤጥ መሆኗን ይደርስበታል። እየተከታተላት ሳለም በድብቅ ከሀገር ልትወጣ ስትል ከአውሮፕላን ማረፊያ መልሶ በቁጥጥር ስር ያውላትና ልጅቷን እንዴት እንደገደለቻት እና ለምን እንደገደለቻት መርታ እንድታሳይ ያደርጋታል።

አቶ ስለሺ ሆስፒታል እንደገቡ ይህንኑ ጉዳይ ለቤተሰብ የሚነግር አንድ ፖሊስ ሀላፊነት ይሰጠውና ወደ አካባቢው ያመራል። ሲያጠያይቅም የቀበሌው ሊቀመንበር አቶ አለባቸውን ያገኘውና ጉዳዩን ያስረዳዋል። እሱም ከአመታት በፊት የእንጀራ እናቷን ገድላ የተሰወረች

እንዲሁም በቀይ ሽብር ውስጥ እጇ ያለበት ወንጀለኛ መሆኗን በመንገር እንዳትለቀቅ ያዘዋል። ወደ አቶ ስለሺ ቤት በመሄድም የባዩሽ ወንድም ለሆነውና ከአቶ ስለሺ ጋር ለሚኖረው ለበላይሁን የዘርትሁንን መያዝ የምስራችና የአቶ ስለሺን ታሞ ሆስፒታል መግባት ይነግረዋል።

ፖሊስ ዘርትሁን በልጅቷ ግድያ እጇ የሌለበት ነፃ መሆኗን በመንገር ከእስር ቤት ሊያስወጣት በዝግጅት ላይ እንዳለ ሌላ ወንጀል የሰራች መሆኗን ይደርስበትና እንደገና እስር ቤት እንድትቆይ ያደርጋታል። ሆስፒታል የተኙ አባቷን ለመጠየቅ በፖሊስ ታጅባ ከእስር ቤት የመጣችው ዘርትሁን አባቷን ሊያስታምም እዚያ ከነበረው የእንጀራ እናቷ ወንድም ከበላይሁን ጋር ይገናኛሉ። ገና ሲያያት እጅግ መጎሳቆሏ በተለይም አንድ አይኗ መጥፋቱ እንዲፀፀት ያደርገዋል። የእህቱ ገዳይ እሷ ሳትሆን እሱ እንደሆነ በመግለፅ እጁን ለፖሊስ ይሰጣል። በፖሊስ ለተደረገለት ምርመራም እህቱ ለዘርትሁን ያዘጋጀችውን መርዝ የተጨመረበት ብርዝ በስህተት በመጠጣት ለሞት መዳረጓን ይናገራል። ፖሊስም ይህንኑ እና ሌሎች መረጃዎችን በመያዝ ከዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል በጊዜው የተደረገለትን የፊሳ ምርመራ ውጤት አስመጥቶ በማየት ባዩሽ በጊዜው በጠጣችው መርዝ እና ሞንትላቷ ላይ በደረሰባት መፈንከት ለህልፈተ ህይወት መብቃቷን አረጋግጦ ዘርትሁን ከግድያው ነፃ መሆኗን አጣርቶ በነፃ ያሰናብታታል።

በግፍ ከታሰረችበት እስር በት በነፃ የተለቀቀችው በቤት ስሟ ዘርትሁን ፣ በምንኩስና ስሟ እማሆይ ወለተወልድ በመባል የምትታወቀው ይደነቁ የደረሰባትን ግፍ ከምንም ሳትቆጥር መምሬ ዘውዱንና የሺሀረግን አስከትላ ልቅሶ ለመድረስ ወደ አቶ ውድነህ ቤት ትሄዳለች። እሱም እንዳያት ለፈፀመባት ግፍ ይቅርታ እንድታደርግለትና የፈለገችውን ያህል ካሳ ለመስጠት ይማፀናታል። እሷም በእግዚአብሔር ስም ይቅር በማለት ለእሷ ካሳ ከሚሰጥ ይልቅ በምትኖርበት ገዳም የውሃ ችግር ስላለ ገንዘቡንና እውቀቱን በማስተባበር ውሃ እንዲያስገባላቸው ቃል ስታስገባው ታሪኩ ያልቃል።

3.1.2. የሴት ገፀባህሪያት አሳሳል በእመ ምኔት

በዚህ ክፍል ቀደም ብሎ እንደ ተገለጸው በእመ ምኔት ውስጥ ዋና ገፀባህሪዋና ሌሎች ሶስት ገፀባህርያት ይተነተናሉ።ትንታኔው ከወንድ ሁለት አቶ ስለሺ እና መምሬ ዘዱ ከሴት ደግሞ ሁለት ዘርትሁንና ግምብ ወግሽ የተባሉ ገፀባህሪያት ላይ ያተኩራል።

ዘርትሁን የእመ ምኔት ዋና ገፀባህሪ ናት። በልቦለዱ ውስጥ የዚህች ገፀባህሪ ካላዊ መልክ በተወሰነ ደረጃ ጎሊናዊ መልኳን ደግሞ በሰፊው ተስሎ (ነው) እናገኘዋለን። የዘርትሁን ውጫዊ መልክ በልቦለዱ ውስጥ ብዙም ተገልፆ አናገኘውም።

ዘርትሁን በልቦለዱ ውስጥ ባብዛኛ ጎሊናዊ መልኳ መልካም ሆኖ ተስሏል ።ዘርትሁን ትጉህ፣ አስተዋይ፣ ትሁት፣ ይቅር ባይ እና ዕናት ያላት ገፀባህሪ ሆና ተስላለች ። እነዚህ ባሕርያቷን ይበልጥ የምናየው ከቤቷ ከወጣች በኋላ ነው። ከእንጀራ እናቷ ጋር ተጣልታ ከቤቷ እስክትወጣ ድረስ በተለይ ከእንጀራ እናቷ ጋር ያላት ግንኙነት ጥሩ አልነበረም፤ ለእንጀራ እናቷ ወንድም፣ አቤቶቸው ውስጥ ሠራተኛ ለነበሩት እና በጡረታ ለሚገኙት አረጋውያን ትሑት አሳቢ ሆና የምናገኛት ዘርትሁን ከእንጀራ እናቷ ጋር ግን ዘወትር የምትጨቃጨቅ የምትጣላ ሆና ነው የተሳለችው።" *በስምንት ዓመታት የሚበላለጡት እንጀራ እናትና እንጀራ ልጅ የአቶ ስለሺ ማን ያዘዋልን ቤት የጦርነት ቀጣና በማድረግ በሽምቅና አንዳንዴም በፊት ለፊት ሲጋጩበት ሁለት ዓመታት አልፈዋል። / 2002፣1/"*

በሞቱት እናቷ ምትክ ሚስት ሆና ከገባችው እንጀራ እናቷ ጋር ዘወትር ስምምነት የላትም። የጥላ እና የጥላቻዋ መንስኤ ይታወቃል። ለእንጀራ እናቷ ወንድም መልካም ስታደርግለት ስታስተምረው፣ ስትመክረው የምናገኛት ዘርትሁን የእናቷን ቦታ የወሰደችባትን ሴት ግን በፍጹም አትወዳትም፤ ዘርትሁን ብቻ ሳትሆን የእንጀራ እናቷም ለእርሷ ያላት ጥላቻ ከፍተኛ ነው። ለዚህም ነው በአንድ ቤት ውስጥ እየኖሩ ምክንያት ፈልገው የሚጣሉት የሚሰዳደቡት።

ይህ የተቆጪነት፣ የተሳዳቢነት ባሕርይዋ በአንድ ወቅት ፍጹም ተቀይሮ እናገኘዋለን። ዘርትሁን ገዳም ካገባች በኋላ ይቅር ባይ፣ ትሑት ሆና ነው የምናገኛት። ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የነበራት ምኞት ተቀይሮ ገዳማዊ ሕይወትን በመምረጥ ፍጹም መንፈሳዊ ስትሆን ከዚህ ጋር የሚሄዱትን ባሕርያት ተላብሳ እናያታለን።

ምንም እንኳ ከጊዜያዊው ፈተና ለማምለጥ ወደ ገዳም ገብታ ብትሸሸግም በገዳሙ ውስጥ በነበራት ቆይታ በተመለከተችው ገዳማዊ ኑሮ ተማርካ ስትመነኩስ[1] ባሕርይዋ ተለውጦ ትሑት፣ ታዛዥ እና ይቅርባይ ሆና እናገኛታለን።

[1] መነኰሰ (መነኵሰት) በራሱ ላይ የተፀለየበትና የተባረከ ቆብ አደረገ ጫነ ሳይሞት በሰሌን ተገንዘ ፍታት ተፈታ ። ዓለም በቃኝ አለ መነነ ገዳም ገባ። ዐዲስ አማርኛ መዝገበ ቃላት ገጽ 793።

በትግሯ ወቅት ሸሽታ የተጠጋችበት የገዳም ኑሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሥርዓቱ እና ድርጊቱ እየማረካትና መንፈሷን እየገዛው በመሄዱ ሕይወቷን ከመንፈሳዊው ሕይወት ጋር ለማጣመር በአስተውሎት አሰባ አቅዳ ነበር /ፀሐይ 2002፣ 97/::

ወደ ገዳም የሄደችው ለመመንኮስ አይደለም፤ ይልቁንም "የእንጀራ እናቷ ገዳይ ናት" ተብላ ከመትፈለግበት ቀዬ ለመሸሽ ነበር:: ሆኖም እዚያ ባየችውና በሰማችው ነገር ተማርካ ፍጹም መንፈሳዊ ስትሆን እናያታለን:: በመንፈሳዊው ዓለም የጽድቅ መንገድ ነው ተብሎ የሚታሰበው የትሩፋት ሥራ ሁሉ በታማኝነቱና በቅንነት ስታገለግል ነው የምናገኛት:: በመንፈሳዊው ሕይወት ትልቅ ቦታ የሚሰጠውን ይቅርታ በተግባር ስትፈጽመው እናያታለን:: "ልጄን ደብቀሻል" በሚል ሰበብ ክፉኛ ደብዳቦ አንድ ዓይኗን በማጥፋት እስር ቤት እንድትገባ ያደረጋትን አቶ ውድነህን ይቅርታ እንድታደርግለት እግሯ ላይ ወድቆ በለመናት ጊዜ እንዲህ እያለች ታዕናናዋለች::

> "እንኳን በእርስዎ በአትዬ ኤልሳቤጥም የያዝኩት ቅያሜ እና ቂም የለም፤ ለበቀልም አልተሰናዳሁም:: በተፈጠረው ሰው ሠራሽ ተንኮል ተረብሸው ላደረጉት ድርጊት አይጨነቁ፤ የሆነው ሁሉ ማንነታችን ሊመዘንበት የተፈጠረ ሁኔታ ነው:: ስለዚህ አይሳቀቁ እባክዎን አይጨነቁ ጋሼ" አለችው:: በሚያዕናና ቃል / ፀሐይ 2002 ፣ 215/::

ዘርትሁን በደል ደርሶባት ዓይኗን ያህል ያሳጣትን ሰው እቤቱ ድረስ በመሄድ ከሐዘኑ ስታዕናናው ይቅርታ እንድታደርግለትም ሲጠይቃት እንኳን በእርሱ እና በሠራችው ተንኮል ለእስር የዳረገቻትን ባለቤቱን እንኳ ቂም እንዳልያዘችባቸው አበክራ ስትናገር እንሰማታለን:: በዚህም ውስጥ ከገዳም ቆይታዋ ያገኘቸው ፍሬ ይቅር ባይነት በውስጧ ገ•ልቶ እናያለን::

ዘትርሁን የዕናትም ተምሳሌት ናት:: በአጋጣሚ የተለወጠውን ሕይወቷን የመ•ጥኝ ብላ እስከ መጨረሻው ስትዘልቅ እናያለን፤ በምንኩስና ሕይወቷ ከዚህ ሕይወት ውስጥም መንፈሰ ጠንካራ ሁና ነው የምናገኛት፤ ባልሠራችው ሥራ ተወንጅላ እስር ቤት ብትገባም የእስር ቤት ቆይታዋን በፍቅር፤ በትሕትና እና በዕናት ነው ስትወጣው የምናያት:: ይህ ዕናት ለሌሎች የሚተርፍ ለሌሎች ትምህርት የሚሆን ዕናት ነው:: ይህንን ዕናቷንና ትህትናዋን ደራሲዋ በሚከተለው መልኩ ትገልፅልናለች።

ይደነቁ የመጣላትን ከማክፈልዋ ባሻገር በጥሩ አንደበትዋና በምታሳያቸው ፍቅርና ትሕትና ከጊዜ ወደ ጊዜ መወደድንና መከበርን አትርፋለች። ስታሠልስም በምታነበው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመረኮዘ መንፈሳዊ ታሪክ በመተረክና ትምህርት በመስጠት ተስፋ የቆረጠ ሕይወታቸውን ለመለወጥ ትጥራለች። ...በዚህም የተነሳ ፀብና ክርክር እንዲሁም ድብድብ ይበዛበት የነበረው ክፍል ሰላማዊ እንዲሆን በማድረጓ የጣቢያው ፖሊሶችም ተገርመዋል /ወሐይ 2002፣ 131/።

ዘርትሁን የደረሰባትን መከራ እና እንግልት ከምንም ሳትቆጥር የእስር ቤት ሕይወቷን መልካም ነገሮችን በማድረግ ለማሳለፍ ትጥራለች። ፅናቷን የተመለከቱ የእስር ቤት ሰዎች ሳይቀሩ በሥራዋ በንግግሯ በአጠቃላይ በምታደርጋቸው ነገሮች ተማርከው የጨለመ ተስፋቸውን ብሩህ በማድረግ ተስፋ ከመቁረጥ ተስፋ ወደ ማድረግ ይሸጋገራሉ። ሥርዓተ አልበኝነት የሰፈነበትን እስር ቤት ሰላማዊ ታደርገዋለች። በደረሰባት ነገር ስትማረር አናያትም። "ለምን ይህ ሁሉ ካለምንም ምክንያት ይደርስብኛል?" ተብላ በሌሎች ለሚነሳላት ጥያቄ የምትመልሰው መልስ ይህንኑ ፅናቷን የሚያሳይ ነው።

ዘርትሁን በተንቀሳቀሰችባቸው የሕይወት አጋጣሚዎች ትጉህ የምትመሰገን በመሆኗ ለምትሠራው ሥራ ምስጋናን እንጂ ነቀፌታ አይደርስባትም። ይህንን ትጉህነቷን በአቶ ውድነህ ቤት በቆየችባቸው ዓመታት እና በገዳሙ ውስጥ በነበራት የወጣኒነት ጊዜ እናያለን።

ዘርትሁን በእነ አቶ ውድነህ ቤት የምትወደድ ትጉህ ሠራተኛ ሆና ተስላለች፤ ዘመዶቿን ለማየት "እሄዳለሁ" ብላ ስታስፈቅድ እንኳ አቶ ውድነህና ባለቤቱ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ቢቻል አንዳትሄድ ካልሆነም ቶሎ እንድትመለስላቸው ይለምኗታል።

እንድትቀርላቸው ወይም ቶሎ እንድትመለስ ለምነዋት ቶሎ እንደማትመለስ ስትነግራቸው በቤት ውስጥ አብራቸው በነበረችበት ሰዓት ምን ዓይነት ሰው እንደነበረች ሲነግሯት ነው የምንሰማው። ይህ ትጋቷን በገዳም ቆይታዋም ተንፀባርቋል። ካለመሰልቸት በፍቅርና በትሕትና በምታገለግልበት ገዳም ውስጥ እመ ምኔት[2] ተብላ ሌሎችን መነኮሳት የመምራት ኃላፊነት ይሰጣታል።

[2] እመ ምኔት ፡የገዳም እናት የሴት ደብር አስተዳዳሪ፡ እማሆይ ፡ እመ ሆይ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት 1962 ገፅ 107።

እማሆይ ወለተ ወልድ የተመኘችውን ምንኩስና ካገኘች በኋላ ጊዜዋንና ጉልበቷን አውቀትዋንም ለገዳሙ ማኅበረሰብ ጠቀሜታ ለማዋል መጣጣር ቀጠለች። ... በገዳሙ አስተዳደርም ታምናባት በድንገተኛ ሀመም ባረፉት በእማሆይ ወለተ ጴጥሮስ ምትክ የእመ ምኔትነት ኃላፊነት ተሰጣት /ፀሐይ 2002 ፣ 98/።

ከወጣኒነቷ ጀምሮ ከትሕትና ጋር ገዳሙ በሚፈቅደው ሥርዓት ውኃ በመቅዳት፣ እንጨት በመልቀም፣ አረጋውያንን በመንከባከብ ከፍተኛ ፍቅርን ከማኅበረ መነኮሳቱ ስታገኝ እናያለን። ይህ ዝናና ፍቅር ለተሻለ ቦታ ለተሻለ ሥልጣን ለተሻለ ኃላፊነት እንድትታጭ ያደርጋታል። ወደ ገዳም በገባችበት በጥቂት ጊዜ ውስጥ ለከፍተኛ ኃላፊነት ያላጫት ትጉህ ሠራተኛ መሆኗ ነው። በአጠቃላይ ዘርትሁን በመጽሐፉ ውስጥ አርቆ አስተዋይ፣ ደግ፣ ሩኅሩኅ፣ ዕኑ እና ትጉህ ሆና ተስላለች።

ግምብ ወግሽ <u>በእመ ምኔት</u> ረጅም ልቦለድ ውስጥ የዘርትሁን ቤተሰቦች ጎረቤት በመሆን ለ 25 ዓመታት አብረው በፍቅር የኖሩ እና ከፍቅራቸውም የተነሳ ዘርትሁንን ክርስትና በማንሳት የክርስትና እናቷ የሆኑ ሴት ናቸው ።

<u>በእመ ምኔት</u> ረጅም ልቦለድ ውስጥ የዘርትሁንን ታሪክ ወደፊት እንዲራመድ በማድረግ ረገድ ትልቅ ቦታ ካላቸው ገፀባህርያት መካከል ግምብ ወግሽ አንዷ ናቸው። ግምብ ወግሽ ምን ዓይነት አካላዊ ገለፃ እንዳላቸው ብዙም አልተገለፀም። የምናውቀው የ10 ዓመት ሕፃን ሳሉ መዳራቸውን ነው።

በልቦለዱ ውስጥ "*ግምብ ወግሽ የዐሥር ዓመት ለጋ ለግላጋ ወጣት፣ ባልየው አዳነ የአሥራ ሰባት ዓመት ጐረምሳ ሲሆኑ በ37 ዓ.ም. ጥር ወር ላይ ተአምር በተባለ ድግስ ተደርጐ ጐጆ ወጡ።*"/ፀሐይ 2002 ፣ 10/ የሚል አረፍተነገር እናገኛለን።

በዚህ ዐረፍተ ነገር የአስር ዓመት ወጣት የሚለው በ10 ዓመት ወጣትነት ባይኖርም አዛውንቷ ግምብ ወግሽን ወደ ኋላ ሄደን ምን ዓይነት ሕፃን እንደነበሩ ለመገመት ያስችለናል። ይህ የተተረከው ግምብ ወግሽ ዛሬ በባልቴትነታቸው ለገጠማቸው ብቸኝነት በዚያ ዘመን ከተፈጸመው ድርጊት ጋር የተያያዘ ታሪክ ስላላቸው ነው።

ግምብ ወግሽ በልቦለዱ ተወልደው ያደጉበት ባህል ሰለባ ሆነው ተስለዋል። ባህሉ ባተረፈላቸው ጠባሳ ዛሬ ኑሮአቸውን በብቸኝነት እንዲገፉ ሆነዋል። ሴት ልጅን በሕፃንነቷ መዳር እንደትልቅ

ክብር በሚቆጠርበት ማኅበረሰብ ውስጥ የተወለዱት ግምብ ወግሽ ብቸኛ ሆነው ሕይወታቸውን ሙሉ ከሰው ተገለው እንዲኖሩ የማይሽር ጠባሳ ጥሎባቸው አልፏል።

> *የግምብ ወግሽ ለጋ ማንወን በወሊድ ችግር ተጐዳ። የተፈጠረው ሕፃንም ተቀጨ። የዕድሜንና የአካልን ዕድገት ያላገናዘበው ጋብቻ የግምብ ወግሽን ሕይወት ገና ከማለዳው አጨለመው። በአገር ባህል መድኃኒት፣ በመንፈሳዊ ጸሎትና ጥረት ሕመማቸውን ማስወገድ አልተቻለም። የተጐዳው አካላቸው በሥርዓት መወገድ የሚባውን ሽንት፣ የወር አበባ እና ዓይነ ምድር መቆጣጠር ተሳነው /ፀሐይ 2002፣ 11/።*

ከላይ በጥቅሱ እንደምናየው ግምብ ወግሽ ከባህሉ ማምለጥ አይችሉም። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ከአያቶቻቸው፡ ከአባቶቻቸው የወረሱት ወግና ባህል ነውና። ባህሉ ግን መጥፎ ጠባሳን ጥሎባቸው ነው ያለፈው ።በፊስቱላ መጠቃታቸው ብቻ ሳይሆን ሁለተኛ ልጅ የማይወልዱ፣ ባል የማያገቡ ብቸኛ ሴት ሆነው እንደኖሩ አድርጐአቸዋል። አገራቸውን ለቀው እንዲሰደዱም ምክንያት ሆኗቸዋል።

ከልጅነታቸው ጀምሮ ለህመም የዳረጋቸው ፊስቱላ ሰው ተጠግተው እንዳይኖሩ ፣ የዝቀተኝነት መንፈስ እንዲሰማቸው አድርጎአቸዋል። በአካልም በመንፈስም እድሜ ልካቸውን እየተሳቀቁ እንዲኖሩ መጥፎ ጠባሳውን ጥሎባቸው አልፎአል።

ግምብ ወግሽ ልጅ ባይኖራቸውም ዘርትሁንን እንደ ልጅ ተንከባክበው አሳድገዋታል። በአበልጅነት የታሰረው የረጅም ጊዜ ጉርብትናቸው የእናት ያህል እንዲንከባከቧት አድርጓቸዋል ።ካለልጅ በብቸኝነት ኑሮአቸውን የሚገፉት ግምብ ወግሽ የልጅ አምሮታቸውን በዘርትሁን በኩል ሲወጡ እናያቸዋለን። በክርስትና ልጃቸው በዘርትሁን ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ሴት ሆነው ተቀርፀዋል። እናቷ ከሞቱ በኋላ ቤት ውስጥ በነበረው ምስቅልቅል ዘወትር የምትበሳጨው ዘርትሁን የቤታቸው ምስጢረኛ ወዳጅ የሆኑት ግምብ ወግሽ መጽናኛዋ የዓይን ማረፊያዋ እና የእናቷ ምትክ ሆነውም ተስለዋል።"... *ከአባቷ ግቢ በታች ወደሚኖሩት ክርስትና አናትዋ ቤት በመሄድ በነፃነት መንፈስ ተጫውታ፣ በልታ፣ ጠጥታ በምክራቸው ተዕናንታ ትመለሳለች" /ፀሐይ 2002፣ 4/*።

ግምብ ወግሽ በእምነታቸው ጠንካራ ለሃይማኖታቸው የሚሞቱ ቃላቸውን የማያጥፉ ሆነው ተቀርጸዋል። ዘርትሁን ከእንጀራ እናቷ ጋር ተጣልታ ወደ እርሳቸው በመጣች ጊዜ ይደብቁአታል። መደበቅም ብቻ ሳይሆን ለማንም አሳልፈው እንደማይሰጧት ቁምር ቃል ይገቡላታል /ፀሐይ 2002፣ 13/።

ዘርትሁን በዕለቱ የተፈጠረውን ነገር ስትነግራቸው እውነት የሆነውን ለማጣራት ይሞክራሉ። በእምነታቸው፣ በሃይማኖታቸው ውስጥ ውሸት ኃጢአት መሆኑን የሚያውቁት ግምብ ወግሽ እውነቱን ብቻ እንድትነግራቸው ደጋግመው ይጠይቋታል። አሳልፈው እንደማይሰጧት ቃል ይገቡላታል፤ ይህንኑ የንስሐ አባታቸው መምህሬ ዘውዱ ሊጠይቁአቸው በመጡ ጊዜ ነግረዋቸዋል አሳልፈው እንደማይሰጧትም ድጋሚ ቃል ይገባሉ።

በዘርትሁን፣ በንስሐ አባታቸው በመምሬ ዘውዱም ፊት የገቡትን ቃል ይፈጽማሉ። ይህንን ቃላቸውን እንዲጠብቁ ያደረጋቸው ደግሞ ሃይማኖታቸው ነው። በዚህ ቃላቸውም እስከ ሞት ድረስ ይፀናሉ። የዘርትሁን ፈላጊዎች እሳቸው እንደሸሸጓት የጊዜው እያጣሩ ከማስፈራሪያ ጋር ቢነግሯቸውም ለገቡት ቃል ታማኝ ሲሆኑ ነው የምናየው። በዚህም ምክንያት ህይወታቸው ያልፋል። ግምብ ወግሽ የሃይማኖት ልጃቸውን አሳልፈው ላለመስጠት ሲሉ ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ሰጥተዋል። ለሰው ልጆች ራሱን አሳልፎ እንደሰጠው እንደ ክርስቶስ ለዘርትሁን ቤዛ ሲሆኑ እንመለከታለን። ይህንንም በንስኃ አባታቸው በመምሬ ዘውዱ በኩል እንሰማለን።

> *"ጉዳዩ ብዙ ነው አቶ ስለሺ፣ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ቤዛ አድርጐ በሰጣት ሰው አማካኝነት ከአዲስ አበባ ተሸኝታ ወደ ክፍለ ሀገር ተሸሽጋ ኖራለች።"*
>
> *"እንዴት ማነው ለልጇ መዳን ቤዛ የሆናት ሰው" አሉ አቶ ስለሺ ደንግጠው፡"*
>
> *"እኒያ የተቀደሱ ሰው፣ እኒያ እውነተኛዋ ሴት ግምብ ወግሽ ናቸዋ። እሷን አሸሽተው ያው አንድ ሰሞን ወሬው ሲናፈስ እንደሰሙት የዘርትሁን ልብስ በቤታቸው በመገኘቱ ታስረው ምሪ ፣ ተናጋሪ እየተባለ ተደብድበው በደረሰባቸው ስቃይ አልፈዋል። ነፍሳቸውን ይማርልንና" /ፀሐይ 2002፣ 9/።*

ግምብ ወግሽ በደረሰባቸው ድብደባና እንግልት ሁሉ ቃላቸውን በመጠበቅ አላየሁም በማለት ለዘርትሁን ያላቸውን ታማኝነትና ፍቅር በሞት ይደመደማል። ይህንንም በቅርባቸው የነበሩት የንሰሀ አባታቸው ምስክርነታቸውን ይሰጡላቸዋል።

በአጠቃላይ ግምብ ወግሽ በመጽሐፉ ውስጥ የጎላ ቀሩ አስተሳሰብ እና የባህል ሰለባ ሆነው ተስለዋል። ባህሉ በሕግንነታቸው አካላቸው ሳይፀና እንዲዳሩ በማድረጉ ለፊስቱላ እና ለመሃንነት ችግር አጋልጠአቸዋል። እንደ Chukukere (1995:2) አገላለፅ ብዙዎቹ የአፍሪካ ሴቶች በቤት ውስት ያላቸው የእናትነት ድርሻ የጎላ ነው። አንዲት ሴት በባሏ ቤት የሚኖራት ድርሻ የሚወሰነው ልጅ ስትወልድ ነው።ግምብ ወግሽ ጋርም የምናየው ይህንኑ የማህበረሰቡን አመለካከት ነው። ግምብ ወግሽ ሴትን ስትወልድ ብቻ የሚፈልጋት እና የሚንከባከባት ይህ ባህል ትዳራቸውን እንዲፈቱ ሌላም እንዳያገቡ ወስኖ በብቸኝነት ሕይወታቸውን እንዲገፉ አድርጉአቸዋል። ግምብ ወግሽ የብዙ ኢትዮጵያውያን የገጠር ሴቶች ወኪል ናቸው።

3.1.3.የወንድ ገፀ ባሕርያት ምስል በእመ ምኔት

እንደ ሴት ገፀባህርያቱ ሁሉ ወንድ ገፀ ባህርያቱን በልቦለዱ ውስጥ ካላቸው ሰፊ ቦታ እና ሚና አንፃር የተወሰዱ ናቸው። በልቦለዱ ውስጥ ሰፊውን ድርሻ ይዘው የምናገኛቸው አቶ ስለሺንና መምሬ ዘውዱን ነው።

አቶ ስለሺ በልቦለዱ ውስጥ የዋናዋ ገፀባህሪ የዘርትሁን አባት ሆነው ነው የተሳሉት። በአካባቢያቸው የታወቁ የተከበሩ እና ሀብታም ከሚባሉ ሰዎች ተርታ የሚመደቡ ናቸው።አቶ ስለሺ ከዘርትሁን በስተቀር ሌላ ልጅ ስለሌላቸው የህግ ሚሰታቸው እያሉ በድብቅ ቅምጥ ያላቸው ሰው ሆነው እናገኛቸዋለን።

አቶ ስለሺን በልቦለዱ ውስጥ አዲስ ባገቧት ሚስታቸውና በልጃቸው መሐከል የተነሳውን አምባጓሮ እና የከረረ ጥል ለማብረድ ሲያቅታቸው እንመለከታቸዋለን። የእርቁን ጉዳይ በራሳቸው መፍታት ሲያቅታቸው በዘመዶቻቸው በኩልም ሞክረው በሁለቱም መንገድ መፍትሄ ያጡለትን የወጣት ሚስታቸውንና የብቸኛ ልጃቸውን ጉዳይ እልባት መስጠት ያቃተው አባት ሆነው ነው በመጀመሪያው የመጽሐፉ ክፍል ላይ የምናገኛቸው።

በልጅ እና በሚስት መካከል ያለው የማይበርድ ቅራኔ ለማስጣል ልጃቸውን እንዳይቆጡ በቅምጥል ካደገች ብቸኛና የሙት ልጅ ናት ሚስታቸውን እንዳይቆጡ የአባት ያህል

የሚበልጧት እና እጅግ የሚወዷት ሁለመናቸውን የተቆጣጠረች መልከ መልካም ሴት ናት። አቶ ስለሺ በዚህ መሀከል ነው ሲዋልሉ የምናገኛቸው።

ተጨማሪ ልጅ በተለይ ወንድ ልጅ ፍለጋ የሚያደርጉት ድብቅ ጉዞ በጓላም ይፋ ሆኖ የሚያገኟት ሚስታቸው ሳቢያ ከልጃቸው ጋር የነበረው ግንኙነት ሲሻክር፣ በጦረቤቶቻቸው እና በዘመዶቻቸው ፊት ትዝብት ላይ ሲጥላቸው እናያለን።

> *አቶ ስለሺ ሁለቱንም ይወዱአቸዋል ፣ የፍቅራቸው ዓይነት ይለያይ እንጂ። ማናቸውንም ማጣት አይፈልጉም። በቤታቸው ውስጥ እየገነነ ወደ ጎረቤትና ታዛቢ የወጣው ጭቅጭቅና ፀብ ከትዝብት ላይ እንደጣላቸው ባዩ ቁጥር ግን ያማቸዋል /ፀሐይ 2002 ፡2/።*

የሕግ ሚስታቸው ከመሞታቸው በፊት ከባዩሽ ጋር በድብቅ የሚቀጣጠሉበት ምክንያት ወንድ ልጅ ፍለጋ ቢሆንም ባዩሽ ልጅ ስትወልድላቸው አናይም።

በሁሉም ነገር ተሸንፈው የተውት የቤተሰብ ጉዳይ ግን በሕይወታቸው ላይ የሐዘን ጥላ አጥልቶባቸው ነው የሚያልፈው። ሁለት የሚወዷቸውን ሰዎች ነው በአንድ ጊዜ የሚያጡት ፡ ሚስታቸውን በሞት ልጃቸውን ደግሞ በሕይወት ያጧቸዋል። ይህንኑ ለመምሬ ዘውዱ ሲነግሩአቸው እንሰማቸዋለን።

> *"የወደቀብኝ ፈተና ከምችለው በላይ ሆነብኝ እኮ መምሩ፣ የወለደ ይመዝነዋል ያለሁበትን መከራ ፣እርስዎስ ወልደው ያወቁታል አይደል የልጅን ነገር።አንዲቱ ቅንጣት ለጅ ደብዛዋ ጠፍቶ መኖር መሞትዋን የሚነግረኝ አጥቼ ነፍሴ እንደተንጠለጠለች አለሁ። የባዩሽም አሟሟት ያሳዝነኛል።ይጸጽተኛል። ለሷ ሞት መንስኤዋ እኔው ነኝ" /ፀሐይ 2002፡87/።*

አቶ ስለሺ በትዳራቸው ላይ የሚወሰልቱ ሰው ሆነው ነው የተሳሉት። ይህ ባሕርያቸው ከአንዱ ሁለቱ ስሕተትን እንዲፈጽሙ አድርጐአቸዋል። በሕግ ያገቧቸው የዘርትሁን እናት ከቤት ውስጥ ቢኖሩም በድብቅ ያስቀመጧት በጓለም በይፋ ያገቧት ቅምጥ ነበረቻቸው።

ሚስታቸው ታመው ፀበል በተኙበት ግዜም ከቤት ሠራተኛቸው ጋር በዝሙት ሲወድቁ እናያለን። ከውሽማቸው ከባዩሽ ጋር የነበራቸው ወዳጅነት ብሎም ወደ ጋብቻ ያደገው ግንኙነት

ወንድ ልጅ ፍለጋ ያደረጉት ቢያስመስልም ከቤት ሠራተኛ ጋር በዝሙት መውደቃቸው ይህንኑ ባሕሪያቸውን የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም ከቤት ሠራተኛቸው ጋር በዝሙት ከወደቁ በኋላ ዞር ብለው አያይዋትም። ነገሩን በጥርጣሬ የደረሱበት ባለቤታቸው ሠራተኛዋን ገርፈው ሲያባርሯትም ምንም ዓይነት እርምጃ አይወስዱም። ዘመን ካለፈ በኋላ መምሬ ዘውዱ ከእርሷ ልጅ እንዳላቸው ሲነግሯቸው /ፀሐይ 2002 ፣ 110/ እንኳ ስሟን ለማስታወስ ለተወሰነ ደቂቃ ግር ይላቸዋል።

እንደ ቀልድ ለሥጋዊ ፍላጐታቸው የወደቁት አቶ ስለሺ ልጅን የሚያህል ተወልዶ አድጐ ከ18 ዓመት በኋላ ጉዳዩን ከመጀመሪያው ጀምሮ ሲከታተሉት በነበሩት በልጃቸውና በንስሐ አባታቸው በመምሬ ዘውዱ አማካኝነት ሲነገራቸው እንኳ ሲከራከሩ ነው የምንሰማቸው ለግዜው ከሥጋዊ ፍላጐታቸው እርካታ ያለፈ ሌላ ሐሳብ አልነበራቸውምና ነው።

አቶ ስለሺ የራሳቸው ሃሳብ ብቻ እንዲሳካ የሚፈልጉ ራስ ወዳድ ሆነው ነው የተሳሉት። ልጅ ለመውለድ በተለይም ወንድ ልጅ ለማግኘት ያላቸው ከፍተኛ ፍላጐት በቅምጣቸው በኋላም ሚስት ሆና ቤታቸው በገባችው ባዩሽ ሞት ምክንያት አለመሳካቱ ተስፋ ቢያስቆርጣቸውም በልጃቸው በዘርትሁን በኩል ዘራቸው እንዲቀጥል ከፍተኛ ጉጉት ነበራቸው። ከእንጀራ እናቷ ግድያ ጋር በተያያዘ ከቤት ጠፍታ የነበረችው ልጃቸው በሕይወት ብቻ ቢያገኟት ደስ እንደሚላቸው ሲናገሩ የነበሩት ሰው ቆብ ደፍታ መንኩሳ ከፊታቸው የቆመችውን ልጃቸውን ሲያገኙ ግን በህይወት መገኘቷን ሳይሆን መመንኮሷን መቀበል ሲያቅታቸው እንመለከታለን። የዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያት እንደራሷ ሃሳብ ከምትመነኩስ እንደእርሳቸው ፍላጎት ባል አግብታ ልጅ ብትወልድ ዘር ብትተካላቸው ደስ ስለሚላቸው ነው። ለዚህም ነው ቆብ ደፍታ ከፊታቸው የቆመችውን ልጃቸውን የሚወቅሱት።

> *"የለም ዘርትሁኔ፣ በእርግጥ አድርገሽው ከሆነ እኔንም ገለሽኛል። ሙት ነኝ ማለት ነው። ለዘላለም ሞቴን እያረዳሽኝ ነው" አሏት ሐዘን በጐዳው ድምፅ።*
>
> *"የኔ መመንኮስ ያንተ መሞት ለምን ይሆናል አባዬ?" ሁኔታው ቢያሳዝናትም ገርሟት።*
>
> *"በቃ ተስፋዬ ከሰመ፣ ምኞቴ መከነ። የዘር ሀረጌ ደረቀ። ይህንን ሞት አላልሺውም? ምነው ልጅ ብንማክር ኖሮ፣" አሉና እማሆይን ተቀምጣበት ከነበረው ድንጋይ ላይ ተቀምጠው አንገታቸውን ወደ መሬት ደፉ /ፀሐይ 2002፣ 105/።*

ምኞታቸውና ሀሳባቸውን ልጃቸው ዘርትሁን እንድታሳካላቸው ይፈልጋሉ። እሳቸው ልጅ መውለድ ስላልቻሉ አንድ ልጃቸው ዘርትሁን ልጅ ወልዳ የዘር ሀረጋቸው ቀጥሎ ማየት ይፈልጋሉ።

እሳቸው በስውርም በግልጥም ሞክረው ያቃታቸውን ዘርን የመተካት (የማግኘት) ጉዳይ በልጃቸው ፍላጐት ላይ አዘው አስገድደው እንድትፈጽምላቸው ቢፈልጉም በዘርትሁን በኩል ያለው ተስፋ የጨለመ ሆኖ ያጉታል ለዚህም ነው የልጃቸው መመንኮስ "የፈሰሰ ውኃ አይታፈስ" ሆኖባቸው "ገለሸኛል" እያሉ በሐዘንና በቁጭት የሚናገሯት።

አቶ ስለሺ ቶሎ ተስፋ ቆርጠው እግዚአብሔርን የሚያማርሩ ፣እንባቸውን ወደ ውስጥ መዋጥ የማይችሉ ሆደ ባሻ ምንም የከፋ ነገር መቋቋም የማይችሉ እርብትብት ሆነው ተቀርፀዋል። ዘርትሁን በልጅ አጥፍተሻል ሰበብ ወህኒ ቤት መግባቷን እና መታሰሯን በሰሙ ግዜ ይህንኑ ሆደ ባሻነታቸውን ነው የምናየው። ገና ሳያይዋት መታሰሯን ብቻ በመስማታቸው ብርክ ሲይዛቸው፣ ሲያለቅሱ እናገኛቸዋለን። ከተራኪዋ አንደበት የምንሰማው ይህንኑ ሆደ ባሻነታቸውን ነው።

> *"አቶ ስለሺም ከግንባራቸው ላይ ቾፍፍ ያለውን ቀዝቃዛ ላብና እንባቸውን ከካፖርታቸው ሥር በለበሱት ነጠላ ጫፍ እየጠራረጉ ተነሥተው መንፈሳቸው ተሰብሮ አካላቸው አጐንብሶ ተከተሏቸው። ውስጣቸው ግን ብርክ ይዞቸው ነበር" /ፀሐይ 2002፣ 172/።*

ከላይ እንደምናየው ወንድ ልጅ አለው የሚባለውን ጥንካሬ በእርሳቸው ላይ አናይም አንድ ነገር በሰሙ ቁጥር እግዚአብሔርን ለማማረር የሚፈጥኑ ፣ መከራን ከመቋቋም ይልቅ ተሸንፈው ሲያለቅሱ የሚታዩ ሰው ናቸው። በአጠቃላይ አቶ ስለሺ ከጋብቻ ውጪ በድብቅ ከሌሎች ሴቶች ጋር በመሄድ በትዳራቸው ላይ የሚቀብጡ፣ ቶሎ ተስፋ የሚቆርጡ፣ ነገሮችን ጠንከር ብሎ መቀበል የማይችሉ ፣ እርብትብት ሰብዕና የተላበሱ ሆነው ነው በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉት።

<u>በእመ ምኔት</u> ረጅም ልቦለድ ውስጥ የምናገኛቸው ሁለተኛው ወንድ ገፀባህሪ መምሬ ዘውዱ ናቸው። መምሬ ዘውዱ ከአቶ ስለሺ ጋር ለረጅም ዘመን አብረው የኖሩ ጎረቤታሞች በዚያ ላይ የንሰሐ አባትም[3] ናቸው። መምሬ ዘውዱን በልቦለዱ ውስጥ በዚህ መልክ ነው የምንተዋወቃቸው።

[3] ንሰሐ አባት ፣ ንሰሐን የሚነግሩትየንስሐ አባት ዳግመኛም የነፍስ አባት ይባላል።ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣1959፣ ገፅ 878

መምሬ ዘውዱን ከታሪኩ መነሻ እስከ ፍጻሜው ድረስ ባሉት አቢይ እና ንኡሳን ታሪኮች ውስጥ ሁሉም ቦታ ሁሉም ሰው ሕይወት ውስጥ እናገኛቸዋለን። ከአቶ ስለሺ ቤት እስከ አቶ ውድነህ ቤት፣ ከግምብ ወግሽ ቤት እስከ ዝቋላ ገዳም ሁሉም ቦታ እናገኛቸዋለን። መምሬ ዘውዱ ካህን ናቸው የእግዚአብሔር አገልጋይ በሁሉም ቦታ የመገኘታቸው ምስጢር በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የሚቆሙ፣ በመንፈሳዊው ዓለም የእግዚአብሔር ምትክ ሆነው የሚያገለግሉ ካህን ሆነው ተቀርፀዋል።

እንደተሰጣቸው ማዕረገ ክህነት የተሰጣቸው ማዕረጉ ከሚጠበቀው አገልግሎት አንፃር በአቶ ስለሺ፣ በዘርትሁን፣ በግምብ ወግሽ፣ በውድነህ እና በቤተሰቦቹ ሕይወት ውስጥ ብቅ ጥልቅ እያሉ ያፅናናሉ ይመክራሉ።

በማኅበረሰቡ ዘንድ ይልቁንም በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ የተከበሩ የተወደዱ ሆነው ነው የተሳሉት በእምነቱ የተጣለባቸውን ሥጋዊና መንፈሳዊ ግዴታ በቅንነት የሚፈጽሙ፡ በአካባቢው እና በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ መወደድን ያተረፉ ጥሩ ሰብዕና ያላቸው ናቸው። ይህንንም በልቦለዱ ውስጥ በሚከተለው መልኩ ተገልፆ እናገኛለን።

> *መምሬ ዘውዱ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና በምግባራቸው በአካባቢው የተመሰገኑ ስለሆኑ ክፍተኛ ክበሬታና ታዋቂነትን ያገኙ ናቸው። አንዳንዴ ፍርድ ቤት ሊሄድ የሚገባውን ነገር እሳቸው ዘንድ በመውሰድ በውሳኔአቸውና በምክራቸው በማመን ጉዳያቸውን በአጭሩ የሚያጠናቅቁ ሰዎችም እንዳሉ ይነገራል/ዐሐይ 2002፣ 86/።*

መምሬ ዘውዱ በአካባቢያቸው ሰዎች ዘንድ ያላቸው ፍቅርና መክበር በማንኛውም ጉዳይ ለሰዎች የሚደርሱ እና መፍትሄን የሚሰጡ መልካም ሰው መሆናቸውን በአካባቢው ላይ የሚነገርላቸው ሰው ናቸው። ከሰዎች ጋር ባላቸው ግኑኝነት ውስጥ ነው ይህንን የማስታረቅ፣ የመምከር ፣ ሰዎችን የማፅናናት ባህሪያቸውን የምንሰማው።

ዘመድ አልባ ሆነው ኑሮአቸውን በአንዲት ደሳሳ ጎጆ ውስጥ የሚገፉትን ግምብ ወግሽን ተመላልሰው ጠይቀዋል፣ መክረዋል፣ አስታመዋል፣ በሞቱም ጊዜ የአካባቢውን ሰው በማስተባበር አስከሬናቸው በክብር እንዳያርፍ አድርገዋል። የግምብ ወግሽን መሞት አክስታቸው ለሆኑት እና በዝቋላ ገዳም ለሚኖሩት ለእማሆይ ወለተ ሐዋርያት ለመንገር እና

ሃዘናቸውን አብረው ለመካፈል ዝቋላ ገዳም ድረስ ሄደዋል። በተለይ ግምብ ወግሽ ዘርትሁንን ደብቀዋል ተብለው በፖሊስ እና በቀበሌው ሊቀመንበር ዓይን ውስጥ በገቡ ሰዓት የሚመጣባቸውን ፈተና በትዕግስት እንዲቋቋሙት "እንዲያ ነው ክርስቲያን በርቱ እኔም በጸሎት አልለይዎትም በችግርም ሁሉ ከጐንም አቆማለሁ። ለጠርጣሪም ፍንጭ ላለመስጠት ታዲያ ቆፍጠን ይበሉ። አይሸማቀቁ። በጸሎት ይትጉ።" /ፀሐይ 2002፣ 34/ እያሉ ሲመክሩ እንመለከታለን።

አቶ ስለሺን ከደረሰባቸው ሐዘን እንዲወጡ የሚያፅናኑ በደረሰባቸው መከራ ሁሉ ከጐናቸው የሚቆሙ እንደ አባት የሚመክሩ የሚያፅናኑ እንደ መምህር የሚያስተምሩ ሆነው ነው በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉት።

ዘርትሁን ወደ ዝቋላ ገዳም ከገባች በኋላ እንደ አባት ተመላልሰው ይጠይቋታል፣ በአሠሪዋ ድብደባ ደርሶባት እስር ቤት በገባች ጊዜ ዋስ በመሆን የደረሱላት እሳቸው ናቸው። ከአባቷ ጋር እንድትገናኝ መንገዶችን ያመቻቹ እሳቸው ናቸው። በእያንዳንዱ ድርጊታቸው በእምነቱ የተጣለባቸውን የክህነት ኃላፊነት ሲወጡ ይታያሉ። ልጇ ጠፍታለች ብለው ተስፋ የቆረጡትን አቶ ስለሺን የሚገናኙበትን ሰዓትና መንገድ ካመቻቹ በኋላ የመኖሯን ዜና ሲነግሯቸው አያምኗቸውም በእግዚአብሔር እና በድንግል ማርያም ስም እየማሉ ልጃቸው በህይወት መኖሯን እግዜር በፈቀደ ጊዜ ሊያገኙአት መሆኑን ለአቶ ስለሺ ያበስሯቸዋል። እስር ቤት በነበረች ጊዜም ዋስ በመሆን ያስፈቷታል።

በአጠቃላይ በልቦለዱ ውስጥ ከእያንዳንዱ ሰው ጋር ባላቸው ግንኙነት ሰውን ከችግሩ ለማውጣት የሚጣደፉ ረዳት፣ በመከራቸው ለሰዎች የሚደርሱ አፅናኝ፣ በሄዱበት ቦታ ሰዎችን የሚያስተምሩ እውነተኛ ካህን ሆነው ነው የተሳሉት። "ካህኑ ለህዝቡ የአምላክን ህግና ፈቃድ የማስተማር ሃላፊነት አለበት" ትንቢተ ሚልኪያስ (2፣7) የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እሳቸው በተግባር ሲያውሉት እናያቸዋለን።

3.2. የደራሲዋ ፋይል

በዚህ ክፍል ወደ ገፀባህሪያቱ ትንተና ከመግባቱ በፊት የልቦለዱን ታሪክ ባጭሩ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

3.2.1.የልቦለዱ ታሪክ

<u>የደራሲዋ ፋይል</u> ታሪክ የልቦለዱ ዋና ገፀ ባህሪ በሆነችው በጽዮን፣ በአቶ ታምሩ ፣ በወይዘሮ የተመኝ ፣ በመምህር ግርማ፣ በብዙነሽ እና ሌሎች በታሪኩ ሂደት በየመሃሉ በሚመጡ ንዑሳን ገፀ ባህሪያት ዙሪያ የሚሽከረከር ነው።

በኪነ ጥበብ ዛር የተለከፉት አቶ ታምሩ በዋናነት ከያዙት የመምህርነት ስራ ጎን ለጎን አንድ ረጅም ልቦለድ በመድረስ ለኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ቢሰጡም በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉት ገፀ ባህሪያት የዘመኑን ባለስልጣናት ድርጊት የሚያሳዩ በመሆኑ የማተሚያ ቤቱን ሳንሱር ሳያልፍ ይቀርና ብዙ ዘመን የለፉበት ደግሞም ተስፋ ያደረጉት ልቦለድ ሳይታተምላቸው ይቀራል። ይህም ተስፋ ያስቆርጣቸውና በብስጭት ወደ መጠጥ ፊታቸውን ያዞራሉ። አልፎ ተርፎም በሰፈሩም የታወቁ ጠጪ ይሆኑና "ጣጪው ታምሩ" የሚል ቅፅል ስም ይወጣላቸዋል።

ስሜታቸውን በቅጡ ባልተረዱት ባለቤታቸው ስድብ ምክንያት ብዙ ጊዜ የሚበሳጩት አቶ ታምሩ ገና በጨቅላ እድሜዋ ወደ ስነ ጽሑፍ ካዘነበለችው ልጃቸው ጽዮን ጋር የበለጠ እየተግባቡ ፣ እየተቀራረቡ ሌላውን ቤተሰብ በማግለል ነፍሳቸውን አንድ ስላደረገው ስነ ጽሑፍ በመወያየት እሷም ወደፊት ህይወቷን እንዴት መምራት እንዳለባት በመምከር ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ።

ስነ ጸሑፍን የመጥኝ ብላ ከአባቷ ጋር ተጣብቃ የምትውለው ፅዮን በእናቷ ዘንድ ተቀባይነት አልነበራትም ከሷ ይልቅ ወንዱ ልጃቸው ጋሻው የቤቱን ስራ ሲያግዛቸው በተቃራኒው ሴት ሆና እንደ ሴትነቷ የቤቱን ስራ አለማገዟ እናቷ ከሷም ከባለቤታቸውም ጋር ከፍተኛ ቅሬታ ውስጥ ይገባሉ።

በተፀናወታቸው የድርሰት ፍቅር የተነሳ በገንዘብም በፍቅርም ቤታቸውን ችላ እያሉ የመጡት አቶ ታምሩ ከሁሉም ሳይሆኑ መቅረታቸው ባስከተለባቸው ጠጪነት የተነሳ ተጎድተው ኖረው በዚሁ ሳቢያ ለህልፈተ ህይወት ይዳረጋሉ።

ሲሞቱ የጀመረችውን የስነ ጽሑፍ ስራ ከእውነተኛው ህይወቷ ጋር እያገናዘበች እንድትኖር ከአባቷ አደራን የተቀበለችው ልጃቸው ቃላቸውንና ሃሳባቸውን ለመፈፀም ዘወትር ትፈጨረጨራለች። አቶ ታምሩ ገና ጀማሪ መምህር ሆነው ጎንደር ውስጥ ሲኖሩ ወላጅ አልባ ሆኖ ያገኙትንና ተቀይረው አዲስ አበባ እስኪመጡ ድረስ አየረዱ ያስተምሩት

የነበረው ግርማ ከብዙ ዘመን በኋላ የዩኒቨርስቲ መምህር ሆኖ አዲስ አበባ ሲመጣ ከአቶ ታምሩ ጋር ይገናኙና ቤተኛቸው ይሆናል።

ብዙ ጊዜ ቤታቸው ሲመላለስ በማየት ግርማን የወደደችው የፅዮን ጓደኛ እና ጎረቤት ብዙነሽ ግርማ ለፅዮን ያለውን ስሜት ስለተረዳች እና ቅናትም ስለያዛት ፅዮንን ከሌላ ወንድ ጋር በማገናኘት እና እርኩኛ እንዲኖራት በማድረግ ግርማ ፅዮንን እንዲጠላ እና ከእርሷ ጋር ያለውን ግኑኝነት እንዲያጠናክር ልዩ ልዩ ተንኮል ትፈጽማለች። የ 12 ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውጤት ይወጣና ፅዮን አልፋ ዩኒቨርስቲ ስትገባ ብዙነሽ ግን ውጤት ሳታገኝ ቀርታ እቤት ትውላለች።

ብዙነሽ በግዜው የነበራት አማራጭም ስራ ፈልጎ መግባት ስለነበረ በጓደኛዋ ሶስና አማካኝነት ከተለያዩ ባለስልጣናት ጋር በመተዋወቅ በነሱ ትከሻ ተንጠላጥላ የምትገባበትን መንገድ ታመቻቻለች። በዩኒቨርስቲ ቆይታዋ አብዛኛዋን ግዜዋን በስነ ጽሑፍ ስራ ላይ ታሳልፍ የነበረችው ፅዮን ደግሞ ውጤቷ ይቀንስና ከዩኒቨርስቲ አቋርጣ ወደቤቷ ትመለሳለች። ብዙነሽም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም እና በስራ ያስገቡሻል ሰበብ በጓደኛዋ በሶስና በኩል ከአንድ ባለስልጣን ቤት እንድትሄድ ታደርጋታለች። እዚያም ቤት እንደደረሰች ስራ አንደሚያስገቧት በተነገራት ባለስልጣን ልትደፈር ስትል አምልጣ ትወጣለች።

እቤት በመቀመጧ ምክንያት ያዝኑ የነበሩት እናቷ ከግርማ ጋር አምሽታ ወደ ቤት በመጣችበት በአንዱ ቀን የመረረ ጥል ይጣሉና ከቤት ወጥታ ማንንም ሳታማክር ሰው ቤት ሰራተኝነት ትቀጠራለች። እዚያም እንዳለች የአባቷን ቃል ለመፈፀም የምታደርገው መፍጨርጨር አልሳካ ይላታል። ከስራው ብዛት የተነሳ የድርሰት ስራዋን ማከናወን ስላልቻለች ከዚያ ቤት ትወጣና ከሊል የተባለ ወንደላጤ ቤት ትገባለች።

የብዙ መጻሕፍት መኖር፣ የአሰሪዋ ለስነ ጽሑፍ ያለው ዝንባሌ እና የድርሰት ስራዋን የምታከናውንበት ምቹ ግዜ ማግኘት ቤቱን እንድትወደው ያደርጋታል ። በሌላ በኩል በተወዳደረችበት መስሪያ ቤት አንደኛ ወጥታ ሳለ በተደረገባት አድልኦ የተነሳ ሳትቀጠር የቀረችው እና በብስጭት ከቤት እንደወጣች ሳትመለስ በቀረችው እህቱ ምክንያት ዘወትር ያዝን የነበረው አሰሪዋ ከሊል ከእለታት ባንዱ ቀን ያለ ወትሮው ሰክሮ እና አምሽቶ በመምጣት ለሌላ ነገር ፈልጓት ሲጠጋት እና እሷም እንዳይጠጋት ስትገፋው ይወድቅና ይፈነክታል በዚያም ምክንያት በወንጀለኝነት ትያዝና እስር ቤት ትገባለች።

ከቤት ጠፍታ በነበረበት ጊዜ ባስመዘገበው ስልክ ቁጥር አማካይነት የተጠራው ግርማ ዋስ በመሆን ከእስር ቤት ያስፈታታል። ጀምረውት የነበረው የፍቅር ህይወትም በትዳር እንዲታሰር ይጠይቃታል እሷ ግን የጀመረችውን የድርሰት ስራ ጨርሳ ነፃ ስትሆን እንደምታገባው ትገልፅለትና ወደ እናቷ ቤት ትመለሳለች። ቤቷ ስትደርስም ወንድሟ ሞቶ እናቷን ብቻቸውን ታገኛቸዋለች።

ለብዙ ጊዜ ተለይታት የቆየችውን ጓኛዋን ብዙነሽን በስልክ ፈልጋ ስታገኛት በተንጣለለ ዘመናዊ ቤት የምትኖረው ጓኛዋ ብዙነሽ ከድሮው ፍፁም የተለየች ሆና ታገኛታለች።ምንም እንኩዋን የፈለገችውን ነገር ሁሉ ብታገኝም በተለያየ ጊዜ ከተለያዩ ወንዶች ጋር ግኑኝነት በመፈፀሟ ሳቢያ ለበሽታ በመዳረጓ ሁሉን ነገር ትታ ወደ ቤተሰቦቿ ትመለሳለች።

መስከረም ሲጠባ ያቋረጠችውን የዩኒቨርስቲ ትምህርቷን የቀጠለችው ፅዮን በዚያው ዓመት የድርሰት ስራዋን ጨርሳ በዩኒቨስቲው የስነጽሑፍ ክበብ፣ በለጋሽ ደርጅቶች እና በግርማ አማካይነት ለህትመት ይበቃላታል። የምረቃው ስነ ስርአት ሲያልቅም ለእርሷ እና ለግርማ የገዛችውን የጋብቻ ቀለበት ጣቱ ላይ ስታጠልቅለት ታሪኩ ያበቃል።

3.2.2. የሴት ገፀባህርያት ምስል በየደራሲዋ ፋይል

በየዝና ወርቁ <u>የደራሲዋ ፋይል</u> ልቦለድ ታሪክ ውስጥ ሰፊ ቦታ ያላቸው አራት ገፀባህሪያት ከሴት ሁለት ጽዮንና ብዙነሽ ከወንድ ሁለት አቶ ታምሩ እና ግርማ ለትንታኔ ተመርጠዋል።

ፅዮን <u>በደራሲዋ ፋይል</u> ረጅም ልቦለድ ውስጥ ዋና ገፀባህርይ ሆና ነው የተሳለችው። ጽዮን የስነ ጽሑፍ ሰው የሆኑት አባቷን ለማገዝ ደፋ ቀና ትላለች። ራሷም የሥነ ጽሑፍ ፍቅር ስላላት አብዛኛውን ጊዜዋን ከአባቷ ጋር ነው የምታሳልፈው። ይህ የስነ ጽሑፍ ዝንባሌዋ እና ብዙውን ግዜ ከአባቷ ስር እያለች ማሳለፏ ከእናቷ ጋር ያጣላታል።

ጽዮን በልጅነት እድሜዋ የአባቷን ሀሳብና ፍላጎት ለማሟላት እና እሳቸውን ለማስደሰት ብዙ ውጣ ውረድ ታያለች። የድርሰት ስራቸውን እንዲያከናውኑ አንድ ክፍል ቤታቸውን በሳጠራ ከፍላ ለድርሰት ስራቸው ታመቻችላቸዋለች። ይህም አባቷን በማስደሰቱ ዘወትር በእሳቸውና በባለቤታቸው መሀከል የሚነሳው አለመግባባት ይበርዳል። በቤተሰቡ መሀከል ሰላምን ለማስፈን ዘወትር ስትጥር ነው የምናያት።

ጽዮን አባቷ ሲሞቱ ሲሉ በሕይወቷ እንድትተገብረው በአደራ መልክ ያዘዟትን ትዕዛዝ በተለይ ከጥቂት ቀናት በፊት "የማወርስሽ ሀብቴ ይህ ነው" ብለው ከሰጧት ፖስታ ውስጥ በውስጡ የተጻፈውን የአደራ ቃል እያነበበች ስታለቅስ እናያታለን። መሞታቸው አሰቅቋትም "ምነው ፈጣሪዬ፣ ምናለ ያን ሁሉ ልመናዬን ብትሰማኝና አባቴን ብታቆየው ኖሮ ሥራ ይዤ አንድ ዓመት እንኳ ልንከባከበው ብዬ ነበር የለመንኩህ" /ዮዝና 2002፣6 / እያለች ፈጣሪዋን ስትማፀን እንሰማታለን።

አባቷ ለስነ ጽሑፍ ያላቸው ዝንባሌ እና ብዙ ጊዜ የለፉበት ድርሰታቸው ያለመታተሙ ጉዳይ በልጅነት አእምሮዋ ተቀርጾባታል። አትሟ በፈቀደው ሁሉ የሚፈልጉትን የድርሰት ሥራ እንዲቀጥሉበት ስታመቻቸላቸው ኖራለች። ሆኖም ያሰቡት ሳይሳካ ያለፉት አባቷን በቁጭት ስታነሳቸው ትታያለች።

ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባ የፈተና ውጤት አምጥታ ዩኒቨርሲቲ ብትገባም አባቷ ጀምረውት ያቋረጡትን የድርሰት ሥራ ቀጥላበት ጥሩ ነገር ሰርታ የሙት አባቷን መንፈስ የምታስደስትበትን መንገድ ለማግኘት ትጣጣራለች። በዩቨርሲቲ ቆይታዋም ከትምህርቱ ይልቅ የድርሰት ሥራዋን የምታከናውንበት ጊዜ ይበልጣል በዚህም ምክንያት በትምህርቷ እየደከመች ስትሄድ የተመለከተቻት ጓደኛዋ ማርታ ጉዳዩ ስላሳሰባት ትምህርቷ እንደሚበልጥባት ትምክራታለች።

ጽዮን የምትጣጣረው ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የድርሰት ሥራዋን ከግብ ለማድረስ ነው። ምክንያቱ ደግሞ አባቷ የነገሯት የአደራ ቃል በመሆኑ ነው። ሆኖም መሰናክሉ እጅግ ይበዛባታል። ገና አባቷ ሳይሞቱ አብዛኛውን ግዜ የሚያነቡላትን ድርሰት በማዳመጥና ድርሰቶችን በማንበብ ከአባቷ ጋር ስታሳልፍ የማይወዱት እናቷ እንደ ሴት ልጅ ሥራ ስለማታግዛቸው ይናደዱባታል እናም ዘወትርም የስድብ ናዳ ስለሚያወርዱባት በመሀከላቸው ያለው ክፍተት እየሰፋ ሄዶ የማይግባቡበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ።

> *እሱ እንኳን ላግዝሽ ሲል እቧ... እያሉ ይብከነከናሉ። እሱ ከአባቱ ጋር ቁጭ በሎ ቢያጠናና ቢጽፍ እቧ ደግሞ አብራቸው የቤት ሰራ ሰትሰራ ብታመሽ ነበር ምርጫቸው። ግን እንደሚፈልጉት አልሆነም /ዮዝና 2002፣11/።*

በእናቷ እምነት ሴት ልጅ ቤት ውስጥ ስራ ማገዝ ነው ያለባት ፅዮን ግን እናቷ ለሴት ልጅ ይገባታል ብለው የወሰኑላትን ሳይሆን ለወንዱ ልጃቸው ለጋሻው የሚመኙትን የወንድ ስራ የሚሉትን የፅሁፍ ስራ ነው የምትሰራው። ፅዮን እናቷ በሚፈልጉት መንገድ ስትጓዝ እናያትም ራሷ በመረጠችው ጎዳና ነው ስትሄድ የምናያት። ይህ ከልጅነቷ ጀምሮ ያላትን ጥንካሬ ነው የሚያሳየን። ምንም ባልተማሩት እናቷ እና በተማሩት አባቷ መሀከል ስለእርሷ ያለው አመለካከት ፈፅሞ የማይገናኙ ሁለት ቀጥታ መስመሮች ናቸው።

ፅዮን በተለይ አባቷ ከሞቱ መጓላ ቃላቸውን ለማክበርና ያዘዟትን ለመፈፀም ዘወትር ትጥራለች። ይህ ጥረቷ ግን በዩኒቨርስቲ ትምህርቷ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሮባታል። በትምህርት እየቀነሰች እንደሄደች ቢታወቃትም የተነገራትንና ለአባቷ የገባችውን ቃል ለመፈፀም ስትተጋ ነው የምናያት። በአባቷ ጉዳይ ማንም ሰው ጣልቃ ገብቶ ሀሳቧን እንዲያስቀይራት አትፈልግም። አቋም ብላ የያዘችውን ነገር በፍፁም መለወጥ የማትፈልግ በራሷ የምትተማመን ሴት ሆና ነው በልቦለዱ ውስጥ የተቀረፀችው። በፅሁፍ ስራዋ ምክንያት ውጤቷ ቀንሶ ስለነበር ከዩኒቨርስቲ እንዳትባረር በወንድ ጓደኛዋ በግርማ አማካኝነት ማርክ እንዲለመንላት በጓደኛዋ በማርታ በኩል ስትጠየቅ በፍፁም እንደማታደርገውና በሰው ትከሻ ተንጠልጥላ ማለፍ እንደማትፈልግ መናገሯ የሚያሳየን በራሷ የምትተማመን ሴት መሆኗንና እና ያላትን ፅኑ አቋም ነው። ይህ በእርሷና በጓደኛዋ በማርታ የሚደረገው ንግግር ይህንኑ ነው የሚያስገነዝበን ።

ማርታ ግራ ተጋብታ ስታያት ቆየችና ፦

"እሺ ፤ አስተማሪዎችን እንዲያነጋግርልሽ ነገርሽው?"

አልነገርኩትም አለች የበለጠ ኮስተር ብላ።

ቆይ ፅዮኔ እኔኮ ያንቺ ነገር ብዙም አይገባኝም። ግርማ መምህራኑን እንዲያነጋግርልሽ ማድረግ ብትወድቂ ሊያጋጥምሽ ከሚችለው ችግር ይብሳል?"አለች ማርታ በተሰላቸ ድምፀት።

"ማርቲ፤ ይህንን ነገር በተደጋጋሚ ተነጋግረንበታል። መግባባት አልቻልንም አይደል።ተይኝ ሴትነትን ለመወጣጫ እንደመሰላል መጠቀም ለራስ ክብር መንሳት ነው። በተደጋጋሚ እየነገርኩሽ እንዲህ ትይኛለሽ። ይሂስ በምን ይለያል" /ዮዝና 2002፡119/።

በራሷ ድክመት የመጣባትን ፈተና ሁሉ በራሷ ለመወጣት ስትሞክር ነው የምናያት በእርግጥ በግርማ በኩል ማርኩን አግኝታ ትምህርቷን መቀጠል ትችል ነበር ነገር ግን በሰው ላይ ተንጠላጥሎ ማለፉን ክፉኛ ስትቃወም ነው የምንሰማት ይህ በራሷ ላይ ያላትን ፅኑ እምነት በራስ መተማመን ያስገነዝበናል።

በትምህርት ውጤቷ ዝቅ በማለቱ የተነሳ ከዩኒቨርሲቲ ተባራ ወደ እናቷ ቤት ትመለሳለች። ከዩኒቨርሲቲ ወጥታ እቤት በተቀመጠችበት ሰሞን ጓደኛዋ ብዙነሽ ከወንዶች ጋር አላስፈላጊ ግንኙነት እንድትመሠርትና በዚያም ሳቢያ ሥራ እንዲያስገቧት ከባለሥልጣን ጋር ስታገናኛት በዚያ መንገድ የሚመጣውን ስራ አሻፈረኝ ብላ ስትተው ነው የምናያት። ብዙነሽ ከባለስልጣናቱ ጋር መልካም ግኑኝነት መስርታ የምትፈልገውን ስራ እንድትገባ በተደጋጋሚ ብትጨቀጭቃትም እንደማታደርገው ነው የምትነግራት በዚህን ጊዜ ብዙነሽ *"ፈጣው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ካልሆነ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሀል"* /የዝና 2002 ፡151/ እያለች ትተርትባታለች።

በማህበራዊ ህይወቷ ከሰዎች ጋር ያላት ግኑኝነት ውስጥ መልካም እና ቀና ሴት ሆና ነው የተሳለችው ከግርማ በፊት በብዙነሽ አስተዋዋቂነት እጮኛዋ የሆነው መንግሻን ከልቧ ስትወደው ስታምነው እናያታለን ሌላ ሴት ማግባቱን በጆሮዋ እስክምትሰማ ድረስ /ፀሐይ 2002 ፡50/ በእምነት ስትጠብቀው ነው የምናያት።

በጓደኛዋ ብዙነሽ በኩል በተደጋጋሚ ተንኮል ሲፈፀምባት እስከመጨረሻው በፍቅር እና በቅንነት ትቀበላታለች።፡

ከእናቷ ጋር ተጣልታ ከቤት ስትወጣ የምትጠጋበት የእጮኛዋ የግርማ ቤት ቢኖርም ሰው ቤት ተቀጥራ ራሷን ለማስተዳደር ትጥራለች ግርማ ቤት ስትገባ አናያትም። ድርሰቷን ለማሳተም ባላት ፅኑ አቋም ብዙ መከራዎችን ትጋፈጣለች። ሰው ቤት ስትቀጠር ይዛው የምትሄደው ይህንኑ የድርሰት ሥራዋን ነው። የአባቷን የአደራ ቃል ለመጠበቅ።

በሰው ቤት እያለች ሰው ገድለሻል በሚል ሰበብ ተጠርጥራ ወህኒ ቤት ትወርዳለች። ከእስር ቤት ወጥታ ወደ እናቷ ቤት ስትሄድ ግርማ እቤቱ ገብታ እንድትኖር ሲጠይቃት ፈቃደኛ አትሆንም። ቤቱ ነው የምገባው ብላ ወደ እናቷ ቤት ትሄዳለች። ሁሉን ነገር ከአባቷ ሕይወት ጋር ታያይዘዋለች። አባቷ ባንድ ግዜ ትዳር፣ ሥራና ድርሰት ጀምረው ሳይሳካላቸው በመቅረቱ በብስጭት ጠጭ ሆነው እንደሞቱ ይታሰባታል። ግርማ የጋብቻ ጥያቄ ሲያነሳባት የድርሰት

ስራዋን ሳትጨርስ ትዳር ውስጥ መግባት እንደማትፈልግ "በውስጤ የመስከን ስሜት አስኪሰማኝ። በእግሮቼ መቆም መቻሌን አስካረጋግጥ" አለች ከላይ ከላይ እየቃተተች /የዝና 2002 ፡240/። በማለት ቁርጡን ትነግረዋለች። በዚህ እምነቷም ወንታ የድርሰት ስራዋን ከፍፃሜ አድርሳ መጨረሻ ላይ ለግርማ የቃል ኪዳን ቀለበት ስታስርለት እናያታለን።

ባጠቃላይ ፅዮን ችግርን መቋቋም የምትችል ጠንካራ፣ ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ እስከመጨረሻው የምትታገል በባሕርይዋ ከሰዎች ጋር ተግባብታ መኖር የምትችል ነገሮችን በቀና የምትመለከት ለቃሏና ለዓላማዋ የምትተጋ ጽኑ ሴት ሆና ነው የተሳለችው።

<u>በየደራሲዋ ፋይል</u> ረጅም ልቦለድ ውስጥ ለትንታኔ የተመረጠችው ሁለተኛዋ ሴት ብዙነሽ ናት። ብዙነሽ በልቦለዱ ውስጥ ብዙም አካላዊ ገለፃዋን አናየውም። የጽዮን ጐረቤት በትምህርት ቤት ህይወትም እኩል የክፍል ደረጃ አብረው የነበሩ ፣ የፅዮን የልብ ጓደኛ ሆና ነው የተሳለችው።

ብዙነሽ የፅዮንን እጮኛ ግርማን ትወደዋለች እሱ ግን አስቦት አያውቅም በተቃራኒው ጽዮንን ስለሚወዳት ብቻ በመቅናት ብዙ መጥፎ ነገሮችን ስትሰራባት እናያለን። በፅዮን በጣም ትቀናባታለች። በሕይወቷም ጣልቃ እየገባች ብዙ ጊዜ የከፋ ነገር እንዲደርስባት ስትጥር ነው የምናያት። ግርማን ስለምትወደው ብቻ የራሷ አድርጋ ለማስቀረት በማሰብ ምንም የማታውቀውን ጽዮንን ከመንገሻ ጋር ጓደኝነት እንድትመሠርት የምታደርገው /የዝና 2002 ፡ 35/። መንገሻ ለፅዮን እንደማይሆናት እያወቀች የራሷን ጥቅም ለማስቀደም ስትል ብቻ ነው። የሚያገባት እጮኛ እንዳለችው እያወቀች ከግርማ ዓይን ሥር ዞር ለማድረግ የምታደርገው ተንኮል ጽዮንን በእጅጉ ሲጐዳት እናያለን። በዚህም የብዙነሽን ቀናተኛነት፣ ራስ ወዳድነት ነው የምናየው።

ብዙነሽ ራሷን ለርካሽ ነገር ያስገዛች ደካማ ሴት ተደርጋ ተስላለች። ከጽዮን ጋር አንድ ክፍል ሆነው እኩል የ12ኛ ክፍልን ፈተና ቢፈተኑም ውጤት ሳይመጣለት ቀርታ ቤቷ ትቀመጣለች። ከጓደኛዋ ከሶስና ጋር በመሆንም በሥራ ፍለጋ ሰበብ ከተለያዩ ባለሥልጣናት ጋር ስትቀጠር ትታያለች። የራሷ አልበቃ ብሏት በትምህርት ማቋረጥ ሰበብ እቤት የተቀመጠችውን ጽዮንንም ሥራ የምታገኝበት መንገድ እንደሆነ እና በተቻላት መጠን ከሰዎች ጋር መግባባት እንዳለባት እየመከረች እና እያባበለች ወደ አዘቅት ውስጥ ልትጥላት ስትሞክር እናያታለን።

በዚሁ መጥፎ ባሕርይዋ ምክንያትም ከቤሰቦቿ ጋር በመጣላት ከጓደኛዋ ከሶስና ቤት ጠቅልላ የገባችው ብዙነሽ ከብዙ ወንዶች ጋር ወጣ ወጣ ማለት ብዙ ገንዘብ የምታገኝበትን መንገድ ለራሷ ቀይሳ በዚያው መንገድ የምትንዝ ልጅ ሆና ተስላለች።

> *ታዲያ ብዙዎች ባለትዳሮች ይሁኑ እንጂ በልተውና ጠጥተው ሰውታቸው ሲሞቅ መዳራት ሲያምራቸው በግልጽ የታወቀ አሳዳሪ የሌላትን ብዙነሽን ሲያሽኮረምሙ ያመሻሉ አሷም ፍላጐታቸውን እየፈጸመች ገንዘብ ማግኘት ጀምራለች /ዮዝና 2002፣ 209/።*

ከላይ ካለው ሀሳብ የምንረዳው ብዙነሽ ገንዘብ ለማግኘት ብቻ በምታደርገው ጥረት ውስጥ ራሷን በማዋረድ እና ርካሽ ሴት በመሆን ለጊዜያዊ ደስታ ብቻ ከሚፈልጓት የተለያዩ ወንዶች ጋር ስትቀበጥ ነው የምናያት። ብዙነሽ በጊዜያዊና በብልጭልጭ ነገር የምትደለል ሰነፍ ሴት ተደርጋ ተስላለች በልቦለዱ ውስጥ።

ሕይወቷ የተመሳቀለ፣ አርቃ የማታይ ፣ ነገን የማታስብ ሴት ነች ብዙነሽ። አለማስተዋሏ ደግሞ ብዙ ጎዳና አያስኬዳትም በአጭሩ ስትቀር ነው የምናያት። የምትፈልገውን ያህል ገንዘብ ብታገኝም በስተመጨረሻ በሽተኛ ትሆናለች። ጽዮን ከብዙ ጊዜ በኋላ አድራሻዋን አፈላልጋ ባገኘቻት ጊዜ መንፈሷ ደክሞ አካሏ ዝሎ ፊቷ ገርጥቶ ነበር። ህይወቷ እንደጠዋት ጤዛ አይነት ነው ብዙ ስትንዝ አናያትም። በመጥፎ ባህሪዋ ምክንያት ጥላ የወጣችው ቤት የማታ የማታ ስትመለስ ነው የምናያት ።

ባጠቃላይ ብዙነሽ ቀናተኛ ፣ራስ ወዳድ፣ ከተለያዩ ወንዶች ጋር ለገንዘብ ስትል የምትቀበጥ ደካማ ሴት ናት ። ሰዎች ላይ ክፉ ከማድረስ የማትመለስ አደገኛ ሴት ሆና ተቀርፃለች።

3.2.3. የወንድ ገፀባህርያት ምስል በየደራሲዋ ፋይል

አቶ ታምሩ በየደራዋ ፋይል ውስጥ የዋና ገፀባህሪዋ ፅዮን አባት ሆነው ነው የምናገኛቸው። አቶ ታምሩ መምህር ናቸው ከዚህ ሞያቸው በተጨማሪ ጥሩ ደራሲም ናቸው። ከልጃቸው ከፅዮን ጋር በብዙ ነገር ይግባባሉ በጣምም ይወዷታል።

አቶ ታምሩ አካላዊ መልካቸው ምን እንደሚመስል በደንብ የተገለፀ ነገር የለም። የተማሩ በባህሪያቸው ጠጪ በቤታቸው ውስጥ ብዙ ጊዜ ከሚስታቸው ጋር የሚጣሉ ነጭናጫ ሆነው ተቀርፀዋል።

በልቦለዱ ውስጥ ምንም ነገር ያልተመቻቸው ኑሮአቸው እና አሳቸው ማዶ ለማዶ የሚተያዩ ሲያስቡት እና ሲያልሙት የኖሩት ነገር በእውን ያልተሳካላቸው በዚያም ምክንያት የሚበሳጩ ጠጪ እና መጠጥ ባስከተለባቸው ጉዳት ምክንያት ለሞት የተዳረጉ ገፀባህርይ ሆነው ተስለዋል።

ደራሲ የመሆን ህልም አላቸው፤ ነገር ግን ህልማቸው ሲጨናገፍባቸው ነው የምናየው ብቸኛ የቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆናቸው ኑሮ ይከብዳቸዋል በዚህም ምክንያት እቀጥላለሁ ብለው እቅድ ያወጡለትን ትምህርት ሳይማሩ ነው የሚቀሩት። የስነ ጽሑፉም ጉዳይ ባጭር ሲቀር ነው የምናየው። እንኳንስ መጻፍ ማንበብ በማይችሉበት ደረጃ ላይ የሚደርሱት የጽዮን አባት ያለ ባህሪያቸው ጠጪ ሆነው ነው የምናገኛቸው።

> *አቶ ታምሩ የኔ የሚሉት ወገን ሰላልነበራቸው አባወራና የሁለት ልጆች አባት በመሆናቸው ቢያስደስታቸውም ትምህርታቸውን እንደገና ለመቀጠል ግን ቀላል ሆኖ አላገኙትም። በዚያ ላይ ባለቤታቸው ስሜታቸውን ተረድተው ሁኔታውን ሊያመቻቹላቸው በማይሞክሩበት አንዲት ክፍል ቤት ውስጥ መጻፍም ሆነ ማንበብ የሚቻል አልነበረም በዚህ ምክንያት የአሁኑ ኑሯቸው ከዱሮ ምኞታቸው ጋር እንዳልሰመረ ሲሰማቸው እያደር በስጨትጨት ማለት ጀመሩ። ቤታቸውንም እየጠሉትና ከመጠጥ ጋር እየተወዳጁ መሄድ ቀጠሉ /ዮዝና ፣ 25 /።*

ከጥቅሱ እንደምንረዳው አቶ ታምሩ ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩት እርሳቸው በሚያገኙት ደመወዝ ብቻ ነው። ደመወዛቸው ከቤት ቀለብ ተርፎ ተስፋ አድርገው የነበረውን ትምህርት እንኳ እንዳይቀጥሉ ሆነዋል። በዚህም ላይ ውስጣቸው ያለው የስነ ጽሑፍ ዝንባሌ ልውጣ አልውጣ እያለ ሲታገላቸው ቁጭ ብለው የሚጽፉበት ቦታ የላቸውም። ቤታቸው አንድ ክፍል በመሆኗ ብዙም ለጽሑፍ ሥራ የምትመች አይደለችም። ከዚህም በተጨማሪ ብዙም ያልተማሩት ባለቤታቸው ስሜታቸውን ተረድተው የሚፈልጉትን ነገር ሲያደርጉላቸው አይታይም። ይህ ሁሉ ተደራረቦ ደህናው ሰው ባሕርያቸው ተቀይሮ ጠጪ ሲሆኑ እናያቸዋለን። በደንብ የሚግባቡትና የሚያወሩትም ከጽዮን ጋር በመሆኑ ብዙ ጊዜያቸውን ከሷ ጋር በማሳለፍ ቤተሰቡንም ችላ ማለት ይጀምራሉ።

አቶ ታምሩ ስለ እውነት ማውራት እውነትን መጻፍ ደስ ይላቸዋል ለዚህም ነው ልጃቸው ጽዮን ከራሷ ስሜት ይልቅ እውነትን እንድታስቀድም ሲመክሯት የምንሰማው የልባቸውን እውነት ወይም የገሃዱን ዓለም ነፀብራቅ በድርሰታቸው አካተው ቢጽፉም በማሳተሚያ ድርጅት ተቀባይነትን ያጣሉ ያ ግን በሕይወታቸው ላይ በመወሰን ተስፋ እንዲቆርጡ እና የበለጠ ስካራም እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። አንድ ቀን ይህንን የድርሰት ሥራቸውን ያቃጥላሉ። ክብራት አስመጥተው በወረቀቱ ላይ በመለኮስ ሲያነዱት እንዳያቃጠሉት ዕዮን ስትሰምናቸው እንዲህ ይላታል።

> *"የኔንም ያንቺንም ጠላት ነው የገደልኩት አበቃ!" አሏት። የሻከረው የድምፃቸው ቅላፄ አስደንግጧት ቀና ብላ አይቻቸው ዓይኖቻቸው የተቆጣ እብድ ዓይኖች ይመስላሉ። እጆቻቸው ይንቀጠቀጣሉ። ፀጉራቸው ቆሟል የምታደርገውን አጥታ አንገታቸው ላይ ተጠምጥማ አለቀሰች /የዝና 2002፣ 17/።*

አቶ ታምሩ በቶሎ ተስፋ የሚቆርጡ ገፀባህሪ ናቸው ፣ ሌላ መንገድ ወይም አማራጭ አይታያቸውም። ለዚህም ነው ብዙ ዘመን የለፉበትን ድርሰታቸውን ማተሚያ ቤት ስላልተቀበላቸው ብቻ በአንዴ እሳት የሚለኩሱበት። የልጃቸው የዕዮን ያክል እንኳ ወኔ የላቸውም። ባህሪያቸው ወዲያው ወደ ጠጪነት ተቀይሮ በሰፈሩ "ጣጤው ታምሩ" የሚል ቅፅል ስም እስኪወጣላቸው ድረስ ስካራም ይሆናሉ።። በባህሪያቸው ትዕግስት የሌላቸው ተደርገው ነው የተቀረፁት።

ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በተለይ ከባለቤታቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ጥሩ አልነበረም ምንም የትምህርት እውቀት የሌላቸውን ባለቤታቸውን አይረዷቸውም ባለመማራቸው "አንቺ ደደብ" /የዝና 2002፣ 16/። እያሉ ሲሰድቧቸው እንሰማለን። በዚያም የተነሳ በየቀኑ ለጭቅጭቅ የተጋለጡ ሰው ነበሩ። የተማሩ ሰው ቢሆኑም እንደ አዋቂነታቸው ሲንቀሳቀሱ ግን አናያቸውም ቤተሰባቸውን እንኳን ባግባቡ መምራት ያቃታቸው ህይወትን አቻችለው ለመኖር የሚከብዳቸው ደካማ መልክ ተሰጥቶአቸው ነው የተሳሉት።

በአጠቃላይ አቶ ታምሩ ብሩህ ሐሳብ የነበራቸው የድርሰት ሰው ቢሆኑም ለመማር እና እራሳቸውን የተሻለ ቦታ ላይ ለማስቀመጥ ቢጥሩም እንቅፋታቸው በዝቶ በረጅሙ የጀመሩት ጉዞ በአጭሩ ሲጠናቀቅ እናያለን። ለዚህ ደግሞ የራሳቸው ባሕርይ በተለይ በቶሎ ተስፋ መቁረጣቸው ሕይወትን ለመጋፈጥ ጠንካራ አለመሆናቸውን ነው የሚያሳየን። እሳቸው

ሊጋፈጡት ያልደፈሩትን ህይወት ግን ትንሿ ልጃቸው ፅዮን ተቀብላቸው ከፍጻሜ እንድታደርስላቸው ነው የሚፈልጉት።

> *"እኔን መስለሽ እንደወጣሽ ገና ልጅ ሳለሽ አይቻለሁና፣ ለስነ ጽሑፍ ያለሽን ተሰጥኦና ፍቅርም አውቀዋለሁና የሚሰማሽን የከንቱነትና የባዕድነት ስሜት ይቀንሰዋል። ያደረብሽን የስነ ጽሑፍ ፍቅር ግን ከእውነተኛው ኑሮሽ ጋር አያገናዘብሽ ያዣው አለበለዚያ ሕይወትሽ ይጐሳቆላል። ልብ በይ የኔ ልጅ! ይኼንን የምመክርሽን ለራሴ ሕይወት ማድረግ አልቻልኩም።"* /ዮዝና 2002፣ 6/ ይሏታል።

እሳቸው ተስፋ ቆርጠው ከመንገድ ላይ ቆመዋል ቀጣዩን መንገድ ግን እሷ እንድትጨርስላቸው አጥብቀው ሲለምኗት እንሰማለን። በሚወዱት ግን ታግለው ሊያሸንፉት ያልቻሉትን የስነ ጽሑፍ ፍቅር በሷ ውስጥ አብቦ ሊያዩት ሁሉ ይመኛሉ። የተሸነፈ አካላቸው ባጭሩ መቀጨቱ ቢታወቅም እሷ ውስጥ ያለው የስነ ጽሑፍ ፍቅር ግን እንደሚያብብ ተስፋ ያደርጋሉ።

በየዝና ወርቁ <u>የደራሲዋ ፋይል</u> ውስጥ የምናገኘው ሌላው ገፀባህሪ **ግርማ** ነው። ግርማን ከልጅነት እድሜው ጀምሮ ነው በፅዮን አባት በአቶ ታምሩ በኩል የምንተዋወቀው። አቶ ታምሩ ወላጅ አልባ የነበረውን ግርማን በልጅነቱ እየረዱ አስተምረውታል በትምህርቱ በርትቶ የዩኒቨርሲቲ መምህር የሚሆነው ግርማ የፅዮን የወንድ ጓደኛዋም ነው በልቦለዱ ውስጥ።

ግርማን በመጽሐፉ የመጀመሪያ ገጾች ውስጥ የምንተዋወቀው በአካላዊ መልኩ ነው። አራት ኪሎ ከዳግማዊ ምኒሊክ ት/ቤት ፊት ለፊት ያገኛቸውን የቀድሞ መምህሩን አቶ ታምሩን ሲጠራ እንዲህ ተገልጿል

> *"ጋሼ! ጋሼ!" እያለ ሲጠራቸው ዞረው እያለ ሲጠራቸው ዞረው አዩ። ጥቁር መልክ መልካም፣ ውኃ ሰማያዊ ጅንስ ጃኬትና ሱሪ የለበሰ ረዘም ባለ ቁመናው ከሳቸው በለጥ ያለ ሰው፣ ወተት የመሰሉ ጥርሶቹን በፈገግታ አስቀድሞ እየቀረባቸው ነበር* /ዮዝና 2002፣ 21/።

ግርማን በገልህ የምናየው በአቶ ታምሩ ቤተሰብ ውስጥ ነው። ዛሬ ላይ የዩኒቨርስቲ መምህር ሆኖ የምናየው ግርማ ወላጅ አልባ ሆኖ በአቶ ታምሩ እና በስራ ባልደረቦቻቸው እርዳታ ነው ትምህርቱን ተምሮ ለቁም ነገር የሚበቃው። ማንም የሚከታተለው እና የሚረዳው አንድም ወላጅ እና ዘመድ ሳይኖረው በራሱ ጥረት ትልቅ ደረጃ ይደርሳል።

ግርማ ተምሮ ትልቅ ደረጃ የደረሰ ጠንካራ እና ለችግር ያልተንበረከከ ሰው ነው። ጉንደር ከምትገኝ ገጠር ቀበሌ ተነሥቶ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ ጽሑፍ መምህር ሆኖ ነው ከአቶ ታምሩ ጋር የሚገናኙት። እራሱን በደንብ እስኪገልጥላቸው ድረስ ማንነቱን አልለዩም ያው ካስተማራቸው ተማሪዎች አንዱ ይሆናል በማለት ነበር እጃቸውን ለሰላምታ የዘረጉት። የት እንደሚተዋወቁ ከስመ ጋር ሲነግራቸው ግን ያስታውሱታል። በተገናኙበት አጋጣሚ ሲተቃቀፉ ግዙፉን ግርማን በደንብ ማቀፍ አልቻሉም እላቸው በሰውነት ከእርሱ አንሰው ነበርና።

> *"ግርማ ነኝ፤ አዘዘ" ሲላቸው ግርታቸው ወዲያውኑ ተገፈፈና አስታወሱት። ግርማ በአካል ተለወጠባቸው እንጂ የሚረሱት ልጅ አልነበረም እና በደስታ ሊያቅፉት እጃቸውን ዘረጉ። ግን እሱ ገዝፎ እሳቸው ቀጭጨው ነበርና ጭንቅላታቸው አንገቱ ሥር ተወሸቀ። በተራው አቀፋቸውና ተሳስመው ተሳሳቁ /ዮዝና 2002፣ 21/።*

በሁለቱ መተቃቀፍ ውስጥ የግርማ መግዘፍና የአቶ ታምሩ መቀጨጭ ትዕምርት ነው። ግርማን እዚህ ደረጃ እንዲደርስ በቁሳቁስና በምክር እየረዱ ያስተማሩት አቶ ታምሩ በብዙ ነገር ተጐሳቁለው በመንፈስም በሥጋም ደክመው ሰውነታቸው ጫጭቶ ትምህርታቸውን እንኳ ሳያሻሽሉ በአሉበት ምንም ሳይለወጡ እንዲያውም ከሚያውቃቸው በአካል አንሰው ነው የሚያገኛቸው። ምንም ያልነበረውና በእርሳቸው እርዳታ የተማረው ግርማ በመንፈሳዊም በሥጋም ጐልምሶ የከፍተኛ ተቋም መምህር ሆኖ ነው የሚገናኙት።

ግርማ መጽሐፋቸውን ለማሳተም የመጀመሪያውን ረቂቅ ሲያሳዩት በደስታ በታይፕ በማስመታት ለጎትመት የተዘጋጀ ሲያደርግላቸው እናያለን። እላቸው ከሞቱ በኋላም ቤተሰቡን ተመላልሶ ሲጠይቅ በገንዘብም በምክርም ሲረዳቸው ነው የምናየው። ይልቁንም ጽዮንን የሚወዳት እጮኛዋ ቢሆንም በትምህርቷ እና በድርሰት ሥራዋ እንድትበረታ ሲመክራት እና ሲያግዛት እናየዋለን /ዮዝና 2002፣ 12/።

በተለይ በፅዮን ህይወት ውስጥ ከመጀመሪያው ከተገናኙበት ሰዓት ጀምሮ እስከመጨረሻው የቃል ኪዳን ቀለበት እስከሚያስሩበት ጊዜ ድረስ በሃሳብ በምክር እና በገንዘብ ደግፏታል። በግድያ ወንጀል ተጠርጥራ በታሰረች ጊዜም ዋስ በመሆን ከእስር ቤት ያስፈታታል።

ግርማ መልካምና ከማንኛውም ሰው ጋር በቀላሉ የሚግባባ ባህሪ ያለው ተደርጎ ተስሏል ይህ መልካም ባህሪውም በተለይ ከሴቶች ጋር ባለው ግንኙነት ሀሳባቸው ተለውጦ እንዲያፈቅሩት

ያደርጋቸዋል። ይህ ከሰዎች ጋር በነፃ መንፈስ የሚያደርገው ግንኙነት የፅዮን ጓደኛ ብዙነሽ እንድታፈቅረው አድርጓታል /ዮዝና 2002፣ 32/።

ከፅዮን ጋር ባሳለፋቸው ጊዜያት ብዙ ጊዜ በመሃከላቸው አለመግባባት ተፈጥሮ በተደጋጋሚ ጥላው ስትሄድ በትዕግስት ሲይዛት እናያለን አኩርፋ ከቤቱ ስትቀር ያለችበት ድረስ ሄዶ ይፈልጋታል በተደጋጋሚ በድላው፣ አስቀይማው፣ በተደጋጋሚ ይቅርታ ስትጠይቀው፣ በተደጋጋሚ ይቅርታ አድረጎላት እንደወትሮው አብሯት መኖር ይጀምራል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ትዕግስቱን ነው የምናየው።

ባጠቃላይ ግርማ በልቦለዱ ውስጥ ሌሎችን የሚረዳ ትዕግስተኛ በቀላሉ ከማንኛውም ሰው ጋር የሚግባባ ነገሮችን ዝግ ብሎ በሰከነ መንፈስ ማየት የሚወድ ጠንካራ ዓላማ ያለው ሰው ተደርጎ ነው የተሳለው።

3.3. የገቦ ፍሬ

3.3.1.የልቦለዱ ታሪክ

በዚህ ክፍል በቀደሙት ሁለት ምዕራፎች ላይ እንደተደረገው ሁሉ ወደ ገፀባህሪያቱ አሳሳል ትንታኔ ከመግባቴ በፊት የልቦለዱን ታሪክ በአጭሩ አቀርባለሁ

በዋና ገፀ ባህሪዋ አማካይነት በአንደኛ መደብ "እኔ" እያለ የሚተርከው የገቦ ፍሬ ረጅም ልቦለድ ታሪኩ የሚጀምረው ዋና ገፀ ባህሪዋ ነፃነት ፍርድ ቤት ችሎት ፊት ቆማ ነው። በምልሰት ብዙ አመት ወደ ኋላ ተጉዛ ችሎት ፊት ያቆማትን ታሪክ ትተርክልናለች።

ጎንደር ውስጥ ክምር ድንጋይ ከተማ አቅራቢያ ከምትገኝ የገጠር ቀበሌ ለቤተሰቧ የመጨረሻ ልጅ ሆና የተወለደችው ነፃነት ቤተሰቦቿ በእንክብካቤ እና በፍቅር አሳድገዋታል። ደግሶ ማብላት በሚወዱት አባቷ ቤት ውስጥ ካሉት አምስት ልጆች ሶስት ሴት እና ሁለት ወንዶች መሀከል ማግባት በነበረባት እድሜ ሳታገባ እስከ አስራ አንድ ዓመት የቆየችው ነፃነት ብቻ ነበረች ሴቶች 5 ዓመት ሳይሞላቸው ወንዶቹ ደግሞ አስራ ስምንት ሳይደፍኑ ነበር ያገቡት።

በወቅቱ የቀበሌ ሊቀመንበር የነበሩት አባቷ በአካባቢው በነበሩ መምህራን ጉትጎታ ነፃነትን የትምህርት ብርሃን እንድታይ ወደ ትምህርት ቤት ቢልኳትም የቀበሌው ሊቀመንበር ስለሆኑ እና እንደ ማሳያ ልጃቸውን በማስተማር አርአያ መሆን ስለሚጠበቅባቸው በሰው ፊት ደስተኛ ይምሰሉ እንጂ በውስጣቸው ግን ፍጹም ደስተኛ አልነበሩም።

አባቷ እግሯ ላይ በደረሰባት እክል እንደ አካባቢው ባህል ወግ ጠያቂ ባል ሳታገኝ እድሜዋ ያለፈባት የአስራ አንድ ዓመት ልጃቸውን ነፃነትን ከቤት ወጥታ ለሰው ባትታይ በእርሷ ምክንያት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚደርስባቸውን ሀሜት እና ሽሙጥ ማምለጥ ይችሉ ነበር ነገር ግን የነፃነት የትምህርት ፍቅርና ጉብዝና የመምህራኑ ክትትል ሀሳባቸውን እንዳያሳኩ ሳያመቻቸው ይቀራል።

ይህንኑ እክል እንዳልነበር ቆጥራ ትምህርቷን በብሩህ ስሜት ስትከታተል የነበረችው ነፃነት የክፍሏ ተማሪ በነበረችው እና ከሷ ላቅ በምትለው ቸኮለች ስድብ የአካሏ ጎዶሎነት ገዝፎ ይታያትና ለምን እንደዚያ እንደሆነች እናቷን ትጠይቅና በህፃንነቷ በተኛችበት ክብት ተረከዟን ረግጧት ጉዳት እንደደረሰባት ይነግሯታል።

በተለይ ግን አንድ ቀን ትምህርት ቤት ውስጥ ለነበረው የሩጫ ውድድር ተመርጣ ቁምጣ ለብሳ መሮጧን የሰሙት አባቷ ከውድድሩ በኋላ ወደ ቤት ስትመለስ የሰደቧት ስድብ እና የተቆጧት ቁጣ በህይወት ዘመኗ ሁሉ ራሷን እንደ ጎዶሎና እንደ ዝቅተኛ ብቻ አድርጋ እንድታስብና እንድትገምት አድርጓታል። "ባንቺ የተነሳ በቀዬው በሀገሩ መዋረዴ አንሶኝ የባሰ ደህና አካል እንዳለው ሰው አካልሽን እያሳየሽ ትሮጫለሽ?"የሚለው የአባቷ ንግግር እውነትም ብላ ራሷን ጎዶሎ አድርጋ እንድትቀበል አድርጓት አልፏል።

በራሷ ጥረት እና በመምህራኑ ጉትጎታ አማካኝነት እስከ ሰባተኛ ክፍል የተማረችው ነፃነት ከዚያ በላይ የመቀጠል እና የመማር እድሏ በአባቷ ይጨናገፋል። አባቷ ከተማ ገብተው ወደ ወላጆቻቸው ሲመለሱ ከተሜ መስለው ብር ይዘው በሚመጡት የጎረቤቶቻቸው ልጆች ይቀናሉ። እሷም ከተማ ገብታ እንደ ልጆቹ እየሰራች ካፖርት ገዝታ እንድታለብሳቸው በዓመት በሁለት ዓመት አንዴ ብቅ እያለች ከተሜነቷን ለጉረቤት እንድታሳይ ይፈልጋሉ። ትልቁ ጉዳይ ግን በሷ ምክንያት የሚደርስባቸውን ሀሜትና ሽሙጥ ለመሸሽ በማሰብ አዲስ አበባ እንድትሄድ ከወንድማቸው ጋር ይልኳታል።

ነፃነት አዲስ አበባ ከገባች በኋላ ግን ገጠር እያለች ትደነቅባቸው የነበሩ ነገሮች ሁሉ ውሸት መሆናቸውን አገር ቤት ሲገቡ ተብለጭልጨው የሚመጡት የቀበሌዋ ልጆችም ከተማ ውስጥ ኑሮአቸው እዚህ ግባ የማይባልና ከገጠሩ ብዙም ያልተሻለ መሆኑን ሳታውል ሳታድር ትገነዘባለች። እሷም የመጣችው በልፅጋ ቤተሰቧን እንድታበለፅግ ነውና እመቤት በተባለች ዘመዷ አማካኝነት ሰው ቤት ትቀጠራለች። ከህፃንነቷ ጀምሮ ብርቱ ፍቅር የነበራትን ትምህርቷን ግን ለመቀጠል ወስና ቀን ቀን ሰው ቤት እየሰራች ማታ ማታ መማር ትጀምራለች።

በሰው ቤት የሰራተኝነት ህይወቷ ምንም ከሌላቸው ደሃ መናጢ ቤት ሞልቶ ከተረፋቸው ሀብታም ቤት ብሎም ብዙ ቤተሰብ እስካላቸው ድረስ ብዙ ቤት እየገባች ሰርታለች። በአንድ የሰው ቤት ስራ አጋጣሚም ከቤቱ ባለቤት ልጅ ጋር በፍቅር ይወድቃሉ። አነጋገሯ፣ ሳቋ፣ አተያይዋ ሁለመናዋ

ሚች እናቱን መስላው የቀረባት በሰራተኝነት የተቀጠረችበት ቤት ልጅ ልቦናው ወደ ፍቅር ያዘነብልና ይወዳታል። በዚህ ሁኔታ ብዙም ሳይቆዩ በወንድሞቹ አማካይነት የውጭ ሀገር የመሄድ እድል ሲያገኝ ከሄደ በኋላ እንደሚወስዳት ቃል ገብቶላት ይለያያሉ።

በአንድም በሌላም ምክንያት ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት ስትል የኖረችው ነፃነት ከአንድ ላጤ ሴት ቤት ተቀጥራ እየሰራች እንዳለ ዘመድ ነኝ እያለ በሚመላለስ አንድ ሰው ትደፈራለች። ይህም ሰው ከደፈራት በኋላ ከውጭ የመጣ መሆኑን እና ሊያገባት እንደሚፈልግ ይነግራትና አብረው እንዲሆኑ ያስገድዳታል። አሰሪዋ ሴት እንዲሁም ምክር የጠየቀቻት ዘመዷ እመቤት ይገሏኟትና ከሰውዬው ጋር መሆን ትጀምራለች። በአጋጣሚ ውሃ ልትቀዳ ከቤት ወጥታ ወረፋ እየጠበቀች ሳለ በመኪና ሲመጣ የተመለከተችው አንዲት ጉረቤቷ ስለእርሱ ማውራት ትጀምራለች። የአሰሪዋ ውሸማ እንደሆነ ሚስት አሜሪካን ሀገር እንዳለውና መውለድ ስለማትችል በጉዲፈቻ መልክ ህፃን ሊያሳድጉ ተስማምተው እንደመጣ። እዚህ ከደረሰ በኋላ ግን ሀሳቡን ቀይሮ የሰው ልጅ ከማሳደግ ለምን የራሴን ዘር አላሳድግም በሚል አንዷን እንዳስረገዘ አሰሪዋ ስታወራ መስማቷን ታወራላታለች።

ነፃነት ከጎረቤቷ የሰማችውን መረጃ በመያዝ አገባሻለሁ እያለ የሚዋሻትን ሰው ክፉኛ ትጠላዋች። በአንድ አጋጣሚ እቤት ሲመጣም ብዙ ብር ትሰርቀውና ከቤት ትጠፋለች ከአንድ ዘመዷ ጋር ትማከርና ፅንሱን ታስወርዳለች። ይህንኑም በስልክ ትነግረዋለች። በዚህ ድርጊቷ እና ገንዘቡን ዘርፋ በመሰወሯ የተናደደው ሰው ቢያገኛት በወንጀል እንደሚያሳስራት ከተመቸውም እንደሚገላት በመዛት ስልኩን ጆሮዋ ላይ ይዘጋል።

በነፍስ ማጥፋት ወንጀል እና በሌብነት የምትፈለገው ነፃነት ዱካዋን በማጥፋት እና ከአካባቢው በመራቅ ሰው ቤት ገብታ እንደምንም የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ብሄራዊ ፈተና ትወስዳለች። በዚህ መሀከል አሜሪካን ሀገር የሚኖር አንድ ሰው የልጆች ሞግዚት የምትሆንና እንደ እጮኛው አድርጎ ለመውሰድ ልጅ እግር ቢጤ እንደሚፈልግ በዘመዷ በእመቤት በኩል ትሰማለች። ነገሩ እውነት ባይመስላትም እመቤት ግን አንድትሞክር በመወትወት የኤምባሲ ጉዳይ ልታስጨርስላት እየተሯሯጠች ሳለ የፈተና ውጤት በመውጣቱ ውጤቷን ልትቀበል በሄደችበት አጋጣሚ በፖሊስ ትያዝና እስር ቤት ትገባለች።

በድንገት በወንጀል ተይዛ እስር ቤት መግባቷን የሰማው የአሜሪካኑ ወዳጇ እዚያው አሜሪካን አገር የምትኖር እና አዲስ አበባ የመጣች የህግ ባለሞያ የሆነች ጓደኛውን ጥብቅና እንድትቆምላት ያደርግላታል። በወንጀል ክሷት የነበረው ሰውም ሌላ ሴት በመግደሉ ምክንያት እስር ቤት ይገባል። የወንጀሉን ጉዳይ ስትከታተል የነበረችው ሴትም የእርሱ ሚስት ሆና ትገኛለች በመጨረሻም የቀጠሮ ቀን ከጠበቃዋ ጋር ቆሞ የነበረውና ብዙ ጊዜ በእመቤት በኩል ሲረዳት

የነበረው ሰው አብ መሆኑን ታውቅና ትደሰታለች በመጨረሻም ከእስር ቤት በነፃ ስትሰናበት እና አንድ ላይ ሲሆኑ ታሪኩ ያልቃል።

3.3.2. የሴት ገፀ ባሕርያት ምስል በየገቦ ፍሬ

በእነዬ ሺበሽ የገቦ ፍሬ[4] ውስጥ ነፃነት፣ እመቤት፣ አቶ ክብሩ እና አብ ለትንታኔ የተመረጡ ገፀ ባህሪያት ናቸው። ገፀባህሪያቱ እንደቀዳሚዎቹ ምዕራፎች በተሳሉበት የልቦለዱ ዓለም በሰፊው የምናያቸው እና ከዋና ገፀባህሪ ጋር ጥብቅ ትስስር ያላቸው ናቸው።

የገቦ ፍሬዋ **ነፃነት** የልቦለዱ ዋና ገፀባህሪይ ስትሆን ከመነሻው የምንተዋወቃት በወንጀለኝነት ተይዛ ከታሰረች በኋላ በቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤት ስትቀረብ ነው። ይህንን ትዕይንት መነሻ በማድረግ ነው በራሷ *አንደበት "የተወጠረ ስሜቱ ያለፈ ታሪኬን መጮልጮል የጀመረው ድንገት ነበር። ሳላስበው ከፍርድ ቤቱ የተከሳሽ ሳጥን ወጥቼ ገጠር ገባሁ" /እነዬ 2003፣ 10/። በማለት* እዚህ የተገኘችበትን ረጅሙ እና እንደ ሰንሰለት የተያያዘውን ታሪኳን የምትተርከው።

ነፃነት በኖረችበት ማኅበረሰብ ውስጥ ጋብቻ በ5 ዓመት ሲፈጸም እሷ ግን ሳታገባ እስከ 11 ዓመቷ ድረስ ቆይታለች። በዚህ ቆይታዋም ት/ቤት እንድትገባ ተደርጎአል ምክንያቱም በጊዜው የቀበሌ ሊቀመንበር የነበሩት አባቷ እንደሠርቶ ማሳያ ልጆቻችሁን ትምህርት ቤት ማስገባት አለባችሁ በሚለው የመምራኑ ጥያቄ ሳይወዱ በግድ ነበር ያስገቧት። ከሕፃንነቷ ጀምሮ የትምህርት ፍቅር የደረባት ነፃነት በትምህርት ቤቷ ጐበዝ እና ጠንካራ ተምርቷን ወዳድ እንደነበረች በራሷ አንደበት *"የተማርኩትን በትክሰ ወኔ በአትኩሮት አከታተል ስለነበር ፊደሎቹን ለይቶ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም" /እነዬ 2003፣ 14/* ብላ ትገልፃለች።

---

[4] የገቦ ፍሬን የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ትርጉም ሰጥተውት ሰምቻለሁ ለምሳሌ ተራራ ማለት ነው ፣ አጥንት ማለት ነው የሚሉ ሰዎች አጋጥመውኛል በዚህ ምክንያት በልቦለዴ ሳልተረጉመው አልፌዋለሁ ምክንያቱም ለአንባቢው ትቼ ነው። በኔ ግን የገቦ ፍሬ ማለት አዝመራ ሲሰበስብ መሬት ላይ ረግፎ የሚቀር እህል አለ ያ እህል ተደብቆ ከርሞ መሬቱ ላይ ሌላ አህል በተዘራ ጊዜ ተቀላቅሎ ይበቅላል ታስቦ የተዘራ ሳይሆን ተቀላቅሎ የበቀለ ነው ብቸኛ ስለሆነም ፍሬው ከሌሎቹ ወፍራም ነው እንዲህ ዓይነትን ፍሬ "ገቦ ይመስላል" ይላሉ። እኔ ይህንን ነው ለመጠቀም የፈለኩት ለኔ የገቦ ፍሬ ነፃነት ናት ። ነፃነትን ከልጅነቷ ጀምሮ ትኩረት ሰጠቶ የተከታተላት የለም እሷ ግን በራሷ ወድ"ቃ እየተነሳች ትልቅ ለመሆን በቅታለች። ስለዚህ ነፃነት የገቦ ፍሬ ናት ለኔ።(ከእነዬ ሺበሽ ጋር በ18/8/2004 ዓ.ም በተደረገ ቃለ መጠይቅ በደራሲዋ የተሰጠ ትርጉም ነው)

ገና በሕፃንነት አእምሮዋ ትምህርቷን የምትወድ አባቷ ሊያስቀሯት ቢፈልጉ እንኳ እሺ የማትል ለትምህርቷ ቅድሚያ የምትሰጥ ንቁ ልጅ ሆና ተስላለች። ነፃነት ጉበዝ ልጅ ነች በራስ የመተማመን መንፈሷም ጠንካራ ነው። ይህንንም ከሚከተለው ንግግሯ እንመለከታለን።

> *ደስተኛና እና በራስ መተማመን የነገሰብኝ ልጅ ነበርኩ። ወራ ከጀመርኩ ማቋረጥ አልወድም እኔ ልቅደም ባይ ነኝ። እንኳን ሌላውን አባቴን እንኳን ጮክ ብዬ እንዲያዳምጠኝ አድርገው ነበር። እሱም ምንም ያህል የመሰጠው ነገር ቢኖር ቅድሚያ ሰጥቶ ያዳምጠኛል። ይህ ደግሞ ለራሴ ያለኝን ግምት ከፍ አድርጐ በራስ መተማመኔን ያጐላዋል /እነዬ 2003፣ 18/።*

ነፃነት በህፃንነቷ ገና ከጥዋቱ የሚሰማትን ማንኛውንም ነገር በነፃነት መግለጥ የምትችል ደስተኝነቷንና በራስ መተማመኗን ወላጅ አባቷ ሳይቀሩ የተቀበሉላት በቤተሰቧ መሀከል በደስታ የምትኖር ተደርጋ መሳሏን ነው የምንመለከተው።

ነፃ አስተሳሰብ ኖሯት እንድትንቀሳቀስ፣ በነፃ እንድታወራ ያደረጋት የራሷ ጥንካሬ እና በተፈጥሮ ያገኘችው በራስ የመተማመን መንፈስ ነው። ይህ ግን ብዙ አብሯት ሲዘልቅ አናይም በነፃነት ወጥታ የምትገባው ትንሿ ነፃነት በአንድ ታሪካዊ አጋጣሚ ይህንን የበታችነቷን አጉልቶ የሚያሳይ ስድብ በት/ቤት ጓደኛዋ ትሰደባለች። ቸኮለች የተባለች የክፍሏ ልጅ *"አንቺ/ ጅብ ነው አይደል ተረከዝሽን የገመጠው?" /እነዬ 2003፣ 18/* ብላ የሰደበቻት ስድብ በሕይወት ዘመኗ ሁሌ እራሷን ከሰው በታች አድርጋ እንድታስብ ጥቁር ጠባሳውን ጥሎባት አልፏል።

ይህ በነፃነት አእምሮ ውስጥ የማይጠፋ፣ የማይፋቅ ስድብ በየደረሰችበት ከአእምሮ ጓዳዋ ብቅ እያለ ቀና ብላ እንዳትሄድ ከሰው ጋር አውርታ እንዳትግባባ አድርጓታል። ጠንካራ ብቃትና ከሰው ጋር በመግባባት ፈጣን የነበረችው ልጅ በአንድ ጊዜ ባሕርይዋ ተቀይሮ ፈሪ ሆና እናገኛታለን።

ሳታገባ የመቆየቷ ምስጢር ከዚሁ ጋር የተያያዘ መሆኑም ይገባታል። ምን ሆኜ ነው ለሚለው ጥያቄዋም ከቤተሰብ አጥጋቢ ምላሽ አታገኝም። በህይወቷ አስተውላው የማታውቀው የእግሯ እንከን እረፍት ይነሳታል። የቤተሰቡ በተለይም ለአባቷ ውርደት ሆና መኖሯ እየቆየ ይገባታል። በአንዱ የትምህርት ቤት ውድድር ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በሩጫ መሳተፏን የሰሙት አባቷ "በተከበርኩበት አገር አዋረደችኝ" ይሏታል። ባለባት እንከን ምክንያት ባል ማጣቷ ልጆችን በ5

ዓመት መዳርን በለመደ ማኅበረሰብ ውስጥ ለሚኖሩት አባቷ ለአቶ ክብሩ ትልቅ የመንፈስ መሰበር ነበር። በዚህም ምክንያት ነው የሀገሬውን ስድብና ሽሙጥ ፍራቻ ከሀገሯ ወጥታ ወደ አዲስ አበባ እንድትሰደድ የሚያደርጓት። ይህንኑ የአባቷ ስሜት በገዛ አንደበቷ እንዲህ እያለች ትነግረናለች፦

> *በእኔ ምክንያት ቤተክርስቲያን መሳሚያ ፣ለቅሶ መድረሻ ሸንጎ መኃጋገሪያ ሙሉ ነፃነት ሲያጣ ቢጠላኝ ምን ይፈረድበታል። ሰው በየቀኑ ስሜቱ እየተጎዳ፣ በተወለደበትና በኖረበት ሀገር እያፈረ፣ እንዴት ኖረ ማለት ይቻላል? የከረመና የገነገነ ባህል ድንገት ተነስተህ ቅረፍ ብዬ ስለፈረድኩበት አፈርኩ። መጥፎው እንደመልካም ነገር ተቆጥሮ ነግሷልና በመልካም ነገር ማፈርና መሳቀቅ እጣ ፈንታ ሆኗል።ይህን ደግሞ እሱ ብቻ እንዳላመጣው እሱ ብቻ ሊያስወግደው አይችልም /እነዱ 2003 ፣ 90/።*

የተወለደችበት አካባቢ ባህል አባቷ በሰው መህከል እንደልባቸው እንዳይንቀሳቀሱ በእርሷ ምክንያት ተዋርደው እንዲኖሩ አድርጓቸዋልና ለአባቷ ስታዝንላቸው እናያለን። ስለዚህ ብቻቸውን ምንም ሊያደርጉት የማይችሉትን ስር የሰደደ ባህል ባንዴ መንቀል አይቻልም በማለት የወቀሰቻቸው አባቷን እንደገና ይቅርታ ታደርግላቸዋልች። አሁን ላለችበት ህይወት ባህሉን ነው የምትወቅሰው፡፡ ምክንያቱም በአባቷ ላይ የምታየው በአካባቢው አፍሮ እና አንገት ደፍቶ የመኖር ስሜት እንቅፋት የሆነው ባህሉ ያመጣው አመለካከት ነው የሚል እምነት አላት።

የአካባቢው ባህል የሚፈለገውን ክብር ማሟላት ያልቻለችው ነፃነት የልብ ስብራቷን ይዛ ከሀገር ስትወጣ አንድ ተስፋ ግን በውስጧ ሰንቃ ነበር። ትምህርት ተምሮ ራስ የመቻል ታላቅ ተስፋ። ወደ ከተማ ከገባች በኋላ በተለያዩ ቤቶች በቤት ሠራተኝነት ተቀጥራ ስታገለግል የትምህርቷን ነገር መቼም ቸል ብላ አታውቅም። የሰው ቤት በቀያየረች ቁጥር መጀመሪያ የምትጠይቀው በአካባቢው ትምህርት ቤት መኖሩን ነው ጥንካሬዋ በዚህ ውስጥ ሲገለጥ እናያታለን።

ከሌሎች ጋር ባላት ግንኙነትም እንደመሃይም ወይም ምንም ፊደል እንዳልቆጠረ ሰው በአሰሪዋ ትቆጠራለች። የቤት ሰራተኛ ሆነው የሚገቡት መህይም ናቸው ብሎ በሚያስብ ማህበረሰብ ውስጥ ነፃነትም ይሄ እጣ ደረሷት እንደነበር በአንድ አጋጣሚ አሰሪዋ

ያልሰበረችውን እቃ ሁሉ ዘርዝራ ልታስፈርማት የነበረውን ሁኔታ በራሷ እንደበት እንዲህ ትገልጣለች።

> *እኔ ነፃነት ... ከወ/ሮ ሀይወት ቤት ከጥቅምት 26 ቀን ጀምሮ በወር አሰር ብር የተቀጠርኩ ሲሆን ፣በቆየሁበት ጊዜ ሁለት ሸክላ ሳህን፣ አንድ ፔርሙስ ፣ ሁለት ብርጭቆ የሰበረኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ /እነዬ 2003 ፣124/።*

ሰው ቤት የምትቀጠር ሰራተኛ መሀይም ናት ተብሎ በሚቆጠር ማህበረሰብ ውስጥ ሰዎች ለሰራተኛ ያላቸውን አመለካከት ወይም እንዴት አድርገው እንደሚስሏቸው ያሳያል። ነፃነት ለዚህች አሰሪዋ ምንም የማታቅ መሀይም ተደርጋ ነው የተሳለችው።

ነፃነት ፅኑ ዓላማ እና ህይወትን የመቋቋም ጥንካሬ ቢኖራትም በብዙ ቦታ ራሷን ከሰው እኩል ማድረግ ግን ሲያቅታት እናያታለን። በደረሰችበት የህሊና ቁስል ሆኖ የሚያሰቃያት የጎዶሎ ነኝ ስሜት ወደ ፍቅር ህይወት እንዳትገባ እንቅፋት ይሆንባታል። እንደማንኛውም ሰው ለፍቅር የተሸነፈ ልብ ቢኖራትም ውስጧ ተቀርጾ የቀረው የበታችነት ስሜት ግን በሙሉ ልብ ፍቅርን ለመቀበል ሲያዳግታት እናያለን። በተቀጠረችበት ቤት ውስጥ ካለ የቤቱ ባለቤት ልጅ ጋር ፍቅር ብትጀምርም ለማፍቀርና ለመፈቀር የማትበቃ ፍጡር አድረጋ ራሷን ስትወቅስ እናያታለን።

> *በማንም ቢሆን ሊፈቀር እንደማይችል አምኖ የተቀበለው እኔነቱ ማፍቀር የሚለውን መብት ማን እንደሰገሰው አላውቅም። ምስኪን ልቤ! ባላሰበችው ችግር ውስጥ ገባች። /አነዬ 2003፣ 237/*

እንደማንኛውም ሰው ልቧ ለፍቅር ቢሸነፍም እንደሰው ማፈቀር የማትችል ከሰው ሁሉ ያነሰች አድርጋ ነው ራሷን የምትገምተው። አፈቀርኩሽ ብሎ የሚመጠጣውን አብን እንኳን ለመቀበል ስታመነታ ነው የምናያት። በብዙ ነገር ጠንካራ ሆና የምናያት ነፃነት የሰው ሁሉ የበታች ነኝ የሚለው ሀሳብ ግን በሄደችበት ቦታ ሁሉ ዝቀተኝነቷን ሲያውጅባት ነው የምናየው።

ማንኛውም ሰው ላይ ሊደርስ የሚችለውን የአካል ጉድለት እሷ በቀላል አታየውም። ከወጣችበት ማህበረሰብ ከባህሉ ጋር አያይዛ በማየት ቀየውን ለቃ እንኳን ብትመጣም ከውስጧ ሊወጣ

ያልቻለው የህሊና ቁስል ዝቅተኝነቷን አምና እንድትቀበል ያደርጋታል። ይህንን ግን የሰጣት ተፈጥሮ ሳይሆን ማህበረሰቡ ነው።

ነፃነት ያላመነችበትን ነገር የማታደርግ ደፋር ሴት ተደርጋም ተስላለች። በሰው ቤት ቆይታዋ በግድ ከደፈራት ሰው ጋር አገባሻለሁ በሚል ማባበል ፅንስ እንድትቋጥር ትደረጋለች፡ በኋላ ላይም ለማጎፀን ኪራይነት የተፈለገች ሴት መሆኗን ከሌሎች እንደበት ስትሰማ ይህንን ማጎበረሰብ በመቃወም ፅንሱን ታቋርጣለች። ማህበረሰቡ የሚጭንብኝን ማንኛውንም ነገር መቀበል የለበኝም ስትል እንሰማታለን።

> *'በፍፁም! ዘጠኝ ቢሞላም አብረን እንሞታታለን እንጂ እናትነቱን የማያውቅ ልጅ አይወለድም! ተፈጥሮ እንደ ሁሉም ዘሬን እንድተካበት እንጂ ሌላ መራራ የግፍ ጆንያ እንድሸከምበት አይደለም ማህፀን የሰጠችኝ። ይህ ማህበረሰብ የተለያየ የግፍ ቀንበሩን ሲያሸክመኝ እያየሁ እስክወድቅ በእሽታ ተሸክሜ መንገዛገዝ የለብኝም ያቅሜን ያህል መታገልና እምቢ ማለትን መቻል አለብኝ /እነዬ 2003 ፣288/።*

በአጠቃላይ ነፃነት ከልጅነቷ ጀምሮ ትልቅ ሰው እስከሆነችበት ጊዜ ድረስ ከቤተሰቧ ጀምሮ በተለያዩ ሰዎች የጎሊና እና የአካል ጉዳት ሲደርስባት በሚያሳይ መልኩ ተቀርፃለች። የአካሏ ጎዶሎ መሆን ባስከተለባት ለጋብቻ ያለመፈለግ እና እንደ ሀገሬው ባህል አለማግባት በህይወት ዘመኗ ራሷን የበታች አድርጋ እንድታስብ ከሰዎች ጋር በሚኖራት ግንኙነት ሁሉ ራሷን እንድትጠራጠር አድርጓታል። በተቀጠረችበት ቤት መደፈሯ ለአካል እና ለህሊና ጉዳት አጋልጧታል። ባህሉና እምነቱ በወላጆቿ ላይ በፈጠረው ጫና ምክንያት ከሀገሯ ወጥታ በመሰደዷ ብዙ መከራ ደርሶባታል። ነፃነት በገጠር በሕፃንነታቸው ለሚጸሩ እና በተለያየ ምክንያት ወደ ከተማ ተሰደው የመከራ ገፈት ቀማሽ ለሆኑት ሴቶች ሁሉ ትዕምርት ነች እነርሱን ትወክላለችና።

<u>በገቦ ፍሬ</u> ውስጥ የምናገኛት ሌላዋ ገፀባህሪ እመቤት ናት። በልቦለዱ ለመጀመሪያ ጊዜ ተያዥ በመሆን ነፃነትን ሰው ቤት ያሰገባቻት በየጊዜውም ከሰው ቤት ስትወጣ እየፈለገች የምታስገባት ዘመዷ ናት። አዲስ አበባ በመምጣት እና ሰው ቤት ረጅም ዓመት በመስራት ትቀድማታለች። እመቤት አንድ ቦታ ላይ ብቻ እድሜዋ የገፋ መሆኑ ከመገለፁ በስተቀር አካላዊ መልኳ ምን እንደሚመስል አይታወቀም። በእድሜ የገፋች መሆኗ ብቻ

ተነግሯል። እመቤት በነፃነት ሕይወት ውስጥ ብቅ ጥልቅ እያለች የምትመክራት፣ ከሰው ቤት ስትወጣ የምታጽናናት ፣ ሁሌም በጎ የምታስብላት ጥሩ ሰብዕና ያላት ሆና ተቀርፃለች። ለነፃነት የአክስት ልጅ ዘመዷም ናት። በመጀመሪያ አዲስ አበባ እንደመጣች ሰው ቤት የምታስገባት እሷው ነች።

በቅጡ ባልለመደችው የሰው ቤት እና የሰው ፀባይ የተደናገረችው ነፃነት አሠሪዋ በሰደበቻት ጊዜ መልስ ስትመልስላት ሰው ቤት ስትኖር እንዴት አንገቷን ደፍታ መኖር እንዳለባት ስትነግራት እናያለን። "ባለጌ ያሳደገሽ" ብላ የሰደበታችን አሠሪዋን መልሳ በመሳደብ ከቤት ስትወጣ ደመወዟ ለመቀበል ስትሄድ ነበር ስሞታውን ከአሰሪዋ የሰማችው። "ነፃነት አባቴ ተሰደበ" በማለት የተደፈርኩ ባይነት ወኔ ቢቀሰቀስባትም እንዴት መኖር እንደሚገባት ስትመክራት እናያለን።

> *"አ... አንቺ እኮ ማወቅ ያለብሽ አባትሽ ምንም ሆነ ምንም ከመቀጠር አላዳነሽም እሱ ስንት ነገር ኢያሰው ለአስር ብርና ለቁራሽ እንጀራ ስደት ሲያበቃሽ፣ አንቺ በሰው ነገር ስሙን ጥበቃ ክሥራ መፈናቀል አለብሽ? ምንም ሁኚ፣ ከየትም ነይ፣ ከሰው ቤት እስክገባሽ ድረስ የሚያግዙሽንም የሚናጋሩሽንም አንገትሽን ደፍተሽ ማስተናገድ ብቻ ነው ያለብሽ። ማንም ለአንቺ ስሜት ተጨንቆ ቃላት እንዲመርጥልሽ አትጠብቂ።" /አነዬ 2003፣ 107/።*

እመቤት መካሪዋ ናት ከሷ ቀደም ብላም ከሰው ቤት ስለገባች የእያንዳንዱን ሰው አመል ታውቃለች። ሰው ቤት እየሠሩ የእናት የአባት የራስ ክብር የለም። እንደሱ ከሆንሽ የትም ቤት ልትሠሪ አትችይም እያለች ስትመክራት ነው የምንሰማው።

የገባችበት ቤት ሴት ዓረብ አገር እንደሚልኩ እና እሷንም እንደሚልኳት ቃል መግባታቸውን ከነገረቻት ግዜ ጀምሮ ስለ ዓረብ አገር መጥፎነት እያወራች እንዳትሄድ ትመክራታለች። ነፃነት የተማረች በመሆኗም የመንግሥት ሥራ ብታገኝ ብላ ባላት ትርፍ ጊዜ ሁሉ በየማስታወቂያ ሰሌዳው እየሄደች ሥራ ስትፈግላት ትውላለች። በተቻለ መጠን ከሰው ቤት የተሻለ ሥራ አግኝታ የዓረብ ሀገር እቅዷን እንድትቀይር ብዙ ጊዜ ስትመክራት እናያለን። ይህንንም በራሷ በነፃነት አንደበት እንሰማለን።

በተለይ በአንድ ጓደኛዋ አርዳታ ከአንድ ሆቴል ቤት ውስጥ የወጥ ቤት ስራ አግኝታ ለብቻዋ ተከራይታ መኖር ከጀመረችባት ቀን ጀምሮ እንደሷው የተሻለ ነገር እግኝቼ የአረብ ሀገር ወሬዬን እርግፍ አድርጌ እንድተው የማትሞክረው የለም። ለኔ ስትል ያለቻትን ትርፍ ጊዜ ሁሉ ከማስታወቂያ ሰሌዳዎች ካዛመደቻቸው ቆይታለች።/እነዬ 2003 ፡ 328/

ከአብ ጋር በስልክ በመገናኘት እሷ በማታውቀው መንገድ ወደውጭ እንድትሄድ ሁኔታዎችን ታመቻችላታለች። በምስጢር ሞግዚትነት የሚፈልግ ሰው መኖሩንና ሰው ፈልጊ እንዳላት እሷም ብትሄድ እንደሚሻል ስትነግራት እና ሁኔታዎችን ሁሉ ስታመቻችላት እናያለን።

በነፍስ ግድያ ወንጀል ተከሳ ፍርድ ቤት ስትቀርብም እመቤት ከጉኗ የነበረች ታማኝ ዘመዷ እና ጓደኛዋ ሆና ተስላለች። ባጠቃላይ እመቤት የዋህ ቅን አሳቢ አርቆ አስተዋይ ሆና ተስላለች ይህንንም ባህሪዋን ለዘመዷ በምታደርግላት ነገሮች ውስጥ ሁሉ ይታያል።

3.3.3. የወንድ ገፀ ባሕርያት ምስል በየገቦ ፍሬ

አቶ ክብሩ የነፃነት አባት ናቸው። በልቦለዱ ውስጥ የኖሩበት ባህል እና ሃይማኖት ተጭኗቸው የባህሉ እና የአስተሳሰቡ ተገዢ ሆነው የሚኖሩ ሰው ናቸው ። በተወለዱበት እና ባደጉበት ቀዬ ውስጥ ተከብረውና ተፈርተው መኖር የሚፈልጉ በዚያም ምክንያት ደግሰው የሚያበሉ መዳር የሚወዱ በልጆቻቸው ክብርን ማትረፍ የሚፈልጉ ገፀባህሪ ሆነው ተቀርፀዋል። በዚህም ምክንያት ይህንን ዝናና ክብር ልታስገኝላቸው ይልቁንም በማህበረሰቡ ውስጥ ተሸማቀው እንዲኖሩ ካደረገቻቸው ከልጃቸው ነፃነት ጋር በየጊዜው ሲጣሉ እናያለን።

የሴት ልጅ ከቤት መውጣት በተለይ ዘመናዊ ትምህርት መማርን እንደ ነውር ይቆጥሩታል። የቀበሌ ሊቀመንበር እንደመሆናቸው መጠን አርአያ እንዲሆኑ እና ልጃቸውን እንዲያስተምሩ በመምህራኑ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ልባቸው ባይፈቅድም ለነፃነት በፊት ለፊት የሚያስተምሩ ሆነው ሲቀርቡ በውስጣቸው ግን መማሯን በፍፁም የሚቃወሙ ሆነው ነው የተሳሉት። ይህንን ለትምህርት ያላቸውን አሉታዊ አስተሳሰብ በነፃነት በራሷ አንደበት እንዲህ ሲነገር እንሰማለን።

ቢሆንም ባይሆንም መስከረምን ጠብቄ የሚኒስትሪ ካርዴን መጨበጥ ፈልጌአለሁ። ትምህርት ቤታችን ከዚያ በላይ አታራምድም እንጂ እኔስ ሰባተኛንም በትዕግስት መሟገቱ የማይቀር ነበር።እያደሩና ቀለብ እየጫኑ መማር ግን ርቆ የተሰቀለ ብቻ ሳይሆን ተሰቅሎ የማይወርድ ተስፋ ይመስላል። አባቱ የሚጭነው እህል፣ ወይም ለቤት ኪራይ የሚከፍለው ገንዘብ ያጣል ብዬ አይደለም ግን እሱ በደስታ እና በእምነት ያን ያደርግልኝ ዘንድ እኔ ወንድ ሁኜ መፈጠር ነበረብኝ /እነዬ 2003፣66/።

መማርን እንደ ነውር የሚቆጥሩት አቶ ክብሩ የትምህርትን ጥቅም የማያውቁ ሆነው ሳይሆን ባህሉን እና የአካባቢውን ማህበረሰብ ፍራቻ ነው። ትልቅ ክብር የሚሰጡአቸው ወንዶች ልጆቻቸው እንኳን የሚመርጡት የቤተክርስቲያንን ትምህርት ነው። ዘመናዊውን ትምህርት ብዙም የማይደግፉት አቶ ክብሩ ከሰዎች ጋር ሲሆኑ ግን ስልጣኔን የሚወዱ አስመሳይ ባህሪን የተላበሱ ሆነው ተስለዋል።

የህገሩን ባህል እጅግ አጥብቀው የሚያከብሩት አቶ ክብሩ ነፃነትን ከቀዬዋ ተለይታ ገና በትንሽነቷ አዲስ አበባ እንድትገባ የሚያደርጉት የአካባቢውን ባህልና ወግ ለመጠበቅ እንዲሁም የራሳቸውን ክብር ፍለጋ ነው። እንደሌሎቹ ወንድምና እህቶቿ ድረው እና ኩለው ደግሰው አለማብላታቸው፣ አማች አለማፍራታቸው፣ ባለባት የእግር ላይ እክል የተነሳ ባል አለማግኘቷ በማህበረሰባቸው ውስጥ ምን ያህል አንገታቸውን ያሰደፋቸው መሆኑን በአንድ አጋጣሚ ከእርሷ ጋር በተፈጠረ ጥል *"አረ ይሀችን ወሰፌ ! ማን ትኩሪያን ይላታል። ደርሳ በነገር ትወጋለች እንጅ!ምን ይላል እና መሆኑ ነው? እንደ አሀያ በየሚዳው እየተዛለለች አፍሬ መኖሬ ሳያንስ!...ንግግሩን ብስጭት አቋረጠው። /እነዬ 2003፣ 65/* በማለት እንደገለፀ ትናገራለች።

ባጠቃላይ አቶ ክብሩ ክብራቸውን የሚፈልጉ ከልጃቸው ይልቅ የራሳቸውን ክብር የሚያስቀድሙ ራስ ወዳድ ናቸው። በልቦለዱ እጅግ ወግ አጥባቂ ባህላቸውን የሚጠብቁ የማህበረሰቡን ትችት በእጅጉ የሚፈሩ እና አስመሳይ ሆነው ነው የተቀረፁት። የባህል የወግ የእምነት ሰለባ ሆነው ነው የተሳሉት።

ሌላውን ገፀባህሪ አብን በዋና ገፀባህሪዋ በነፃነት ህይወት ውስጥ ነው በደንብ የምናየው። በሰው ቤት ሰራተኝነት በገባችበት አንዱ ቤት የቤቱ ባለቤት ልጅ ነው አብ። ነፃነትን

ይወዳታል በተለይ አንባቢ መሆኗ አንዲቀርባት አድርጎታል። ከዚህም በተጨማሪ ነፃነት ቁርጥ ሟች እናቱን ስለምትመስል ይወዳታል እናም ይቀርባታል ። ይህ መቀራረብም አድጎ ወደፍቅር ያመራል። የአብን አካላዊ ገለፃ በነፃነት አንደበት ነው የምንሰማው።

> *የቀይ ዳማ መልክ መልካም ወጣት ነው። በስርዓት የተስተካከለው ፀጉሩ በአዲስ ግራጫቲ ሸርት ላይ ቆዳ ጃኬት ጋር ተባብሮ የአንገቱን ውበት አጉልቶታል። ረዘም ያለ ቁመቱ ከተስተካከለ ቅርፅ ጋር ለአይን ይማርካል/አነዱ 2003 ፡150/።*

አብ ከሰው ጋር መነጋገር የማይወድ ዝምተኛ ከራሱ ቤተሰብ ጋር እንኳ ተቀራርቦ የማይጫወት በቤተሰቡ ዘንድ የሚፈራ ሁኖ ተቀርጿል። ይህንንም ነፃነት ለመጀመሪያ ጊዜ ቤታቸው ተቀጥራ ስትገባ ለመታዘብ ችላለች። ከመኝታ ክፍሉ የሚወጣው ወደውጭ ሲወጣ ብቻ ነው። ምግብ እንኳን ተቀላቀሎ ሲበላ አይታይም እዚያው መኝታ ቤቱ ድረስ ሄዶለት ነው የሚመገበው ።ይህን ሁሉ ፀባዩን የተገነዘበችው ነፃነት ቤቱን አዕጂልኝ ባላት ባንዱ ቀን ከመኝታ ቤቱ ያገኘችውን ልቦለድ መፅሃፍ ስታነብ ድንገት ሲደርስባት በድንጋጤ ሰታለቅስ እና ሲያባብላት እናየዋለን ምክንያቱም እናቱ ሳይቀሩ ትንንሾቹን ልጆች የሱን እቃ እንዳይነኩ ሲያስጠነቅቋቸው ትሰማ ነበርና ነው እሱ ግን ከጠበቀችው በላይ ትሁት ሆኖ ሲያባብላት እንመለከተዋለን።

> *በእሀትና በወንድሞቹ ብቻ ሳይሆን በእናቱ ዙምር የሚፈራ ሰው ለእኔ የሚራራበት ልብ ይኖረዋል ብዬ አልገመትኩም ቢቀበለውም ባይቀበለውም የይቅርታ ቃላት ማውጣት ፈልጌ አንደበቴን ማዘዘ አቃተኝ። ይልቁንም አፌን ለመክፈት በታገልኩ ቁጥር እንባዬ ያለገደብ መውረድ ጀመረ። እሱ ሁኔታዬ ሁሉ አግራሞትን የሚጨምር ሆነበት መሰለኝ ቆሞ መገረሙን ቀጠለ። ሆኖም እየተደራረበ የሚፈሰው እንባዬ ሳያስጨንቀው አልቀረም /አነዱ 2003 ፡152/።*

አብ ዝምተኛ ነው አቤቱ ሲገባም ከማንም ጋር ሲነጋገር አይታይም። በዚህም ምክንያት ቤተሰቡ በሙሉ ይፈራዋል ከሰው የማይገጥም የተባለለት አብ ግን መፅሐፎቹን እየወሰደች እንድታነብ ከመፍቀዱም በላይ እሱም እሷን ተከትሎ አንባቢ ሲሆን እናየዋለን የባህሪ ለውጥ። አንባቢ መሆኗ አግራሞት የፈጠረበት አብ ማንም ሊወደኝ አይችልም ብላ ተስፋ ቆርጣ የተቀመጠችውን ነፃነትን ሰያፈቅራት እናያለን። ማፍቀሩን ያወቀው ጓደኛው ብዙ

ልዩነት በመሃከላቸው እንዳለ ሲነግረው አይቀበለውም። እግሯ ላይ ባለ እክል ምክንያት ባህሉ ባል እንዳታገባ ያደረጋትን ሴት ነው አብ የሚቀበላት። በእሱና በጓደኛው መሀከል የነበረው ምልልስም ይህንኑ የእሱን እምነት የሚያሳይ ነው። ጓደኛው ከእርሷ ጋር የፍቅር ህይወት ውስጥ መግባቱን በተቃወመው ጊዜ በሁለቱ መሀከል የነበረው ልውውጥ የሚከተለውን ይመስላል።

> *"...እኔ የለሁበትም !አካሄድህን ደጋግመህ አስበህ መንገድህን ብትቀይስ ግን ደስ ይለኛል*
> *"ግድ የለህም! እኔም ለህይወቴ ማንንም ጋብዤ አላውቅም። ያገባኛል ብለህ ለሰጠሽኝ ምክር ግን ሳላመሰግንህ አላልፍም!"*
> *"ጥሩ ግን ቤተሰብ ፣ ማህበረሰብ የሚባሉ ጣጣዎችንም አክሴፕት አድርጎ መጓዝ አይከፋም!"*
> *"እኔ የማልወደው እነዚህን ጣጣዎች አይደል። ህይወት እንገሌ በፈለጉት ፣ እነ እንትና በሚወዱት የሚገነባ አይደለም..." /እነየ 2003፣ 170/*

በማህበረሰቡ ውስጥ ሰርዶ ያለውን ኋላ ቀር አመለካከት ችላ በማለት ከነዓነት ጋር ፍቅር ሲጀምር እናያለን። ከአገር የመውጣት እድል አግኝቶ ሲሄድ እንኳን አይረሳትም እዚያው ሆኖ በዘመዷ በእመቤት በኩል አስፈልጎ ሊወስዳት ብዙ ነገር ሲያመቻችላት እናያለን። በታሰረችም ጊዜ ጠበቃ ቀጥሮ ከእስር ቤት ያስፈታታል።

ባጠቃላይ አብ መልካም የተማረ አስተዋይ ሁሉን ሰው በእኩል አይን ማየት የሚወድ አሮጌውን ባህል እና አምነት የማይቀበል ገፀባህሪ ተደረጎ ነው የተሳለው።

4. በሶስቱ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የሚታዩ ተመሳስሎዎች እና ልዩነቶች

በዚህ ምዕራፍ በሶስቱ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ያሉ ተመሳስሎዎችና ልዩነቶች ትንተና ተደርጎባቸዋል። ንዕዕሩ በሶስቱም ልቦለዶች ውስጥ የልቦለዶቹ ማዕከል ተደርገው በተሳሉት ዋና ገፀባህሪያት ላይ የተደረገ ነው። ምክንያቱም አብዛኛው ተመሳሰሎና ልዩነት ጎልቶ የሚታየው ዋና ገፀባህሪያቱ ላይ ብቻ በመሆኑ ሌሎቹ እና ንዑሳን ገፀባህሪያት ላይ የምናገኘው ተመሳስሎና ልዩነትም ከዋና ገፀባህሪያቱ አንፃር የተነፃፅሯል። ከዚህ አንፃር የዋና የገፀባህሪያቱ የፆታ፣ የቤት ሰራተኝነት ፣ የዋና ገፀባህሪያቱ አባቶች ፍላጎት ፣ እስር ቤት ፣ ራስን መቻል ፣ ረዳት መፈለግ በሁሉም ልቦለዶች የሚታዩ ተመሳስሎዎች ሲሆኑ ዋና ገፀባህሪያቱ እስር ቤት የሚገቡበት ሰበብ፣ ከእስር ቤት የሚወጡበት መንገድና እጣ ፈንታቸው ልዩነቶች ሆነው በዝርዝር ተተንትነዋል።

4.1. ተመሳስሎ

4.1.1.የዋና ገፀ ባህሪያቱ የፆታ ተመሳስሎ

በፀሐይ መላኩ እመ ምኔት ፣ በየዝና ወርቁ የደራሲዋ ፋይል ፣ እና በእነዬ ሺበሺ የገቦ ፍሬ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የየልቦለዶቹን ታሪኮች ከመጀመሪያው እስከ ፍፃሜው ድረስ ይዘው የሚዘልቁ ሶስት አበይት ገፀ ባህሪያት ሴቶች ናቸው። በእመ ምኔት ዘርትሁንን ፣ በየደራሲዋ ፋይል ፅዮንን ፣ በገቦ ፍሬ ነፃነትን እናገኛለን።

ሴት ደራሲያኑ በልቦለዶቻቸው አማካይነት ወደ ተደራሲው እንዲደርስ የፈለጉትን አንዳች ቁምነገር እንዲያስተላለፉላቸው በዋናነት የመረጡአቸው ገፀባህሪያት ከወንዶቹ ይልቅ ሴቶቹን ነው። ወንዶቹ ገፀባህሪያት በዋና ገፀባህሪያቱ አቀንቃኝነት የሚጓዘውን ታሪክ እንዲያጎለብቱ ፣ ዋና ገፀባህሪያቱን አጉልተው እንዲያሳዩ ፣ በመሀከላቸው በሚኖረው እርስ በርሳዊ ግኑኝነት ሰብዕናቸውን ፣ አመለካከታቸውን ፣ ፍላጎታቸውን እና ህልማቸውን በይበልጥ የሚያሳውቁን በዙሪያቸው ያሉ ንዑሳን ገፀባህሪያት ሆነው ተስለዋል።

ዋና ገፀባህሪያቱ በሴትነታቸው ከቤተሰባቸው ጀምሮ ከማህበረሰቡ የሚጠበቅባቸውን ማንኛውንም ነገር እንዲፈፅሙ መገደዳቸው ያመሳስላቸዋል። ለምሳሌ የእመ ምኔቷ ዘርትሁን ልጅ ወልዳ ዘር እንድትተካ በአባቷ ትገደዳለች። በራሷ ፈቃድ ተጉላ መነኩሴ መሆንን ሳይሆን ማህበረሰቡ አባቷም የሚያምኑበትን ልጅን ድሮ ወግ ማዕረግ አይቶ ዘር መተካት እንዳለባት በአባቷ ይነገራታል። የደራሲዋ ፋይል ፅዮን ከእናቷ ጋር

የምትጋጭበት ዋና ጉዳይ እንደ ሴትነቷ ጓዳ ገብታ አለመስራቷ ፣ ብዙውን ጊዜ ከአባቷ ጋር ቁጭ ብላ ስለድርሰት ጉዳይ ማውራቷ በእናቷ ዘንድ የጋጠወጥነት ስም ሲያሰጣት እንመለከታለን። የጎቦ ፍሬዋ ነፃነት ከተወለደችበት መንደር ገና በህፃንነቷ ተሰዳ ሰው ቤት ለመቀጠር የምትበቃው በሀገሩ ወግ እና ልማድ ሴት ልጅ ማግባት ባለባት የጋበቻ እደሜ ሳታገባ በማላለፏ በእርሷ የተነሳ በቤተሰቡ ላይ የሚደርሰውን ነቀፋና ሽሽት ነው።

ባጠቃላይ ሴት ደራሲያኑ ለየልቦለዶቻቸው ሴቶችን በዋና ገፀባህሪነት መቅረፃቸው ፣ እንዲንቀሳሱ በፈቀዱላቸው የልቦለዱ ዓለም በሴትነታቸው ምክንያት በቤተሰብ ፣በማህበረሰብ፣ በባህል የሚደርስባቸውን ተፅዕኖ ለማሸነፍ የሚጥሩ ጠንካራ ፣ ትሁት፣ በራሳቸው ሀሳብ የሚፀኑ፣ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚታገሉ እና ከዓላማቸው ፈቀቅ የማይሉ አድርገው መሳላቸው ተመሳስሎውን ይበልጥ ያጎላዋል። ለሶስቱም ገፀባህሪያት የተሻለ ሰብዕናን ማላበሳቸው ለያታ አቻዎቻቸው ማድላታቸውንም ጭምር ያሳየናል።

4.1.2. የሰው ቤት ሰራተኝነት

በልቦለድ ዓለም ደራሲው ገፀባህሪያቱን ከተለያዩ የህይወት ገፅታዎች አምጥቶ የተለያየ ደረጃ ሰጥቶ ይቀርፃቸዋል ። በልቦለዱ ውስጥ እንደሚፈለግባቸው የስራ ድርሻ የተማረ ፣ ገበሬ ፣ መምህር፣ ወዛደር፣ የቤት ሰራተኛ ፣ ዶክተር ... ወዘተ በመሆን እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋቸዋል። ገፀባህሪያቱ በደራሲው እንደተሰጣቸው ቦታ ዋና ገፀባህሪያት፣ ንዑሳን ገፀባህሪያት ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ።ለጥናት በመረጥኳቸው ሶስት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የምናገኛቸው ሶስቱም ገፀባህሪያት በሰራተኝነት አገልግለዋል። ሰው ቤት በሰራተኝነት የሚቀጠሩበት መንስኤ የተለያየ ይሁን እንጂ ሰው ቤት በሰራተኝነት መቀጠራቸው በእጅጉ ያመሳስላቸዋል።

ሰው ቤት የሚገቡበት የየራሳቸው ዓላማ አላቸው። ማንኛውም ሰው ዓላማውን ለማሳካት ይበጀኛል የሚለውን መንገድ መርጦ እንደሚጓዘው ሁሉ እነሱም በየልባቸው ቋጥረው የያዙትን አላማ ከዳር ለማድረስ እና ለማሳካት የሄዱበት መንገድ ወይም የመረጡት የስራ ዘርፍ የሰው ቤት ሰራተኛ ሆነው መቀጠርን ነው። ሶስቱንም በልቦለዱ ዓለም ውስጥ በሰው ቤት ሰራተኝነታቸው በደንብ እናውቃቸዋለን።

በእመ ምኔት የምናገኛት ዘርትሁን ሽሽታ ወደ ገዳም ከመግባቷ በፊት ከክርስትና እናቷ ከግምብ ወግሽ ጋር በመሆን ለእግዚአብሔር ስዕለትን ተስለው ነበር። በጊዜው የደረሰባትን ከባድ ፈተና በሰላምና በጤና አልፋ ለገዳም ህይወት ከበቃች በቤት ሰራተኝነት ተቀጥራ

በምታገኘው ገንዘብ ለገዳሙ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ገዝታ ብፅአት እንደምትሰጥ ቃል በገባችው መሰረት በአቶ ውድነህ ቤት ለሁለት ዓመት በቤት ሰራተኝነት እና በሞግዚትነት ስታገለግል እናያታለን።

<u>የደራሲዋ ፋይል</u> ፅዮንም ከእናቷ ጋር በተፈጠረው ጊዜያዊ አለመግባባት ሳቢያ ከቤት መውጣቷ ራሷን ለመቻል እንዲሁም የአባቷን የአደራ ቃል ለመፈፀም እና የድርሰት ስራዋን ለመጨረስ ስትል በተለያዩ ሰዎች ቤት በቤት ሰራተኝነት ተቀጥራ አገልግላለች።

<u>በየገቦ ፍሬ</u> ውስጥ የምናገኛት ነፃነትም በትንሽነቷ ከአገሯ ወጥታ ሰው ቤት ነው የምትገባው። ሰውነቷ ላይ በነበረ እክል ምክንያት ትዳር ሳትመሰርት 11 ዓመት የሞላችው ነፃነት በሀገሬው ወግና ልማድ መሰረት ለቤተሰቦቿ በተለይም ለወላጅ አባቷ በማህበረሰቡ መህከል አንገት ደፍቶ መኖር ምክንያት ትሆናለች ።

ቤተሰቧ በተለይም አባቷ ባህሉ ያመጣባቸውን ተፅዕኖ ለመሸሽ እና ከሰው ሀሜት ለመዳን ሲሉ እየተማረች 7ኛ ክፍል ደርሳ የነበረች ልጃቸውን ወደ አዲስ አበባ እንድትሂድ ያደርጓታል። በቤተሰቦቿ ግፊት ከሀገሯ ወጥታ አዲስ አበባ የምተገባው ነፃነት ያቋረጠችውን ትምህርት ለመቀጠል በቤት ሰራተኝነት ሰው ቤት ነው የምትገባው።

ዋና ገፀባህሪያቱ የሰው ቤት ሰራተኛ ሆነው መቀጠራቸው ፣ ሰው ቤት የሚገቡበት መነሻ ሰበብ ያላቸው መሆኑ፣ ሰው ቤትን ለዓላማቸው ከግብ መድረስ መጠቀማቸው በእጅጉ ያመሳስላቸዋል። በሰው ቤት በነበራቸው ቆይታ የተለያየ ችግር ያጋጥማቸዋል፣ በአሰሪዎቻቸው አካላዊና ህሊናዊ ጉዳት ይደርስባቸዋል። <u>የእመ ምኔቷ</u> ዘርትሁን በተቀጠረችበት ቤት ባለቤት ባልሰራችው ስራ ነፍሰ ገዳይ ተብላ ለእስር ትዳረጋለች በነፍሰ ገዳይነት መጠርጠሯ ብቻም አይደለም በዚያ ሳቢያ አይኗ ጠፍቶ ለአካል ጉዳት ተዳርጋለች ። <u>የ የደራሲዋ ፋይል</u> ፅዮን አባቷ ከጊዜ በኋላ በተፀናወታቸው የስካር ፀባይ በአካባቢዋ ፣ በትምህርት ቤቷና በሰው ሁሉ ፊት እንድትሸማቀቅ ሆናለች። በአንድ ወቅት በትምህርት ቤት ውስጥ ልጆች ተሰብስበው ስለሰካራም እያወሩ ሲስቁ ከራሷ አባት ጋር በማገናኘት ወሬውን የሚያወራውን ልጅ ባላሰበው መንገድ ዘላ ስታንቀው እናያታለን።ከዚያም አልፎ እስከ ዩኒቨርሲቲ ህይወቷ ድረስ ዘልቆ በመግባት ከሰው ጋር ያላትን ግኑኝነት ቁጥብ ያደርግባታል። በዩኒቨርሲቲው መኝታ ቤት ልጆች ሲስቁ ሲጫወቱ እሷ ዘወትር የምታስበው በስካር ሳቢያ ለሞት የተዳረጉትን አባቷን ነበረ። በወንጀለኝነት ተጠርጥራም ብዙ መንገላታት ደርሶባት እስር ቤት ገብታለች።በተመሳሳይ መልኩ <u>የገቦ</u>

ABABA UNIVERSIT

ፍሬዋ ነፃነት የእግሯ ላይ እክል እንደ እኩዮቿ ባል አለማግባቷ ከሰው የተለየች እንደሆነች እንዲሰማት አድርጎአታል፣ ከቤት ከአባቷ ጀምሮ እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ከዚህ ጋር ተያይዞ ይደርስባት የነበረው ሽሙጥና ስድብ ራሷን ከሰዎች ጋር አስተካክላ እንዳታይ አድርጓት ኖሯል። በሰው ቤት በሰራችባቸው ጊዜያት በሰዎች መደብደብ እስከ መደፈር ድረስ አካላዊ ጉዳት ደርሶባታል። ባጠቃላይ ሶስቱም ሴት ገፀባህሪያት በተመላለሱበት ህይወት የህሊና እና የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

4.1.3. የአባቶቻቸው ፍላጎት

በየልቦለዶቹ የምናገኛቸው ሶስት ዋና ገፀባህሪያት በተለያየ መንገድ የአባቶቻቸውን ፍላጎት ለመፈፀም ሲገደዱ ይታያሉ። አባቶቻቸው የልጆቻቸውን ሳይሆን የራሳቸውን ፍላጎት እና ዓላማ እንዲያሳኩላቸው በተለያየ መንገድ ይገፋፉአቸዋል።

የእመ ምኔቷ ዘርትሁን በራሷ ውሳኔ ብትመነኩስም ይህ ድርጊቷ ግን አባቷን በእጅጉ ሲያስከፋቸው እናያለን። ከእርሷ ሌላ ልጅ ስላልነበራቸው ልጅ ፍለጋ በሀማ ባለቤታቸው ላይ ቅምጥ የነበራቸው አባቷ መመንኮሷን ፣ ባል እንደማታገባና ዘር እንደማትተካ ሲረዱ "ዘር የማግኘት ተስፋዬ መክነ" እያሉ መመንኮሷን እንዳልተቀበሉት በምሬት ሲናገሩ እናዳምጣቸዋለን።

በደራሲዋ ፋይል ውስጥ በድርሰት ዛር የተለከፉት የጽዮን አባትም እሳቸው ሞክረው ያልተሳካላቸውን የደራሲነት መሥያ ልጃቸው ፅዮን ተረክባ ከዳር እንድታደርስላቸው ከልጅነቷ ጀምሮ ሲመክሯት፣ ሞት አፋፍ ላይ ሆነው እንኳ በዚሁ ሞያ እንድትገፋበት በቃልም በጽሑፍም ጭምር ኑዛዜ ሲተዉላት፣ እስከመጨረሻው በድርሰት መሥያ እንድትቀጥል ተፅእኖ ሲያሳድሩባት እናያለን።

የገቦ ፍሬዋ ነፃነት ገና ህፃን ሳለች ትንሿ ልቧ ወደ ትምህርት አዘንብሎ የትምህርትን ነገር የመጥኝ ብትልም በሀገሩ ወግ መሰረት ቶሎ ባል እንድታገባ በሚፈልጉት አባቷ ፊት ግን ይህ ተቀባይነት አልነበረውም። ሴት ልጅን በአምስት ዓመት መዳር እንደ ትልቅ ክብር በሚቆጠርበት ማህበረሰብ ውስጥ ተከብረው የኖሩት አባቷ የራሳቸውን ፍላጎት በማስቀደም ባል አንድታገባ ሲገፋፏት እናያለን።የመዳሩ ጉዳይ አልሳካ ሲላቸውም ሀገሩን ለቃ እንድትሄድ ያደርጓታል።ቀየውን መልቀቋ ብቻም ሳይሆን በየጊዜው በወሬያቸው መሀል

ምሳሌ አድርገው እንደሚያነሷቸው ከተማ ቀመስ የጎረቤቶቻቸው ልጆች እሷም አዲስ አበባ ገብታ ስራ በመስራት ገንዘብና ልብስ እንደትልከላቸው ጭምር ይፈልጋሉ።

ዕዮን የአባቷን ፍላጎት ለመፈፀም ከሞቱ በኋላ እንኳን የሙት መንፈሳቸውን ለማስደሰት በድርሰት ስራዋ ቀጥላ ለፍፃሜ ስታበቃ እናያታለን። የአባቷን ክብር ወዳድነት በእጇ የምታከብረው ነፃነት በትምህርት ራሷን ችላ ፣ስራ ይዛ ፣ተለውጣ በዚያ ባፈሩባት ማህበረሰብ መሀከል ልታሰከብራቸው ስትጥር እናያታለን። ይህንን በመናቅ ወደ ምንኩስናው ዓለም ተጠቃላ የገባችው ዘርትሁን እንኳ በመውለድ ፍላጎታቸውን ባታሟላም አባቷ ባንድ አጋጣሚ ከሰራተኛቸው ጋር በፈፀሙት ስህተት መወለዱን የማያውቁትንና እሷ በድብቅ እየረዳች ያሳደገችውን ወንደሟን አምጥታ ስታስተዋውቅ እና ለልጅ ያላቸውን ፍላጎተ ስታሟላ ነው የምናያት።

ባጠቃላይ ገፀባህሪያቱ በሀሳብም በድርጊትም የወላጆቻቸው ተገዢዎች ናቸው። በደራሲዎቻቸው ጠንካራ እና የራሳቸውን አላማ አንዲያሳኩ የሚጥሩ ገፀባህሪያት ተደርገው ቢሳሉም የወላጆቻቸው ፈላጎት ተፅዕኖ ሲያይለባቸው እና ይህንን የወላጆቻቸውን ፍላጎት ለማሳካት እና ወላጆቻቸውን ለማስደሰት በህይወት ዘመናቸው ሲጥሩ እናያቸዋለን ።

4.1.4. መታሰር

በሶስቱም ልቦለዶች ውስጥ የምናገኛቸው ሶስቱም ዋና ገፀ ባህሪያት ሌላው የሚያመሳስላቸው ነገር በእስር ቤት ህይወት ያለፉ መሆናቸው ነው። መታሰራቸው ብቻም ሳይሆን ለእስር የሚያበቃቸው ጉዳይ ጭምር ተመሳሳይ ነው በነፍስ ግድያ ወንጀል መጠርጠር።

<u>የእመ ምኔቷ</u> ዘርትሁን በሰራተኝነት በተቀጠረችበት በእነ አቶ ውድነህ ቤት የአቶ ውድነህን ልጅ ህይወት አጥፍታለች ወይም እስከ ህይወቷ ሰውራታለች በሚል በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ተጠርጥራ ነው እሰር ቤት የምትገባው። <u>በ የደራሲዋ ፋይል</u> ውስጥ ዕዮን ለሁለተኛ ጊዜ ሰራተኛ ሆና በገባችበት ቤት አስሪዋ የነበረውን ከሊልን ገድላዋለች በሚል ተጠርጥራ ከእስር ቤት ትገባለች። <u>በገቦ ፍሬ</u> ውስጥ ነፃነት ፅንስ አስወርዳለች ፣ነፍስ አጥፍታለች በሚል ነው እስር ቤት የገባችው።ሶስቱም ዋና ገፀ ባህሪያት በቤት ሰራተኝነት በተቀጠሩበት ቤት ውስጥ ከነፍስ ግድያ ወንጀል ጋር በተያያዘ ነፍስ አጥፍተዋል በሚል ክስ ተጠርጥረው ለእስር መዳረጋቸው በእጅጉ ያመሳስላቸዋል።

ዋና ገፀባህሪያቱ የመንፈስም የአካልም አስረኞች ናቸው። በተቀጠሩበት ቤት በተጠረጠሩበት የነፍስ ግድያ ወንጀል በአካል እስር ቤት ገብተዋል በዚህም ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የጀመሩትን ዓላማ ከግብ እንዳያደርሱ ታግደዋል። በመንፈስ የራሳቸው ሃሳብ እና ዓላማ እስረኞች ናቸው ምክንያቱም ከመጀመሪያው አስከመጨረሻው በዚያው ዓላማ ውስጥ ሲዳክሩ ነው የምናያቸው። ዓለማቸውን ለማስፈፀም ከመጣር ውጭ ሌላ አማራጭ ሲጠቀሙ አናያቸውም።

4.1.5. ራስን የመቻል ትግል

ገፀ ባህሪያቱ ባለፉበት የህይወት ጎዳና በራሳቸው ጥረት የሚፈልጉበት ቦታ ለመድረስ የሚጥሩ ፣ የሚፍጨረጨሩ ፣ ጠንካራ ገፀባህሪ ሆነው ነው የተሳሉት።

ዘርትሁን ለእግዚአብሔር የገባችውን ስዕለት ለመፈፀም ገንዘብ ቢያስፈልጋትም ከሀብታም አባቷ ወይም ከሌላ ሰው ብር ስትለምን አናያትም። በጉልበቷ ሰርታ ባገኘችው ገንዘብ ስዕለቷን ስተከፍል እናያለን።

ፅዮንም አባቷ ከሞቱ በኋላ በደንብ ሊረዳት የሚችለው እጮኛዋ /ፍቅረኛዋ/ግርማ አጠገቧ ቢኖርም የሱ ጥገኛ ሆና ለመኖር አትፈልግም። በጓደኛዋ በብዙነሽ አማካይነት የተገኘላትን እና አካሏን ሽጣ እንድትገባበት የተፈለገውን የመንግስት ስራ አትቀበለውም።ይህ የሚያሳየው በሌላ ሰው ላይ ከመደገፍ ይልቅ በራሷ ላይ ያላትን የራስ መተማመን ነው። በሰው ቤት ተቀጥራ ራሷን ለማሸነፍ ስትጥር ነው የምናያት ። በዩኒቨርስቲ ቆይታዋ ወደ ድርሰቱ ዓለም በማድላቷ ምክንያት ውጤቷ አሽቆልቁሎ ከዩኒቨርስቲ ለመባረረ አደጋ ውስጥ በነበረችበት ሰዓት የዩኒቨርስቲ መምህር በነበረው እጮኛዋ ግርማ አማካይነት ከመምህራን ማርክ አንዲለመንላት በጓደኛዋ በተጠየቀች ጊዜ አሻፈረኝ ስትል ነው የምንሰማት።ይህ ባህሪዋ በራስ መተማመኗን እና ጥንካሬዋን በግልፅ ያሳየናል።

ነፃነት አዲስ አበባ ከገባች በኋላ በአእምሮዋ ሰንቃ የያዘቻትን ተምሮ ትልቅ ሰው የመሆን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በጉልበቷ ሰው ቤት እየሰራች 12ኛ ክፍል ድረስ ስትማር አናያታለን። በሰው ቤት ህይወቷ ብዙ ፈተናዎች በመቋቋም ራሷን ለመቻል ስትጥር ነው የምናያት። በምትገባበት ቤት ባሉ ሰዎች የተለያየ ባህሪ ምክንያት ችግር ሲፈጠረባት እና የተለያዩ ሰዎች ቤት ብትገባም ትምህርቷን በፅናት ስትከታተል ነው የምናያት።

ባጠቃላይ ሶስቱም ገፀባህሪያት ለዓላማቸው እስከ መጨረሻው ብርቱ ሆነው የሚታገሉ፣ የሚፈልጉትን ለመፈፀም ወደ ኋላ የማይሉ፣ በሀሳባቸው የሚፀኑና በራሳቸው ሁሉን ነገር ለመፈፀም የሚታገሉ ጠንካራ ገፀ ባህሪያት ሆነው ተስለዋል።

4.2. በሦስቱ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የሚታዩ ልዩነቶች

4.2.1.ሰው ቤት በሰራተኝነት የሚገቡበት ምክንያት

በሶስቱም ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የምናገኛቸው ሶስቱ ሴት ገፀ ባህሪያት የሰው ቤት ሰራተኛ ሆነው መቀጠራቸው በእጅጉ ቢያመሳስላቸውም ሰው ቤት የሚገቡበት ምክንያት ግን የተለያየ ነው።

ዘርትሁን ሰው ቤት የምትገባው ከእንጀራ እናቷ ሞት ጋር በተያየዘ ምክንያት ከቤት ወጥታ የክርስትና እናቷ ቤት በተሸሸገች ጊዜ አምላክ ከክፉ ሁሉ እንዲጠብቃት በተሳሉት ስዕለት መሰረት ለስዕለት የሚያስፈልጋትን ገንዘብ ለማግኘት ስትል ነው።

ፅዮን ሰው ቤት የምትገባበት ምክንያት ከእናቷ ጋር የነበራት ጊዜያዊ ጥል ይሁን እንጂ ዋናው ነገር የአባቷን አደራ እና ኑዛዜ ለመፈፀም ማለትም የድርሰት ስራዋን ከዳር ለማድረስ እንዲረዳት በማሰብ ቄምር ነው።

ነፃነት ሰው ቤት የምትገባው ከህፃንነቷ ጀምሮ የሙጥኝ ብላ የያዘችውን ትምህርት ከዳር ለማድረስ እና ስራ ይዛ ትልቅ ደረጃ ለመድረስ ብሎም አባቷን ለመርዳት ካላት ፅኑ ፍላጎት የተነሳ ነው።

ባጠቃላይ ሶስቱም ገፀ ባህሪያት ወደ ሰው ቤት የሚገቡበት መንገድ እና አላማ የተለያየ ሲሆን በተለይ ሁለቱ /ነፃነትና ፅዮን/ ወላጅ አባታቸውን ለማስደሰት፣ ዘርትሁን ደግሞ ወሰና በገባችበት ገዳማዊ ህይወት ውስጥ አምላኳን ለማስደሰት ብላ ነው።

4.2.2. የገፀ ባህሪያቱ እጣ ፈንታ

ሶስቱም ልቦለዶች የዋና ገፀ ባህሪያቱን መነሻና መድረሻ /እጣ ፈንታቸውን/ ያሳዩናል። ገፀ ባህሪያቱ ከአንድ ጫፍ ተነስተው የህይወት እጣ ፈንታቸውን በሚያሳይ መልኩ አንድ ቦታ ታሪካቸው ሲቆም እናያለን።

በእመ ምኔት ውሰጥ የምናገኛት ዘርትሁን የ 19 ዓመት ወጣት እያለች የሚጀምረው ታሪኳ ይህንን ዓለም በመናቅ እና ወደ መንፈሳዊው ዓለም በማዘንበል እንዲሁም በምንኩስና ህይወት በመወሰን ገዳም ገብታ ስታገለግል፣ እጣ ፈንታዋ በምንኩስና ህይወት ሲደመደም እናያለን።

በአፍላ አድሜዋ ታሪኳ የሚጀመረው የደራሲዋ ፋይል ፅዮንም ገና በጠዋቱ በተማረከችበት የስነጽሑፍ ስራ ውስጥ ጠልቃ በመገባት በዚያ ውስጥ የሚያጋጠማትን ፈተና ሁሉ ተቋቁማ በማለፍ የዘወትር ምኞቷ ተሳክቶላት መጽሐፏን አሳትማ ስታስመርቅ እና የረጅም ጊዜ ጓደኛዋ ከነበረው ግርማ ጋር በትዳር ለመጣመር ቀለበት ስታስር ነው የምናያት።

የገቦ ፍሬዋ ነፃነት ምንም እንኳን ትምህርቷን ጨርሳ ስራ በመቀጠር ትልቅ ሰው የመሆን ምኞቷ ሙሉ በሙሉ ባይሳካላትም የ 12ኛ ክፍልን ጨርሳ እቤታቸው ተቀጥራ በነበረበት ሰዓት በፍቅር ወድቆላት ከነበረ ሰው ጋር በትዳር ስትጣመር እናያታለን።

ባጠቃላይ ሶስቱም ሴት ገፀ ባህሪያት በተለያየ መስመር የሄዱበትን የህይወት ጎዳና አንድ ቦታ ሲቋጩት በገሃድ እናያቸዋለን። ፅዮንና ነፃነት በትዳር ዘርትሁን ደግሞ በምንኩስና ህይወት እጣ ፈንታቸው ይደመደማል።

4.2.3. ከእስር ቤት የሚወጡበት መንገድ

በየልቦለዶቹ ታሪክ እንዳስተዋልነው ሶስቱም ገፀ ባህሪያት ወደ እስር ቤት የሚገቡበት መንገድ አንድ አይነት / በነፍስ ግድያ ወንጀል በመጠርጠር /ቢሆንም ከእስር ቤት የሚወጡበት መንገድ ግን የተለያየ ነው።

ፅዮንና ነፃነት ከእስር ቤቱ በፍቅረኞቻቸው አማካይነት ሲወጡ፣የእመ ምኔቷ ዘርትሁን ደግሞ ከታሰረችበት ወህኒ ቤት የምትወጣው በንሰሀ አባታቸው በመምሬ ዘውዱ አማካይነት ነው።

ባጠቃላይ በልቦለዶቹ የምናገኛቸው እነዚህ ሶስት ሴት ገፀ ባህሪያት ተጠርጥረው ከታሰሩበት የነፍስ ግድያ ከወንጀል ነፃ ቢሆኑም ከእስር ቤቱ ለመወጣት ግን ዋስ የሚሆናቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል። በዋሶቻቸውም አማካይነት ከእስር ቤት ይወጣሉ። ደራሲዎቹ ዋና ገፀ ባህሪያቱን በታሪክ ሂደት ራሳቸውን ችለው የሚንቀሳቀሱ ፣ በራሳቸው

የሚተማመኑ ፣ ጠንካራ አድርገው ቢቀርጿቸውም ከገቡበት አስቸጋሪ ሁኔታ ለመውጣት ግን የወንዶች እገዛ የሚያስፈልጋቸው አድርገው ነው የቀረጿቸው።

ከዚህ የምንረዳው ቁም ነገር በማህበረሰቡ ውስጥ በሰፊው ገኖ የሚታየው ባህል እምነት እና አመለካከት በደራሲዎቹም ውስጥ ስር ሰዶ መኖሩን ነው። ደራሲዎቹ ነፃና ራሳቸውን የቻሉ ሴት ገፀባህሪያት ለመቅረፅ ቢሞክሩም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን በተለይም ሴት ልጅ በራሷ ምንም ማድረግ አትችልም የወንዶች እገዛ ያስፈልጋታል የሚለውን ማህበረባህላዊ እሳቤ ከእነርሱ አልፎ በገፀባህሪያቶቻቸው ላይ ሲንፀባረቅ ታይቷል።ይህ የሚያሳየን አሁንም ልንላቀቀው ያልቻልነውና በውስጣችን ስር ሰዶ ያለ ኋላ ቀር ባህል መኖሩን ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት በተመረጡት ሶስት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ያሉ ወንድ እና ሴት ገፀባህሪያት ምስል ምን እንደሚመስል በሰፊው ተተንትኗል። በልቦለዱ ውስጥ ባላቸው ከፍተኛ ሚና እና ዘላቂነት በተመረጡ ገፀባህሪያት ላይ በማተኮር በየገፀባህሪያቱ የሚታየው ምስል ምን እንደሚመስል ከመጻሕፍቱ መረጃን በመውሰድ ተተንትኗል።

በሶስቱ ልቦለዶች ውስጥ ከተሳሉት ወንድ እና ሴት ገፀባህሪያት ሴት ገፀባህሪያቱ በዋና ገፀባህሪነት የተሳሉ ሲሆን ወንዶቹ ገፀባህሪያት ከእነርሱ ጋር ባላቸው ግኑኝነት ሳቢያ የተሳሉ ናቸው።ሴቶቹ ገፀባህሪያት በተለይም ዋናዎቹ ገፀባህሪያት ጠንካራ ፣ ተስፋ የማይቆርጡ ፣ ታማኝ ፣ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ በየራሳቸው ዓለም መኖር የሚፈልጉ ፣ የሚደርስባቸውን ችግር እና መከራ በፅናት እና በትዕግስት ታግለው ለመውጣት የሚፍጨረጨሩ ናቸው።በተቃራኒው በልቦለዶቹ ውስጥ አብዛኛው የምናገኛቸው ወንድ ገፀባህሪያት ከዋና ገፀባህሪያቱ ጋር ባላቸው ግኑኝነት እንዲሁም በራሳቸው እና በማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ሚና የተለያየ ደካማ ባህሪን ተላብሰው ተስለዋል።

ለምሳሌ <u>የእመ ምኔቷ</u> ዘርትሁን ከቤቷ ከወጣች በኋላ ከገዳማዊ ህይወቷ ጋር ተያይዞ በምታደርገው ጉዞ ባልሰራችው ስራ ተጠርጥራ አይኗ ጠፍቶ እስር ቤት እስክመግባት ትደርሳለች። በዚህ የስቃይ ህይወት ውስጥ ሆናም በእምነቷ ስትፀና ፣ የይቅርታ ሰው በመሆን የበደላትን ሰው ይቅርታ ስትጠይቅ፣ በታሰረችበት እስር ቤት ውስጥ ለእስረኞች መልካም ነገርን በማድረግ የብዙ ሰዎችን መጥፎ ባህሪ እስክመለወጥ ለሌሎች አርአያ ትሆናለች።

<u>የደራሲዋ ፋይል</u> ፅዮን ቤተሰቧ ውስጥ ያለውን ምስቅልቅል ኑሮ ለማደላደል ስትጥር፣ በጓደኛዋ ግፊት አማካይነት የሚገጥማትን ፈተና ተቋቁማ ስታልፍ ፣ በራሷ ተፍጨርጭራ ያሰበችበት ቦታ ስትደርስ ትታያለች። <u>የገቦ ፍሬ</u> ውስጥ የምናገኛት ነፃነትም ከልጅነቷ ጀምሮ የሚደርስባትን የባህል እና የእምነት ተፅእኖ ተቋቁማ በራሷ መንገድ ስትጓዝ ፣ አላማዋን ለማሳካት በምታልፍበት የችግር እና የመከራ ጎዳናዎች ሁሉ በጽናት ስትጓዝ እናገኛታለን።

በተቃራኒው በሶስቱም ልቦለዶች ውስጥ የምናገኛቸው ወንድ ገፀባህሪያት የተወሰኑት ተስፋ የሚቆርጡ፣ የራሳቸውን ሃሳብ ለማሳካት የሚጥሩ ራስ ወዳዶች ፣ ቶሎ የሚከፋቸው (ሆደ

ባሻዎች) ተደርገው የተሳሉ ናቸው። ለምሳሌ የፅዮን አባት አቶ ታምሩ እና የዘርትሁን አባት አቶ ስለሺ. በልቦለዶቹ ውስጥ ከላይ በጠቀሱት ሰብዕናዎች የሚታወቁ ናቸው።ከዚህ በተቃራኒ የፅዮን እና የነፃነት የወንድ ጓደኛ የሆኑት ግርማ እና አብ በዓላማቸው የሚፀኑ ጠንካራ ፣ አስተዋይ ፣ቃላቸውን የማያጥፉ ታማኝ ተደርገው የተቀረፁ ሲሆን በሁሉም ወንድ ገፀባህሪያት ውስጥ ግን ደግነትን እናያለን።

ባጠቃላይ በልቦለዶቹ ውስጥ ያገኘናቸው እና የተመረጡት ገፀባህሪያት ምስሎች ተስፋ የማይቆርጡ ጠንካራ፣ ታማኝ ፣ትሁት ፣ አስተዋይ ፣ ራስ ወዳዶች፣ የባህል እና የእምነት ባሪያዎች፣ ሆደ ባሻ ምስል የሚታዩባቸው ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የልቦለዶቹ ደራሲያን የልቦለዱ ማዕከላዊ ያደረጓቸውን ገፀባህሪያት ጠንካራ ፣ ተስፋ የማይቆርጡ ፣ ራሳቸውል ለመቻል የሚፈጨረጨሩ ፣ አላማቸውን ለማሳካት የሚጥሩ ጠንካራ አድርገው ቢቀርፁአቸውም የወንድ እርዳታ ሲያስፈልጋቸውና ወንዶቹ ሲረዱአቸው ያሳዩናል።

የእመ ምኔቷ ዘርትሁን በዓላማዋ የፀናች ፣ ጠንካራ ተደርጋ ለሌሎች አርአያ መሆን የምትችል ሆና ብትሳልም በመጨረሻ ላይ ከታሰረችበት የእስር ቤት ዋስ በመሆን የሚያስፈቷት የንሰሀ አባታቸው አቶ ስለሺ. ናቸው። የደራሲዋ ፋይል ፅዮንም የተማረች ዩኒቨርስቲ እስከመግባት የደረሰች እና ለርካሽ የወሲብ ጥያቄ ሳትንበረከክ በዓለማዋ ፀንታ ብናያትም በወንጀለኝነት ተጠርጥራ ከታሰረችበት የምትፈታው በወንድ ጓደኛዋ በግርማ አማካይነት ነው።

የገቦ ፍሬዋ ነፃነትም ብዙ ውጣ ውረዶችን በራሷ ያለፈች ፣ ዓላማዋን በማሳካት በኩል ጠንካራ ሆና ብትሳልም አሜሪካን ሀገር የነበረው የወንድ ጓደኛዋ አብ ባመቻቸላት መንገድ ነው ከእስር ቤት ነፃ የወጣችው። ደራሲያኑ ከላይ ካነሳነው ሀሳብ አንፃር ስናያቸው ለዖታ ወገናቸው ማድላታቸውን እንገነዘባለን። ሌላው በደራሲዎቹ ስራዎች ውስጥ በጉልህ የምናየው አዲስ ነገር ሴቶች ከዚህ በፊት ከሚሳሉበት በተለየ መንገድ ሴት ገፀባህሪያቶቻቸውን መሳላቸው ነው። ለምሳሌ ብዙ ጊዜ ሴት ገፀባህሪያት ሲሳሉ ከውበታቸው ጋር ተያይዞ ነው በሶስቱም ልቦለዶች ውስጥ ግን ከውበት ጋር ተያይዞ የሚመጣ ጥገኝነት ፣የተቃራኒ ፆታ ግኑኝነት አናይም ። ከዚያ በተቃራኒው ግን የሴቶቹ ውስጣዊ ሰብዕና ላይ አተኩረው ቀርፀዋቸዋል።

ባጠቃላይ ሴት ደራሲያኑ ዋና ገፀባህሪያቶቻቸውን ጠንካራ አድርገው ቢስሉም የማታ የማታ ለወንድ አስረክበዋቸው ጥንካሬአቸውን ሁሉ ለወንድ ሰጥተው ወንዶች ሲረዱአቸው

ነው የሚያሳዩን። ገፀባህሪያቱን የራሳቸው ጸታዎች እንኳ ሲረዱአቸው ለማሳየት አለመሞከራቸው በማህበረሰቡ ውስጥ ስር ሰዶ ያለው አመለካከት የማህበረሰቡ አንዱ አካል በሆኑት ደራሲዎቻችን ውስጥም ተቀብሮ ያለ መሆኑን ያሳየናል።

በልቦለዶቹ ውስጥ ከወንዶቹ ይልቅ የሴቶቹ ገለፃ እና ሚና ጎልቶ ይታያል። ሌላው ዋና ገፀባህሪያቱ ሴት ቢሆኑም በማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ጎልቶ የሚታይ አይደለም ። ደራሲያቱ ሴት ገፀባህሪያታቸውን ሲቀርፁ የሰው ቤት ሰራተኛ አድርገው በመቅረፃቸው በህብረተሰቡ ውስጥ አነስተኛ የሚባለውን ቦታ ነው የሰጡአቸው። ዋና ገፀባህሪ ሆነው ሰፊውን ሚና ቢጫወቱም ከቤት ሰራተኝነት ግን አያልፉም።

ዋቢ ምንጮች

ቀዳማይ ምንጮች

እነዬ ሺበሽ። *የገቦ ፍሬ* ። አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት ።አዲስ አበባ፤ 2003 ዓ.ም.።

የዝና ወርቁ። *የደራሲዎ ፋይል* ።ብራና ማተሚያ ድርጅት ። አዲስ አበባ፤ 2002 ዓ.ም.።

ፀሐይ መላኩ። *እመ ምኔት*። አዲስ አበባ፤ አማኑኤል ማተሚያ ቤት፤ 2002 ዓ.ም.።

ካልአይ ምንጮች

ብሌን በላይነህ። "የሴት እና የወንድ ገፀ ባህሪያት አሳሳል ንፅፅራዊ ጥናት በሁለት የአማርኛ አጭር ልቦለድ ስራዎች ውስጥ/ በሙሉጌታ ጉደታ እና በሳሙኤል ልጅ ዓለም/"። ቢኤ ዲግሪ ማሚያ ጽሑፍ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ 1992 ዓ.ም ።

ዓለም ባይለየኝ። "ሴቶች በሴቶች ደራስያን ዓይን"። ቢኤ ዲግሪ ማሚያ ጽሑፍ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ 1984 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። *መጽሐፍ ቅዱስ*። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት። አዲስ አበባ፣1980 ዓ.ም።

ዘሪሁን አስፋው። *የስጦሁፍ መሰረታውያን* ። ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ ፣ 1992 ዓ.ም።

ደስታ ተክለወልድ ። *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበቃላት* ።አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፣1962።

ፈቃደ አዘዘ ። የሴቶች አሳሳል በስነጽሑፍ ውስጥ"። በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ለተዘጋጀ ሴሚናር የቀረበ ። ከታህሳስ 12 — 14 1982 ዓ.ም

Chkukure,Gloria Chineze,(1995). *Gender Voices and Choices: Redefining Women in Contemporary African Fiction.* FOURTH DIMENSION PUBLISHING CO.LTD. 64A.City Layout New Haven P.M.B.01164. Enugu-Nigeria.

Ferguson, Mary Anne,(1997). *Images of Women in Literature* (2nd ed) Boston: Houghton Mifflin Company, BOSTON.

http://WWW.storybites.com/literary-terms/characterization-in-literature.php.

Mulumebet Zenebe. (1996) "A Comparative Analysis of the Images of Men and Women in the Works of Some Ethiopian Women Writers", M.A Thesis. Department of Foreign Languages and Literature; AAU.

Napoliyon Kifle .(2000), "Major Themes in the Works of Four Ethiopian Women Writers". M.A Thesis. Department of Foreign Languages and Literature; A.A.U.

Peter Cilds and Roger Fowler.(2006). *The Routldge DICTIONARY of Literary Terms.*(2nd *ed)*: 2 Park Square, Milton Park, Abingdom, Oxon OX14 4RN.

Willaim Chance and Peter Coiller. (1985) . *An Introduction to Literature.* San Diego. Harcourt Brace Jovanovich Publishes.

Seble W/Kidan.(2009)."The Image of Women in Sisay Nigusu's Novels". M.A. Thesis, Department of Foreign Languages and Literature; AAU.AAU.

Zerihun Asefaw . *Women in the Works of Ethiopian Short Story Writers.* P 118 – 127,Vol. 3 Proceedings of the 13th International Conference on Ethiopian Studies, Kyoto, Japan,1997.

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

እኔ ወርቅነሽ ቱፋ በአ.አ.ዩ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ተማሪ ያቀረብኩት ጥናት የራሴ መሆኑን የተጠቀመበትባቸው ተዛማጅ ጽሑፎች በአግባቡ የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም ወርቅነሽ ቱፋ

ፊርማ

ቀን 5/11/2004

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY